

‹‹በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃምሳ የሚደርሱ የሲቪል ማህበራት በረቂቅ አዋጆች ስማወያየት እድል አግኝተዋል››

- አቶ ሄኖክ መለሰ
የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 6

ድጋፍና ስምምነት ኮሮናን ስመከላከል

ገጽ 8


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ:- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



# አዲስ ዘመን

አፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 239 ሚያዝያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

## ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ "ሚሊየን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" የመጻሕፍት ማሰባሰብ መርሐ ግብርን አስጀመሩ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ "ሚሊየን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" የመጻሕፍት ማሰባሰብ መርሐ ግብርን አስጀመሩ፡፡


የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፤ ‹‹ሚሊየን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ›› በሚል መሪ ሀሳብ ለአብርኆት ቤተ መጻሕፍት በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊየን መጻሕፍትን የማሰባሰብ መርሐ ግብር መጻሕፍትን በመለገስ አስጀምረዋል፡፡ በወቅቱ ባደረጉት ንግግርም፤ ንባብ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለማተኮር፣ የማስታወስ ችሎታን ለማዳበር፤ የሌሎችን ስሜት ለመረዳት እንዲሁም የተግባቦት ክህሎትን ለማዳበር የሚያስችል እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ ለዚህም ቤተ መጻሕፍት የማንበብ ባህልን ለማዳበር ትልቅ ሚና እንዳላቸውና፤ ይህም ለአንድ ህብረተሰብ ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ቤተ መጻሕፍት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ቤተ መጻሕፍት መጻሕፍት ማከማቻ ቦታ ሳይሆኑ፤ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በዕድሜ፣ በብሄር፣ በዘር፣ በኀሳና በመሳሰሉት ሳይለይ

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## የአጎዋ ውሳኔ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር የተከናወኑ ሥራዎች ውጤታማ ሆነዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ ለአፍሪካ ከሰጠችው ከቀረጥ ነፃ የንግድ ዕድል (አጎዋ) ኢትዮጵያን መሰረዟን ተከትሎ ውሳኔው በአምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር የተከናወኑ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገለጹ፡፡

አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩት፤ ምርታቸውን ወደ አሜሪካ የሚልኩ ኢንዱስትሪዎች የአጎዋን ዕድል በማጣታቸው የተነሳ ጉዳት ላይ እንዳይወድቁ የተለያዩ ጠርነቶች ተደርገዋል። ጥርነቶቹም ውጤታማ መሆናቸው ታይቷል።

በተለይ የኢንዱስትሪዎቹን የምርት ዓይነቶችን መቀየር፤ የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋትና የምርቶችን ዋጋ የመጋራት ሥራዎች ተፅዕኖውን ለመቋቋም ካስቻሉ ምክንያቶች መካከል ዋነኞቹ ናቸው ብለዋል፡፡

የአጎዋ ውሳኔ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ መላኩ አለበል






## “የሠላም አማራጩ ኢትዮጵያን የሚያድን እስከሆነ ድረስ እየጎመዘዘንም ቢሆን መቀበል አለብን”

**- አቶ ክርስቲያን ታደሰ**

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር የሚመጣው የትኛውም የሠላም አማራጭ ኢትዮጵያን የሚያድን እስከሆነ ድረስ እየጎመዘዘንም ቢሆን መቀበል አለብን ሲሉ አቶ ክርስቲያን ታደለ ገለጹ፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር የሚመጣው የሠላም መፍትሄና የሠላም አማራጭ ከግል ፍላጎትና አቋም አንጻር ላይዋጥልን፣ ሊያመንና ሊጎመዝዘን ይችላል፡፡ ኢትዮጵያን የሚያድን እስከሆነ ድረስ እየጎመዘዘንም ቢሆን መቀበል ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር የምናመጣው የሠላም መፍትሄና የሠላም አማራጭ ከግል ፍላጎትና አቋም አንጻር ላይዋጥልን፣ ሊያመንና ሊጎመዝዘን ይችላል

“የሠላም አማራጩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ዜና

# የአረንጓዴ አሻራ ክንውን ስርዓተ ምህዳሩን ያገናዘበ ሊሆን እንደሚገባ ተጠቆመ

ዳግማዊት ግርማ



አዲስ አበባ፡- የአረንጓዴ አሻራ ክንውኖች ስርዓተምህዳሩን ያገናዘበ ሊሆን እንደሚገባ ተጠቆመ፡፡ በመርሐ ግብሩ ችግኞችን ከመትከል አልፎ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ እንደሚገባም ተጠቅሷል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የላንድስኬፕ ኢኮሎጂ መምህሩ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዴቢሳ ለሜሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አነሳሽነት የተጀመረው "አረንጓዴ አሻራ" ዘመቻ ክንውኖች ስርዓተ ምህዳሩን ያማከሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ሲከወን የትኞቹ ተክሎች ለየትኛው መልክዓ ምድር ሊሆኑ ይችላሉ እንዲሁም የተጎዱና በትንሽ ክትትል ሊጠገኑ የሚችሉ ዕፅዋት ተመርጠውና ተለይተው በተለየ እንክብካቤ ሊተከሉ ይገባቸዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር በተጠና መንገድ ከተሰራ ዘመን ተሻጋሪ ተግባር መሆኑን የገለጹት መምህር ዴቢሳ፤ ችግኝ የሚተከሉባቸውን መሬቶችና የተክሎቹን ባህሪያት ሳያጠኑ መትከሉ ግን ከፍተኛ አደጋ ሊኖረው እንደሚችል አሳስበዋል፡፡

የትኞቹ የዛፍ ዝርያዎች ለየትኛው አይነት መሬት ይስማማሉ እንዲሁም ቅድሚያ ተሰጥቶት የተጎዱ ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው የሚለውን ጥያቄ በጥናት ላይ የተመሰረተ ምላሽ መስጠት እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

እንደ መምህር ዴቢሳ ገለጻ፤ በአረንጓዴ አሻራ ስም ሌሎች በትልልቅ ዛፎች ስር የሚገኙ በዓይን የማይታዩ ስርዓተ ምህዳሩን በተለያዩ መንገዶች የሚጠቅሙ ብዝሀ ህይወት እንዳይጎዱ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም አሳስበዋል፡፡

በተለያዩ ወቅቶች ላይ የሚተከሉ ተክሎችን ከመትከል ባለፈ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይገባል ያሉት መምህር ዴቢሳ፤ ችግኝ ከመትከል ጎን ለጎን የመንከባከብና የመከታተል ሥራም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል፡፡በመርሐ ግብሩ የሚተከሉ ችግኞች በቁጥር ብቻ ሳይሆን በጥራትም ሊመረጡ እንደሚገባቸውም አሳስበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶክተር) ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የተለያዩ አካባቢ ነዋሪዎች ተሳታፊ የሚሆኑበት በአገር አቀፍ ደረጃ ችግኝ የመትከል መርሐ ግብር የአረንጓዴ አሻራ ክንውን ከተጀመረ አራት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በያዝነው ዓመት መርሐ ግብር ላይም ስድስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል እቅድ ተይዟል፡፡

# በቦረና በደረሰው ድርቅ ከ1 ሚሊዮን በላይ እንስሳት ሕይወት ማለፉን ኢንስቲትዩቱ አስታወቀ

ዳግማዊት ግርማ



አዳማ፡- በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በደረሰው ድርቅ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የቁም እንስሳት ህይወታቸው ማለፉን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ቁጥሩ ከአንድ ወር በፊት በአካባቢው ዝናብ መጣል ከመጀመሩ በፊት የተሰበሰበ መረጃ መሆኑንና ከዚያ በኋላ ተጨማሪ የቁም እንስሳት ሕይወት ሊያልፍበት የሚችልበት ዕድል መኖሩ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ትራንስፎርሜሽን አስተባባሪ ዶክተር ሳሙኤል ቱፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በቦረና ዞን በደረሰው ድርቅ ከአንድ ሚሊዮን በላይ እንስሳት ሕይወታቸው አልፏል፤ በድርቁ የተነሳ የቤት እንስሳት አርቢዎቹም ለችግር ተጋልጠዋል። ፡፡

በዞኑ በተከሰተው ድርቅ የተነሳ ኑሯቸውን በእንስሳቱ ላይ ባደረጉ የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ኪሳራ ደርሷል። በተጨማሪ የአካባቢው ኗሪዎች ላይ የተፈጠረው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ከፍተኛ ነው ብለዋል።

የሞቱት እንስሳት ቁጥር ከአንድ ወር በፊት በአካባቢው ዝናብ መጣል ከመጀመሩ በፊት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የተገኘ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ሳሙኤል፤ ዝናብ መጣል ከጀመረ አንስቶም ቢሆን የድርቁ ተጽእኖ በመኖሩ የተነሳ ተጨማሪ የቤት እንስሳት ህይወት ሊያልፍበት የሚችልበት ዕድል መኖሩን ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ሳሙኤል ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ካሏት የቀንድ ከብቶች መካከል በቦረና የሚገኙት የከብቶች ዝርያዎች ለኢንቨስትመንትም በይበልጥ ተመራጭ ናቸው። አሁን ግን በድርቁ ምክንያት እንስሳቱ በመሞታቸውና ሌሎቹም በመጎዳታቸው በአገር ሃብት ላይ እየደረሰ የሚገኘው ጉዳት ከፍተኛ ሆኗል።

ተፈጥሯዊ ሳርን ብቻ ለመኖነት እየተመገቡ የሚያድጉት የቦረና ከብቶች የተለያዩ መኖዎችን ተቀልበው ከሚያገለግሉ በሬዎች በላይ የመደለብ ተፈጥሯዊ ዕድል እንዳላቸው በጥናት መረጋገጡን የጠቆሙት ዶክተር ሳሙኤል ፤ ከብቶቹን በትንሹ በመንከባከብ የበለጠ ምርታማነት ማግኘት እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይም አንድ የቦረና ላም ከተወለደች አራት ዓመት ሳይሆናት የመውለድ ዕድል እንዳላት ገልጸው፤ እነዚህን የመሰሉ ጥቅሞች ያሏቸውን የቦረና ከብቶች በድርቁ የተነሳ መታጣቱ ጉዳቱን የከፋ ያደርግብናል ብለዋል።

በመሆኑም ድርቁ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ሁሉም ህብረተሰብ የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ አድርገው፤ ከዚህ ቀደም እንደተከናወነው ሁሉ የመኖ አቅርቦቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መለሰ ማሪዮ በበኩላቸው በተመሳሳይ እንደገለጹት፤ በዞኑ በተከሰተው ድርቅ የተነሳ ከአንድ ሚሊዮን በላይ እንስሳት ሕይወት ማለፉ በሀገር ሃብት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ አስከትሏል።

ድርቁ በዞኑ የሚገኙትን እንስሳት ሕይወት ከመቀማቱ በተጨማሪ በስፍራው የሚገኙትን የአካባቢውን ማህረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮቹን በመጋፋት ለከፋ ድህነት እንደዳረጋቸውም ዶክተር መለሰ ገልጸዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በደረሰው ድርቅ ሳቢያ ከ14 ሚሊዮን በላይ እንስሳት ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ የቁም እንስሳት ሕይወታቸው ሲያልፍ ከሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ደግሞ በመኖ እጥረት የተነሳ በመዳከማቸው በሰው ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን የኦሮሚያ ክልል አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መግለጹ የሚታወስ ነው፡፡

# ወወክማ የወጣቶችን የስነ-ተዋልዶ ጤናና ዕውቀት የሚያሳድግ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር /ወወክማ/ የወጣቶችን በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ እውቀትና ክህሎት የሚያሳደግ "ሚዲያ ስማርት ዩዝ" የተሰኘ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ።

በኢትዮጵያ የኦንላይ መተግበሪያ ቴክኖሎጂን መሰረት አድርጎ የሚተገበረው ፕሮጀክቱ በትላንትናው እለት ወደሥራ ገብቷል።

የወወክማ ምክትል ዳይሬክተር ወይዘሮ ሔለን ተፈራ እንደገለጹት፤ የፕሮጀክቱ አላማ ወጣቶች በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ነው።

በአይነቱ አዲስ የሆነው ሚዲያ ስማርት ዩዝ የተሰኘው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የሁለት ዓመት የትግበራ ቆይታ ይኖረዋል ያሉት ወይዘሮ ሔለን፣ በአዲስ አበባ ከተማና በአምስት ክልሎች በሚገኙ አስር የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፣ እንዲሁም ከሌሎች አጋር አካል ጋር በመተባበር የተገበራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሔለን ገለጻ፣ ፕሮጀክቱ በጤናና ስነተዋልዶ ዕውቀታቸው የዳበሩ፣ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የሚወጡና በመንፈስ የጠነከሩ ወጣቶችን ለማፍራት እንደሚጠቅም ተስፋ ተጥሎበታል።

ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶችን በስነ-ተዋልዶ መረጃዎች ዙሪያ በተለያየ መንገድ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይረዳል። የማህበራዊ ሚዲያ ምህዳሩን በመጠቀም በጉዳዩ ዙሪያ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራትም ያግዛል ብለዋል።

የወወክማ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ጥላሁን ክፍሌ በበኩላቸው፤ ወጣቶች በስነተዋልዶ ጉዳዮች ላይ የተረጋገጡ መረጃዎችን በየጊዜው ማግኘት አለባቸው። ለዚህ ደግሞ የማህበሩ ፕሮጀክት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ማህበሩ በወጣቶች ላይ በመሥራት ከ70 ዓመታት በላይ መስራቱን ያስታወሱት አቶ ጥላሁን፤የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየተገበረ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ላይ በጋራ እየሠራ የሚገኝ ተቋም ነው፤ በቀጣይም ወጣቶችን መሰረት ያደረጉ ፕሮጀክቶችን ያከናውናል ብለዋል።

ማህበሩ በአገራችን ከተቋቋሙት የወጣትና ማህበረሰብ ተኮር የበጎ አድራጎት ማህበራት መካከል አንዱ መሆኑን ጠቁመው፤ የዓለምና አህጉር አቀፍ ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር አባልም መሆኑን አስታውሰዋል።

በመሆኑም ማህበሩ የዓለምና አህጉር አቀፍ መሠረታዊ መርሆችን የሚጋራና በቀለም ፣ በፆታ፣ በዕምነትና በአመለካከት ልዩነት የማያደርግ የበጎ አድራጎት ተቋም መሆኑን ጠቁመው።

ማንኛውም ስለስነ-ተዋልዶ ዕውቀት ማግኘት የሚፈልግ ሁሉ ሊጠቀምበት የሚገባ ፕሮጀክት መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ክርስቲያናዊ ማህበር ለሚዲያ ስማርት ዩዝ ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፉን ከዲቪድና ሉስሊ ፓካርድ ፋውንዴሽን ማግኘቱንም ገልጿል፡፡

ዜና

# በግብርናው ዘርፍ የታዩ ውጤቶችን ለማጠናከር የበጀት ድጋፍ እንደሚደረግ ሚኒስቴሩ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በግብርናው ዘርፍ የታዩ አበረታች ውጤቶችን ለማጠናከር ተገቢው የበጀት ድጋፍ እንደሚደረግ የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የፌዴራል ባለበጀት መሥሪያቤቶች የበጀት ስሚ መርሐግብር የግብርና ሚኒስቴርና በስሩ የሚገኙ ተጠሪ ተቋማት የ2015 በጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ አቅርበዋል።

የበጀት ስሚ መርሐግብሩን የመሩት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ እንደገለጹት፣ የግብርናውን ዘርፍ ለማጠናከር አቅም በፈቀደ መጠን የበጀት ድጋፍ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

የግብር ዘርፉ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ መንግሥት በልዩ ትኩረት እየሰራበት የሚገኝ ዘርፍ መሆኑን ጠቁመው፤ ዘርፉን በቴክኖሎጂ በግብዓትና በተለያዩ አማራጮች ለማጠናከር አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል ብለዋል።

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ በበኩላቸው፤ በግብርና ዘርፍ ከዚህ ቀደም የሚገባውን ያህል ትኩረት እንዳላገኘ ጠቁመው፤ አሁን ግን ለዘርፉ መንግሥት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ላይ መሆኑን ገልፀዋል።

በግብርናው ዘርፍ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማትና በአትክልት ልማት አሁን ላይ እየተገኙ ተጨባጭ ለውጦችን ይበልጥ ለማጠናከርና ለማስፋፋት መንግሥት ያለውን ውስን ሀብት ጥቅም ላይ ያውላል ብለዋል፡፡

ዶክተር ኢዮብ በተጨማሪም አጠቃላይ የሀብት እጥረት ስላለ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ለይተን መሥራት አለብን ብለው፤ በተለይ በግብርናው ዘርፍ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን ሲሉም ተናግረዋል፡፡



# ‹‹የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ የግጭቶችን ባህሪ የለየ ዘላቂ መፍትሔ ያስፈልጋል››

**አቶ ወንድወሰን ንጉሴ -**
**በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት ተመራማሪ**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ የግጭቶችን ባህሪና ምንነት በመለየት ዘላቂ መፍትሔ ያስፈልጋል ሲሉ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት የአገረ መንግሥት ግንባታ ተመራማሪ አቶ ወንድወሰን ንጉሴ ገለጹ።

አቶ ወንድወሰን ንጉሴ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአገርን ሰላምና አንድነት ለማረጋገጥ የግጭቶችን ባህሪ መለይ ብሎም እንደየባህሪያቸው ዘላቂ መፍትሄን ማበጀት ይጠይቃል።

ግጭት በተለያየ አጋጣሚ ይከሰታል ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ ትልቁ ችግር የግጭት አፈታት ሂደቱ ነው። የግጭት አፈታት ሂደቱንም በኃይል ሳይሆን በመግባባት ላይ የተመሰረተ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚሞከረው ደም አፋሳሽ በሆነ ጦርነት በመሆኑ ከባድ የሆነ ሰብዓዊ፣ ቁሳዊ ውድመት ያስከትላል ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥት የግጭቶችን ምንነት በመለየት እንደየ ችግሮቹ ባህሪያት ለይቶ የጸጥታ ኃይሉንና በየደረጃው ያሉ አካላትን በማስተባበር እልባት መስጠት እንደሚጠበቅበት ጠቁመዋል።

ሕዝቡን በማሳተፍ በአጥፊዎች ላይ ጠንካራ ርምጃ ስለማይወሰድ ሌሎች ግጭት ቀስቃሾች የሚበረታቱበት ሁኔታ እየታየ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ወንድወሰን፤ ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላም በአጥፊዎች ላይ ግልጽና ተጨባጭ እርምጃ ባለመወሰዱ አጥፊዎች አድማሳቸውን ሲያሰፉ ይስተዋላል ብለዋል።

ግጭት ፈጣሪዎች የሚታረሙበትና የተጎዱ የሚካሱበት አሰራር መኖር መቻል አለበት ያሉት ተመራማሪው፤ በቀጣይ አጥፊዎችን ወደ ሕግ በማቅረብ አስተማሪ ርምጃ መውሰድ ይገባል። በአጠቃላይም የሕግ የበላይነትን ማስከበር ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህ ባለፈ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ በቂ ሆነ የተግባቦት ሥራ ሊሰራ እንደሚገባ የጠቆሙት አቶ ወንድወሰን፤ ችግር በፈጠሩ አካላት ላይ ምን አይነት ርምጃ ተወሰደባቸው፣ የግጭቱ መንስኤና ጠንሳሽስ ማን ነበር በሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ የተግባቦት ስርዓት መፍጠር እንደሚገባ ገልጸዋል።

አስፈላጊ ሲሆን በተለይም ፖለቲካዊ መፍትሔ በሚያስፈልጋቸው ችግሮች ላይም የሚመለከታቸውን የፖለቲካ ምሁራንና ፓርቲዎች በማሳተፍ መፍትሔ ማፈላለግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ግጭት እንዲሁ የሚመጣ ሳይሆን ዑደቱን ጠብቆ የሚከሰት በመሆኑ መንግሥት በየደረጃው ያሉ የደህንነትና የፍትህን ተቋማት በማጠናከር ችግሮች ከመከሰታቸው በፊትና ከተከሰቱ በኋላ ደም አፋስሽ ግጭት እንዳይፈጠር መከላከል ይገባል ብለዋል።



እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፤ ግጭት ሲባል በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ በአገራት መካከል የሚደረግ ሊሆን ይችላል። አሁን በኢትዮጵያ ያለው ግጭት በዋናነት ነፍጥ ያነሱ አካላት ብሔርን፣ የሥልጠን ፍላጎትን፣ ሃይማኖትን፣ የአደባባይ በዓላትን መሰረት አድርገው በሚቀሰቅሱት ችግር የተፈጠረ ነው።

በመሆኑም መንግሥት የጸጥታ ስጋቶችን በአግባቡ ለሕዝቡ በማስገንዘብ ችግሮች እንዳይስፋፉ ማረቅ ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አገር ከዚህ በፊት የነበረው ሰላም በአፈና ውስጥ በነበረ ዝምታ የመጣ ነው ያሉት የአገረ መንግሥት ተመራማሪው፤ ሁሉም ፍላጎቶች በኃይል ተገድበው እንዳይወጡ ተደርገው የነበረ ሰላም እንጂ በዴሞክራሲ የሰፈነ ሰላም እንዳልሆነ ማሳያ ነው ብለዋል።

ይህ አይነቱ ሰላም ደግሞ አንድ ቀን አፈናው ሲላላ የሚላላና ዘላቂነት የሌላው እንደነበር ጠቁመዋል።

መንግሥት አፈናን ሳይሆን ዴሞክራሲዊ ሂደትን መከተል ስለመረጠ ታፍነው የነበሩ ሀሳቦች አደባባይ በመውጣታቸው ግጭቶች እንዲከሰቱ አንዱ ምክንያት ሆኗል። ስለዚህም የግጭቶቹን መንስኤ የለየ ጥልቅ ውይይት ማድረግ ዘላቂ መፍትሄ እንዲመጣ ያግዛል ብለዋል።

በአሮሚያ ክልል በአሸባሪነት የተፈረጀው የሸኔ ቡድን በሰላማዊ ዜጎች ላይ ያስከተለው ጥቃት፤ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር እየተደረገ ያለው ጦርነት፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ካማሺና መተከል ያሉ ግጭቶች እንደአብነት አንስተው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የችግሩን መንስኤ፣ የየአካባቢውን መፍትሄ መፈለግ፣ ሕዝቡን ያሳተፈ ውይይት ማድረግና ተመሳሳይ እርምጃዎች ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ወሳኝ መሆናቸውን ገልጸዋል።

# ‹‹የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራን አሰባስቦ በመምራት በውሃ ጉዳይ የበለጠ ውጤት ለማስገኘት ይሰራል››

**- ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ**
**የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር**

**ዘላለም ግዛው**

ቢሾፍቱ፡- በተበታተነ መልኩ በአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እየተተገበረ የሚገኘውን የውሃ ዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራን አሰባስቦ በመምራት በውሃ ጉዳይ የሚደረገውን ትግል በማጠናከር የበለጠ ውጤት ለማስገኘት እንደሚሰራ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ገለጹ፡፡

በቢሾፍቱ ከተማ ትናንት በተካሄደው ‹‹የውሃ፣ የውሃ ዲፕሎማሲና ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች መማክርት›› ፎረም መርሐ ግብር ላይ የተገኙት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ እንደገለጹት፤ የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራን አሰባስቦ በመምራት በውሃ ጉዳይ በሚደረገው ትግል የበለጠ ድል እንዲገኝ ይሰራል፡፡

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን እውነትና በተፈጥሮ ሃብት አልምቶ የመጠቀም መብትን ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለማሳወቅ በተበታተነ መንገድ የሚደረገውን የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራን አሰባስቦ በመምራት የተገኘውን ውጤት አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ብለዋል ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አገር ወዳድ ዜጎች ባደረጉት ትግል ውጤት ተመዝግቧል፣ ይህንን በውጤታማነት እንዲመራ ለማድረግ ተበታትኖ ያለውን የሰው ኃይል በማሰባሰብ ለበለጠ ድል ይሰራል፣ ትግበራው የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅም ያስችላል።

በተለያዩ ቋንቋዎች የአገርን እውነት በሕግ፣ በእውቀት፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ ተደግፎ እንዲሰራ፣ በተለይ በቀጣይ ከሚተገበረው 3ኛው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ውሃ ሙሌት ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያን ስም ለማጠልሸት የሚሰሩ ኃይሎችን ለመታገል እንደሚያግዝም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያን ለመጉዳት የሚያስቡ ኃይሎች ሉዓላዊነትን በሚጎዳና የሕዝብን ስምና ክብር በሚጋፋ መልኩ ዘመቻ እንደሚያካሂዱና የተለያዩ ተጽእኖዎች እንደሚያደርጉ ጠቁመው፤ ሂደቱ ተገቢ እንዳልሆነም ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሃብታችንን አልምቶ የመጠቀም መብት አለን፤ የአባይ ግድብ ግንባታ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነውም ብለዋል፡፡

አደረጃጀቱን መፍጠር ያስፈለገው የተለያየ ዘርፍ የሚገኙ ባለሙያዎች በየችሎታቸው ድምጽ እንዲሆኑ ለማስቻል መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በተለያዩ ቋንቋዎች የኢትዮጵያን እውነት መናገር ትልቅ ትርጉም አለው ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በተለያዩ እውቀቶች በመታገዝ፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ በመደገፍ እንዲመራ ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ወክለው የተገኙት



አቶ ኃይለሚካኤል ዴቢሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሚደረገው ጫና ውጤቱ በአገርና በሕዝብ ላይ ውጤት ያለው መሆኑን በመገንዘብ የአባይ ጉዳይን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ማድረግ ይገባል፣ ሁሉም በየዘርፉ በባለቤትነት ስሜት መታገል ይገባዋልም ብለዋል፡፡

ጋዜጠኞች ሲዘግቡ የቀጠናውን ጂኦ ፖለቲካና የአባይን የውሃ ሁኔታ መረጃ ባግባቡ ተገንዝበው ሌላውን ማሕበረሰብ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ግብጻውያን በዲጂታል ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ጫና ያደርጋሉ፣ የቲዩተር ተጠቃሚዎች አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ናቸው፤ ይህንን የሚመጥን ሥራ ለመስራት የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ቴክኖሎጂ በማበልጸግ ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል፡፡

ስለመማክርት ፎረሙ ሰነድ ያቀረቡት የውሃ ባለሙያ ዶክተር አዳነች ያሬድ በበኩላቸው፤ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርን በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች፣ በውሃ ሃብት አስተዳደር ጉዳይና በተለያዩ በውሃ መሰረተ ልማቶች ወይም ፕሮጀክቶች ላይ ማማከርና ኢትዮጵያ በውሃ ሃብቷ ለማልማትና ለመጠቀም በምታደርገው ጥረት ውስጥ የምሁራን ምክረ ሃሳብ ለማግኘት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከአላማዎች መካከል እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡

በዘርፉ የሚደረጉ ምርምሮችና አዳዲስ እውቀቶችን ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ፣ ሚዲያውንና የዘርፉን ባለሙያዎች በማቀራረብ የኢትዮጵያን እውነታ ለቀጠናውና ለዓለም ማህበረሰብ ማሳወቅና በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በዓለም ያለውን የተዛባ አስተሳሰብና አመለካከት ለማስተካከል እንደሚያግዝም ጠቅሰዋል፡፡

ለፖሊሲና መመሪያ ግብአት የሚሆኑ ሃሳቦችን ለማግኘት፣ በታችኞቹ ሃገራት ያለውን የውሃ መጠን በጥናት ላይ ተመርኩዞ እውነታውን ለመናገር ጉልህ ሚና ከአላማዎቹ መካከል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

# የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት እንደሚያደርግ ሚኒስቴሩ ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የተቋሙን የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት እንደሚያደርግ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ከክልልና ከተማ አስተዳደር የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አስተባባሪዎች እና የቢሮ ኃላፊዎች ጋር በአዳማ ከተማ ያካሄደውን መድረክ ትናንትና አጠናቋል።

ለመጀመሪያው ዙር ከሰባት ክልሎች ተወክለው የመጡት የጣቢያዎቹ አስተባባሪ እና ኃላፊዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት ጣቢያዎቹ ላይ የሚደርስ ጉዳት፣ የቁሳቁስ አለመሟላት፣ የስልጠናዎች አለመመቻቸት፣ የሠራተኞች ፍልሰት፣ ለዘርፉ የሚሰጠው ትኩረት ማነስ እና የመሳሰሉትን እንደችግር አንስተዋል።

ውይይቱን የመሩት በሥራ እና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን መድረኩ ለሥራ ፈላጊው ወጣት ሥራ ለመፍጠር የሚሰሩት ጣቢያዎች ያሉባቸውን ችግሮች ለመረዳት ሰፊ ዕድል ሰጥቷል ብለዋል።


አቶ ንጉሱ ጥላሁን እና ነቢሃ መሀመድ

ይህንንም ለመፍታት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በጣቢያዎቹ መካከል ካሉት የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አደረጃጀቶች ጋር ተመካክሮ የመፍትሔ አቅጣጫ የማስቀመጥ ድርሻውን ሚኒስቴሩ እንደሚወጣ ተናግረዋል።

በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር አማካሪ ሚኒስትር ዴኤታ ነቢሃ መሀመድ በበኩላቸው የአንድ ማዕከላት ጣቢያ አስተባባሪዎቹ ወጣቱን ከሥራ ጋር የሚያገናኙ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

አስተባባሪዎቹ የወጣቱ ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ችግሮቹ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ለመፍትሄዎቹም ጠንክረው እንዲሰሩ አሳስበዋል።

ለሁለት ቀናት የተካሄደው የመጀመሪያው መድረክ ትናንትና ሲጠናቀቅ የሌሎቹን ክልል እና ከተማ አስተዳደር የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አስተባባሪና ኃላፊዎችን በማሳተፍ በቀጣይ የሚሄድ መሆኑ ተገልጿል።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ከሁለት ሺህ አንድ መቶ በላይ ለሚሆኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰጪ ሙያተኞችና አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና እያከናወነ ይገኛል።

## “የሠላም አማራጩ ...

ከገፅ 1 የዞረ

ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ የሚጎመዝዝ እንኳን ቢሆን ኢትዮጵያን የሚያድንና ህዝቡን ወደ ፊት የሚያሻግር እስከሆነ ድረስ እየጎመዘዘንም ቢሆን መቀበል ያለብን እውነት ሊኖር እንደሚችል ከወዲሁ መረዳት ይኖርብናል ሲሉ ተናግረዋል::

አቶ ክርስቲያን፤ “ኢትዮጵያውያን ሠላም እንፈልጋለን:: የሠላም እጦት መላውን ኢትዮጵያዊ አንገሽግሾታል:: በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ጽንፍ በሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ የማህበረሰብ ክፍል እየተማረረ ነው:: ይህ ጉዳይ አሁን ላይ በቃ ካልተባለ መቼም ሊያበቃ አይችልም” ነው ያሉት::

ከዚህ አንጻር በየትኛውም ደረጃ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች በእነርሱ እምነት ኢትዮጵያን ወደ ፊት ያሻግራሉ ብለው የሚያምኑበትን የሠላም አቅድና አማራጭ ይዘው ቢቀርቡ ሊታይ የሚችልበት እድል እንዳለም ጠቁመዋል:: ሁሉም የሰላም አቅድ እንዲያመጣም ጥሪ አቅርበዋል::

በየትኛውም ሁኔታ ሠላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ ከትግራይ ህዝብ ጋር ተያይዞ በገለጹት ሀሳባቸው፤ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ኢትዮጵያ እንደ አገር እዚህ እንድትደርስ ጉልህ አበርክቶ ያለው ህዝብ መሆኑን አንስተዋል::፡ ይህ ጉልህ አበርክቶአቸውን እንዲቀጥል፤ ኢትዮጵያን ወደፊት ለማሻገር በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባ እና ምቹ ሁኔታዎቹ ምን መምሰል አለባቸው ? አፈጻጸማቸው እንዴት ነው? የሚሆነው የሚለው ቀጣይነት ያላቸው ንግግሮችና ምክክሮችን እንደሚፈለግ ገልጸዋል::

“የምክር ቤት አባል ስሆን የትግራይ ህዝብ ሁኔታም ይገደኛል:: የትግራይንም ህዝብ ወክዬ ነው እዚህ ያለሁት:: እዚህ ስሆን ለመላው ኢትዮጵውያን እንደራሴ ነኝ:: ትግራይም ሠላም እንድታገኝ እፈልጋለሁ:: የሽብር ቡድኑ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የተጎዱ አካባቢዎች በተለይ አፋርና አማራ አካባቢዎች እንዲሁም መላው ኢትዮጵያ ሠላም እንድታገኝ እፈልጋለሁ:: ያ ሠላም እንዴት መምጣት አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ እንደ ምክር ቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ዜጋም ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት መወያየትና መመካከር ይኖርብናል” ሲሉ ተናግረዋል::

የትግራይ ህዝብ ህመም የሁላችንም ህመም መሆን ካልቻለ ኢትዮጵያን እንወዳለን ማለት አንችልም ያሉት አቶ ክርስቲያን ፤ይህን ጉዳይ ሁሉም ማህበረሰብና ፖለቲከኞች ሊረዱት ይገባል ብለዋል ::

አቶ ክርስቲያን፤ እንደ ህዝብ ተወካይ ምክር ቤት አባልነት ሳይሆን “የግል እምነቴ ነው” ብለው ባነሱት ሀሳብ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው ብለዋል:: ኢትዮጵያን አልፈልግም የሚልን አካል ኢትዮጵያን ወደ ፊት እንዴት እናሻግራት በሚል ድርድርና ምክክር ወይም ውይይት ውስጥ ይካተት የሚል አቋም የለኝም ነው ያሉት:: ምክንያቱም ጉዳዩ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ ነው ሲሉም የገለጹት::

በተለይም አሸባሪው ህወሓት በግልጽ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ድረስ እገባለሁ የሚሉ አመራሮች ያሉበት እንደመሆኑ፤ “ መርዝ ቀማሚዎችን ባለ መድኃኒት አድርጎ መቀበል ስህተት ውስጥ እንዳይከተን ጥንቃቄ ማድረግ መቻል አለብን” ብለዋል::

## ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ...

ከገፅ 1 የዞረ

ለመማር፣ ለመስራት፣ ለማስተዳደር፣ በርካታ መረጃዎችን ሊያገኙ የሚችሉበት ቦታ እንደሆነም አክለው ገልጸዋል::

ቤተ መጻሕፍት የሰው ልጅ እውቀት የሚሸመትበት ቦታ በመሆኑ፤ ስላለፈው የሚታወቅበት፣ አዕምሮ የሚነቃቃበት፣ አስተሳሰብ የሚቀረጽበት ምናብን የሚያስተካክልና መልካም ተጽእኖን ወደ ሕይወት ለማምጣት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለውም ተናግረዋል:: መረጃ ዋና ቦታን በያዘበት ዘመን ቤተ መጻሕፍት ልጆች፣ ወጣቶችና አዋቂዎች አስፈላጊውን ክህሎት የሚያገኙበት ቦታ ነው ሲሉም ነው የገለጹት::

“መጻሕፍት ለመግዛትና ብዙ ለማንበብ እድሉን ባላገኝ፤ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ባላሳልፍ ኖሮ ዛሬ የሆንኩትን ሰው መሆን የምችል አይመስለኝም ነበር” በማለትም መጻሕፍትን ማንበብ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ከራሳቸው የሕይወት ተሞክሮ አካፍለዋል::

ፕሬዚዳንቷ፤ የቤተ መጻሕፍት መግለጫ ይህ ብቻ እንዳልሆነ ገልጸው፤ ሰዎች የሚገናኙበት፣ የሚነጋገሩበት፣ ጸጥታ ያለበትን ሥፍራ የሚያገኙበት ቦታ መሆኑና መገለጫው እንደሆነም አንስተዋል:: ቤተ መጻሕፍት የሚከፈተው በርካታ ሰዎች መጻሕፍት የመግዛት አቅም የላቸውም ከሚል አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን፤ በትምህርት ዘልቆ ለመሄድ፣ አዕምሯቸውንና የእውቀት ፍላጎታቸውን በጽኑ የሚያዳብሩበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተብሎ እንደሆነም አስገንዝበዋል::

ከዚህ አንጻር የአብርሖት ቤተ መጻሕፍት ከዲዛይኑ አንስቶ፤ የሚስብና አመቺ ቦታ ነው፤ ከንባብ ባህል ጋር በተገናኘ ትውልዱን ለመለወጥ ትልቅ ሚና እንዳለውም ጠቅሰዋል:: እስካሁንም ለበርካቶች መልካም አገልግሎት እየሰጠ እንዳለ ተናግረዋል:: በተለያዩ ዘርፎች የተጻፉ መጻሕፍትን በማሰባሰብ ሰፊውን ኅብረተሰብ መርዳት ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ገልጸዋል:: መጻሕፍትን መለገስ ትልቅ ስጦታ እንደሆነ የጠቀሱት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፤ ሁሉም ዜጎች በቤታቸው ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል::

በመርሐ ግብሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና በመጻሕፍት ማሰባሰብ ሂደቱ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ጨምሮ እስካሁን ተሳትፎ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል::

በመጀመሪያው ቀን ብቻ የእቅዱን 20 በመቶ ማሳካት እንደተቻለ የገለጹት ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማህበራዊ ጉዳዮች አማካሪና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ናቸው::

"ሚሊየን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" በሚል መሪ ሀሳብ ለአብርሖት ቤተ መጻሕፍት በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊየን መጻሕፍትን የማሰባሰብ መርሐ ግብር ፕሬዚዳንት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ በትላንትናው ዕለት መጻሕፍትን በመለገስ ያስጀመሩ ሲሆን፤ በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከ170ሺ በላይ፣ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ከአምስት ሺህ በላይ መጻሕፍትን ለግሰዋል:: ዘመቻው እስከ ግንቦት 29 ቀን 2014ዓ.ም እንደሚቀየም ተነግሯል::

የአብርሖት ቤተ መጻሕፍት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ ም ተመርቆ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ይታወሳል::

## የአጎዋ ውሳኔ ተፅዕኖ...

ከገፅ 1 የዞረ

አሜሪካ ለኢትዮጵያ ከቀረጥ ነፃ ዕድል መንፈጓን ተከትሎ በወቅቱ ወደ አሜሪካ ምርታቸውን ይልኩ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ገቢያቸው ተጎድቶ እንደነበር ያነሱት ሚኒስትሩ፤ መንግሥት ይህን ችግር ለመፍታት ሁኔታዎቹን ግምት ውስጥ ያስገባ አማራጭ መከተሉ ውጤታማ እንዳደረገው ገልፀዋል፡፡

ቀደም ሲል በአጎዋ ከቀረጥ ነፃ ሥርዓት ሀገሪቷ ተጠቃሚ የሆነችባቸው የጨርቃጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፎች እንደሆኑ የጠቆሙት አቶ መላኩ፤ ምርቶቹን ወደአሜሪካ ከቀረጥ ነጻ ማስገባት እንደማይቻል ሲታወቅ በሌሎች ዘርፎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አቅጣጫ መቀመጡን አስታውሰዋል።

በዚህም በዓለም ላይ በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት የጨመረውን የምግብ ፍላጎት መናር መሰረት በማድረግ የምግብና መጠጥ ኤክስፖርት ኢንዱስትሪው ላይ ኢትዮጵያ የነበራት ድርሻ ከፍ እንዲል ተደርጓል፤ በዚህም ውጤት ተገኝቷል ብለዋል፡፡

ሀገሪቱ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ዕሴት የተጨመረባቸውን የምግብና የመጠጥ ውጤቶችን ወደ ገበያ አቅርባለች። ዕድሉን በመጠቀሟም የውጭ ምንዛሪ ገቢዋን ማሳደግ ችላለች ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይ ሥጋና ወተት የመሳሰሉ ምርቶችን መጠናቸውን በመጨመር በብዛት ወደውጭ አገራት ለመላክ ጥረት መደረጉን አንስተዋል።

የምግብና መጠጥ ኤክስፖርት መጠን ከመጨመር ጎን ለጎን አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋት ሥራዎች እንደተሠሩ የገለፁት ሚኒስትሩ፤ በአውሮፓ፣ በኤስያና በአረብ ሀገራት እንዲሁም በሌሎች ቦታዎችም ጭምር አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን እያቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የገበያ መዳረሻዎችን ከማስፋት ባለፈ የአሜሪካ ገበያንም በተለያዩ ስልቶች መጠቀም በመቻሉ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የአምራች ዘርፉ ወጪ ንግድ እንዲጨምር ዕድል ፈጥሯል ብለዋል።

በዚህም በአሜሪካ የተሻለ ገበያና ተቀባይ የነበራቸውን አምራቾች በመለየት መንግሥት፣ አምራች ኢንዱስትሪዎችና ተቀባዮቻቸው ወጪቸውን እንዲጋሯቸው ጭምር ተደርጎ ምርቶቻቸውን ማቅረብ እንዲቀጥሉ መደረጉን አስታውቀዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በ2014 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት ብቻ 390 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ አስገኝቷል። ይህም በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት ከተገኘው ጋር የሚስተካከል ነው። የመጪዎቹን ሦስት ወራት ገቢ ሲጨመር ደግሞ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከተሠራው ሁሉ ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሪ እንደሚገኝ ይጠበቃልም ብለዋል፡፡

ገቢውን በተሻለ መልኩ ለማሳደግ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን የመሳብና ወደ ሥራ የማስገባት ዕቅድ መያዙን ጠቁመው፤ በተለይም በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገቡ ባለሀብቶችን ቁጥር ማሳደግ ላይ ትኩረት እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡

የጨርቃጨርቅ፣ የብረታብረትና የኬሚካል እንዲሁም የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ላይም ክትትል በማድረግ ቀደም ሲል ግንባታ ጀምረው ያላጠናቀቁት እንዲያጠናቅቁ፤ አጠናቀው ወደ ማምረት ያልገቡት ደግሞ ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል ብለዋል፡፡

አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ከመሳብና የነበሩትን ከማጠናከር አኳያ ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚፈልገው አኳያ ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



‹‹በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃምሳ የሚደርሱ የሲቪል ማህበራት በረቂቅ አዋጆች ለማወያየት እድል አግኝተዋል››

- አቶ ሄኖክ መለሰ
የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 6



የቡናው ዘርፍ ደጀን- ለአራት አስርት ዓመታት የዘለቀ ሙያ

ገጽ 13



ዘጠኝ ነፍስ በጎዳና

ገጽ 16

## ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# አቅዶ መሥራት ያስገኘው ወርቃማ ውጤት

ታክስ ለአንድ አገር ህልውናና የአንድ መንግሥት ጥንካሬ መለኪያ መሆኑ ይገለፃል። ከዚህ አንጻር ጠንካራ ስርዓተ መንግሥት ያላቸው አገሮች ጠንካራ የታክስ አስተዳደር ስርዓት አላቸው። ምክንያቱም መንግሥት ለህዝቡ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችና መሰረተ ልማቶችን ለማቅረብ በቂና አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል። ይህ ገንዘብ ደግሞ የሚገኘው ከታክስ ከሚሰበሰብ ገቢ ነው። ለዚህም ነው የአንድ አገር አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ከታክስ የሚሰበሰበው ገቢ ነው የሚባለው።

ነገር ግን ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ የሚገኙ አብዛኛው አገሮች ወጪያቸውን መሸፈን የሚያስችል ገቢ ከግብር (ታክስ) ስለማይሰበስቡ ያላቸው አማራጭ ብድር እና እርዳታ ተጠቅመው ወጪያአቸውን መሸፈን ነው። ብድር እና እርዳታ ደግሞ በአበዳሪዎችና እርዳታ ሰጪዎች መልካም ፍቃድ የሚሰጡ በመሆናቸው አስተማማኝ የገቢ ምንጮች አይደሉም። ከዚህም ባለፈ በአገሮች የፖሊሲ ነፃነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድርና ለትውልድ የሚተርፍ የወለድ ዕዳ ስለሚዳርግ የሚመከሩ አይደለም።

ይህንን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ብቃት ያለውና አገልጋይነትን የተላበሰ የሰው ኃይል በመገንባት፣ ፍትሐዊና ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ዕውን አድርጎ ተደራሽ አገልግሎት በመስጠትና ግብርን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ለከተማዋ ዕድገትና ብልጽግና የሚያስፈልጋትን ገቢ በብቃት መሰብሰብ የሚያስችል ተልዕኮ በማንገብ ተግቶ እየሠራ ይገኛል። ቢሮው ካነገበው ተልዕኮ አኳያ የዘጠኝ ወራት የእቅድ አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል እንዲሁም በመልካም ሥነ ምግባር መገንቢያ የንቅናቄ መድረኮች ሂደትና ውጤት ዙሪያ በየደረጃው የሚገኙ የተቋሙ አመራሮች ውይይት አካሂደዋል።

በመድረኩ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ በሰጡት መግለጫ፤ ቢሮው በበጀት ዓመቱ 48 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር፣ በዘጠኝ ወራት ደግሞ 37 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ እቅድ ይዞ ወደ ሥራ ገብቷል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት 43 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፤ አፈፃፀሙም ከእቅዱ አንጻር 115 በመቶ ነው። ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ ከ10 ቢሊዮን ብር በላይ ጭማሪ አለው፡፡




ቢሮው ይህንን ውጤት ማስመዝገብ የቻለው የተቋም አቅም ግንባታ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ፣ የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ የሚረዱ የማስተማርና የህግ ማስከበር እንዲሁም ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከርና የላቀ ገቢ መሰብሰብ በሚል የትኩረት መስኮች ለይቶ በመንቀሳቀሱ ነው ብለዋል፡፡

የታክስ ህግ ተገዢነትን ለማረጋገጥ በተከናወኑ ተግባራትም መንግሥት ሊያጣው የነበረን ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ማዳን መቻሉን ኃላፊው ገልጸው፤ የስነ-ምግባር ጥሰት በፈፀሙ ከ200 በላይ ሠራተኞች ላይ ከቀላል እስከ ሥራ ስንብት የደረሰ እርምጃ መወሰዱንና ህግን አክብረው ሲሰሩ ለነበሩና ለተሰበሰበው 100++ (ከዕቅድ በላይ) የገቢ አፈጻጸም የላቀ አስተዋጽኦ ለነበራቸው 299 ግብር ከፋዮች እውቅና መሰጠቱን ተናግረዋል፡፡

ቢሮው ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን ለማሳለጥ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ለአብነትም "ኢቲ" ታክስ የተሰኘ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በማልማት 298 ሺህ ለሚሆኑ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የተሳለጠ አገልግሎት መስጠቱንና በቀጣይም ለደረጃ "ሀ" እና "ለ" ታክስ ከፋዮች በዚህ ቴክኖሎጂ አማካይነት አገልግሎት ለመስጠት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

"ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሁሉም ዘርፍ የተመዘገበውን አበረታች ውጤት ቀጣይነት በማረጋገጥ በዓመቱ መጨረሻ እንደቢሮ የተቀመጠው 100++ የገቢ አፈጻጸም ማሳካት ይገባል" ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ከዕቅድ ግምገማው በመነሳት ያላሳካናቸውንና ልናሳካቸው የሚገቡ ተግባራትን በመለየት የቀጣይ ሦስት ወራት ዕቅድ አዘጋጅቶ በትኩረት መሥራት፣ ብልሹ አሠራሮችን ማረም፣ የተጀመረውን የቤት ለቤት ጉብኝት አጠናክሮ ማስቀጠል፣ ከታክስ ከፋዩ ጋር ያለው ጤናማ ግንኙነት ማጠናከር፣ በተቀመጠው ህግና ስርዓት መሰረት ለግብር ከፋዮችና ደንበኞች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት፣ በየመድረኩ በግብር ከፋዮች የሚነሱ አስተያየቶችን በመለየት ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ ሥራዎችን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መገምገም፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን ማጠናከር፣ አመራሩና ሠራተኛው የሥራ ሰዓት አክብረው እንዲሠሩ ማድረግና ያልተካሄዱና በተለያዩ ምክንያቶች የተንጠባጠቡ የመልካም ስነ ምግባር መገንቢያ የንቅናቄ መድረኮችን ማጠናቀቅ በቀጣይ ትኩረት በመስጠት ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በመድረኩ የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም በቢሮው ዕቅድ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር በአቶ ጥላሁን ግርማ፣ የመልካም ስነ ምግባር መገንቢያ የንቅናቄ መድረኮችን ሂደትና ውጤት በሚመለከት በቢሮው የስነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክተር በአቶ ቀናው ታከለ የቀረቡ ሲሆን፤ ከመድረኩ ለተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች በቢሮው ኃላፊና በዘርፍ አመራሮች ምላሽ ተሰጥቷል ።

## አድራሻ፡-

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608
የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000

የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃምሳ የሚደርሱ የሲቪል ማህበራት በረቂቅ አዋጆች ለማወያየት እድል አግኝተዋል››

- አቶ ሄኖክ መለሰ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ ጃንሜዳ አካባቢ ነው ተወልደው ያደጉት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ህብረት ፍሬ እና ሥላሴ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት ተምረዋል። ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ገብተው በጂዮግራፊ መምህርነት ሰልጥነው ዲፕሎማቸውን አግኝተዋል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጂዮግራፊና አካባቢ ጥናት የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በማህበረሰብ ጥናት መስክ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። በአምቦ ዩኒቨርሲቲና ሲአርዲ ትብብር የሚሰጥ የትምህርት እድል አግኝተውም በዴቨሎፕመንት ማኔጅመንት ተጨማሪ የማስተርስ ዲግሪ መስራት ችለዋል። እንዲሁም ማህበረሰብ ተኮር የሆኑ በርካታ ሥልጠናዎችን በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ወስደዋል።

ስም በተባለ የመንግስት ትምህርት ቤት ለአንድ ዓመት በመምህርነት ያገለገሉት እንግዳችን ጥናት ላይ በሚሰሩ የግልና መንግስታዊ ተቋማት ጋር በመተባበር የዳሰሳ ጥናቶችን ሰርተዋል። ከአንድ ወዳጃቸው ጋር በመሆኑም አማካሪ ድርጅት ከፍተው ህብረተሰቡን አገልግለዋል። በመቀጠልም ሲቪል ማህረሰብ ድርጅት ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመምጣት በተለይም ኤች አይቪ ኤድስ በአገሪቱ አስከፊ በሆነበት ወቅት የተለያዩ ትምህርቶችን ለህብረተሰቡ በመስጠት እንዲሁም ወጣቶች በማሰልጠን የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ይህም አጋጣሚ ደግሞ ፕሮጀክቶችን የማስተባበር እድል ፈጠረላቸው። ከዚህ ባሻገር በወቅቱ የስቀቁትን ሥራ አስኪያጅ በመተካት በተጠባባቂነት እንዲሁም በዳይሬክተርነት ድርጅቱን ለስምንት ዓመት መሩ። በመቀጠልም ኤድስ ሄልዝ ኬር ፋውንዴሽን በተባለና የአሜሪካ መሰረት ባለው ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሰርተዋል። በአፍሪካ ህብረት ትምህርት ዘርፍ በአማካሪነት ለአምስት ዓመት አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤትን በሥራ አስኪያጅነት እየመሩ ይገኛሉ። በምክር ቤቱ ሥራና በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ መለሰ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።


ፎቶ፡-አዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ ስለምክር ቤቱ ዋነኛ ሥራ ምንነት ያስረዱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ይሄ ምክር ቤት እንደሚታወቀው በአዋጅ የተቋቋመው ከአንድ ዓመት በፊት ነው። የለውጡ መንግስት ከመጣ በኋላ በሪፎርም ከተመሰረቱ ተቋማት መካከል ነው። ይህንንም ተከትሎ አዋጅ እንዲከለስ ተደርጓል። ቀድሞ የነበረው 621 የሚባለው የሲቪል ማህበረሰቦች አዋጅ በ1113 ተተክቶ የተከለሰ ሲሆን ይሄ ምክር ቤት እንዲቋቋም በአዋጁ ላይ በግለፅ ተቀምጧል። በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የመወከልና የማስተባበር ሃላፊነት አለበት። ይህም ሲባል በፌደራል ደረጃ የተመዘገቡ ከ3ሺ700 በላይ የሲቪክ ድርጅቶን፤ የመምህራን ማህበር፤ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞችና የሙያ ማህበራት ፌዴሬሽን፤ አገር በቀል የእርዳታ ድርጅቶችንና የመሳሰሉትን በሙሉ የሚካተቱበት ምክር ቤት ነው። ከዚህም በሻገር በክልል ደረጃ ለተቋቋሙ ድርጅቶችም እንዲሳተፉ እድሉ ተፈጥሮላቸዋል።

በተጨማሪም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የመደገፍ ሚናም አለው። በተለይም ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን እንዲያስፍኑና ራሳቸውን እንዲከታተሉ የማድረግ ሃላፊነት ተሰጥቶናል። በሌላ በኩልም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣንን የማማከር ሥራ ይሰራል። እንዲሁም ምክር ቤቱ እውቀትን የማደራጀት፣ የማሰራጨት፣ ለፖሊሲ ግብዓት እንዲሆኑ መረጃዎችን ቶሎ ቶሎ በአገሪቷ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በማየት የዳሰሳ ጥናት በመስራት ጠቃሚ በሆነ የልማት አቅጣጫ ጋር የማስተሳሰር ሥራ ይሰራል። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምክር ቤት በመሆኑ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ የሆነ ገለልተኛ ተቋም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በምክር ቤቱ አባል የሆኑ የሲቪክ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር ሚናቸውን ምን ያህል ተወጥተዋል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንደሚታወቀው የአገራችን የሲቪል ማህበራት ሚና እጅግ የጎላ ነው። ዓይነታቸውም ብዙ ነው። ጤና፣ ግብርና፣ ትምህርት፣ ዲሞክራሲ፣ ሰብዓዊ ድጋፍና የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ አሉ። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ በኢትዮጵያ ልማት ላይ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል ማለት ይቻላል። ጉዞው ግን ቀላል አይደለም። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በማደግ ላይ ያሉ አገሮች በተለይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከፍተኛ የሆነ ፈተና ነው ያለባቸው። ከሚጠበቅባቸው አንፃር ለመስራት እንዳይችሉ እንደአገር ዘርፉ ብዙ ችግሮች ነበሩባቸው። ለዚህ ደግሞ ምቹ ሁኔታ ያለመፈጠሩ በምክንያትነት የሚጠቀስ ነው። በተለይም ቀደም ብሎ የነበረው የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ ለአስር ዓመት ነው የቆየ ከመሆኑም በላይ እጅግ ገዳቢ ነበር። በዚህ ምክንያት አንዳንድ መብት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ምቹ ሁኔታ ስላልነበር እንዲጠፉ ሆኗል። እንኳን አዲስ ማህበራት ሊቋቋሙ ቀርተው የነበሩትም እየተዘጉ፤ እየተዳከሙ እንዲሄዱ ተደርጓል። ይህም በጣም ዘርፉን ጎድቶታል።

ምቹ ምህዳርና የሚያሰራ ህግ በሌለበት ሁኔታ ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን ሚና አሳክተዋል ለማለት አያስደፍርም። ይሁንና በዚያም ውስጥ ሆነው በተለይ በጤናው፤ በትምህርትና በግብርና ዘርፍ የሚሰሩ ድርጅቶች የማይናቅ አስተፅኦ ነው ያበረከቱት። ህግ እንዲወጣ ከማድረግ ጀምሮ የተለያየ ፕሮግራም እንዲተገበሩና ለልማት ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይቷል። ነገር ግን ከሌሎች አገሮች አንፃር ወደኋላ እንደቀረን ይሰማኛል። በቁጥርም ቢሆን በጣም ትንሽ ናቸው። አሁን ላይ ያሉን ማህበራት አራት ሺ አይሞሉም፤ ሌላ አገራት ላይ ግን ከመቶ ሺ በላይ ማህበራት አሏቸው። በህንድን ለምሳሌ ብንወስድ ሶስት ሚሊዮን የሚደርሱ የማህበረሰብ ድርጅቶች ናቸው ያሉት። እናም ይሄ ዘርፍ ገና ብዙ መልማት አለበት ብዬ ነው የማስበው።

ከዚህ ባለፈ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚናቸውን እንዲወጡና በደንብ ግንዛቤ እንዲወሰድና ትክክለኛ ቁልፍ የሆነ የልማት አጋር ናቸው ብሎ እንዲታሰብ እንፈልጋለን። በአሁኑ ጊዜ ያንን ለማምጣት እየሰራን ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የራሳቸው ምክር ቤት እንዲቋቋም ተደርጓል፤ ሆኖም የሚጠበቀውን ያህል የድርጅቶቹን አቅም ለማሳግ ብዙ መስራት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ የሚሰሩ ተቋማት የሕዝብን የልብ ትርታ አዳምጦ እምባን የሚያብስ ሥራ መስራት ላይ ሰፊ ክፍተት እንዳለባቸው ይነሳል። ከዚህ አንፃር እንዳይሰሩ የነበረባቸው ተግዳሮት ምን ነበር?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ትክክል ነው! ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በዋነኝነት ሊሰሩት የሚገባው ይህንን ነው። የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ህዝቡ ላይ የሚደርሰውን በደል በመከታተል አሰራሮች እንዲሻሻሉ ተፅዕኖ የመፍጠር ሚና አላቸው። አስቀድሜ እንደገለፅኩት ለአስር ዓመት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንዲህ አይነት ስራዎችን እንዳይሰሩ ተገድበው ነው የኖሩት። አገር በቀል ድርጅቶች ብቻ በተለይ በገንዘብም ተወስነው እንዲሰሩ መደረጉ እነዚህ ድርጅቶች ሃላፊነታቸውን በሚገባ እንዳይወጡ አድርጓል። በነገራችን ላይ ምቹ ምህዳር አለመኖሩ ዘርፉን ጭምር ጎድቶታል። አሁን በተሻሻለው አዋጅ እንዲሰሩ ቢፈቀድም አቅማቸውን መገንባትም አልቻሉም። ወደዚያ እንዲመጡ፤ ባለው አቅምም እንዲያጎለብቱ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ያለው።

ሁልጊዜ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የወደፊቱን ታሳቢ ያላደረገ ከሆነ በአገር እና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያመጣ እንደሚችል ይሄ ማሳያ ነው። አሁን ላይ እየከፈልን ያለነውም ዋጋም ከዚያ ጋር ተያይዞ ያለ ነው። ሰዎች በድርጅቶች መብት ላይ፤ በዲሞክራሲ ላይ እንዳይሰሩ ከተከለከለ ሊከሰት የሚችለው አሁን እያየነው ያለው አይነት ችግር ነው። አስር ዓመት ደግሞ በጣም ትልቅ ነው። በእነዚህ ዓመታት አብዛኞቹ ድርጅቶች ጠፍተዋል፤ ተዘግተዋል፤ አዳዲሶችም ሊቋቋሙ አልቻሉም። ይሄ በሆነበት ሁኔታ ብዙ ነገር መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን አሁን በመጠኑ ምቹ የሆነ ሁኔታ አለ፤ መስራትና ራሳቸውን ማብቃት ይገባቸዋል። በዚህ በተወሰነ ዓመታት ብቻ አዳዲስ ድርጅቶች እየተቋቋሙ ነው። የተዳከሙትም ዳግም ራሳቸውን እያጠናከሩ ነው ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፈው ስርዓት እነዚህ ድርጅቶች በአዋጅ እንዲዳከሙ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል የውጭ ሃይሎች ጉዳይ አስፈፃሚ ሆነው የተገኙና ለአገር ደህንነት ስጋት የሚፈጥር እንቅስቃሴ ማድረጋቸው እንደሆነ ይነሳል። በእርግጥ ያ ችግር ነበር ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ሄኖክ፡-** አሁን ያነሳሽውን ነገር በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛ ሁሉም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ንፁህ ነው ማለት አይቻልም። እንዲህ አይነት ነገር የሰሩ ምን ያህል ናቸው? ብሎ መጠየቅ ግን ይቻላል። ያለነው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፤ የሚመራውም በኢትዮጵያውያን ነው፤ እንዲህ አይነት የህግ ጥሰት በሚፈፅሙት ላይ እርምጃ መውሰድ ይቻላል። ሁለተኛ ቁጥራቸውም ያን ያህል ብዙ ባለመሆናቸው ማስተካከል ይቻላል። በህግ ማረምና መቆጣጠር የመንግስት ስልጣን ስለሆነ የሲቪክ ማህረሰብ ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ ተከትለው መስራት ስላለባቸው ምንም ለቁጥጥር የሚያዳግት ነገር አይኖርም።

ሁለተኛው ትልቁ ክፍተት የሚኖረው ትግበራ ላይ ነው። ትግበራ ላይ ከተሰጣቸው ዓላማ ውጭ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ ተብሎ ከታሰበ ያንንም መቆጣጠር ይቻላል። ምክንያቱም የመቆጣጠር ስልጣን ያለው መንግስት በመሆኑ በገሃድ ከሚሰሩት ውጭ ሲሰሩ ከተገኙ እስከመዝጋትና ፍቃዳቸውን እስከመሰረዝ ድረስ ስልጣን አለው። ነገር ግን በህግ ትልልቅ ጉዳዮችን መገደቡ ጉዳቱ በአገር ላይ መምጣቱ አይቀርም። አሁንም የምንለው ይህንኑ ነው፤ ለምሳሌ እንዲህ አይነት ነገሮች ሲከሰቱ መንግስት ጋር ሳይደርስ ምክር ቤቱ ራሱ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ የስነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅተናል። ይህም ማለት ድርጅቶች ራሳቸው ቅሬታ እንዲያቀርቡና ራሳቸውን እንዲያርሙ የሚያደርግ ነው። ምክንያቱም ከአገር ህልውና የሚበልጥ ነገር የለም።

ጥቂት ድርጅቶች እንዲህ አይነት ችግር ፈጥረው ቢገኙ እንኳን ማረም የሚቻልበት መንገድ ባለበት ሁኔታ ግን ዲሞክራሲና መብት ላይ እንዳይሰሩ በህግ መደንገግ ከዚያ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ያሳጣል። ደግሞም ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ይሆናል ብዬ አላስብም። ወደፊትም መሆን ያለበት ባልተገባ ድርጊት ውስጥ የአገርን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ድርጅቶች ቢኖሩ ይሄ ምክር ቤትም መንግስትም በጋራ ሆነን እርምጃ መውሰድ እንችላለን። በዚህ ሰበብ ግን ይደረግ የነበረው የሲቪል ማህበራትን የማስደንገጥና የማሸማቀቅ ስራ ነው። እንደሚታወቀው የእነዚህ ተቋማት አንዱ ሚናቸው መንግስትም ያለአግባብ ስልጣኑን የሚጠቀም ከሆነ ያንን መተቸና ምክረ ሃሳብ መስጠት እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳብ ማመላከት ነው። እንዲህ አይነት ተቋማት እንዳይኖር የተደረገው ጥረት ውድቀት አምጥቷል ባይ ነኝ። ህዝቡም ብዙ ተጎድቷል፤ ሲቪል ማህረሰቡ ተደራጅቶ መብቱን ለማስከበር አልቻለም ነበር። ይህንን ሰበብ በማድረግ መብትን መገደብ በአገር ልማት ላይ ትልቅ ጉዳት አምጥቷል። እሴቶቻችንን ማጎልበት አልቻልንም።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ተቋማት የፖለቲካ እና የእምነት ውግንና በማሳየትም ይታማሉ፤ ከዚህ አንፃር የነበረውን ችግር እንዴት ይገልፁታል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንግዲህ በመርህ ደረጃ የሲቪል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ማህበረሰብ ድርጅቶች ገለልተኛ ናቸው። ከመንግስትም ሆነ ከሌላ አካል ውግንና ነፃ ሆነው ይሰራሉ ተብሎ ነው የሚታመነው። ሲቋቋሙም «መንግስታዊ ያልሆኑ» የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው ነው። ይህም ምንም አይነት የፓርቲ ውግንና እንደማይኖራቸው በግልፅ የተቀመጠ ጉዳይ መሆኑን ነው የሚያሳየን። ይሁንና ሰዎች በሃይማኖታቸው፣ በጎሳ፣ አልያም በጓደኝነት የመደራጀት መብት ህገ-መንግስቱ ሰጥቷቸዋል። ያ ማለት ውግንና ይዘው ሌላውን የሚያገል ሥራ ይሰራሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን በአገራቸው የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ አይሰሩም ማለት አይደለም። አንዱ ብዥታ ያለው በዚህ ጉዳይ ላይ ነው። የፖለቲካ ሁኔታውንም ሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲፈቱ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላሉ። የነበሩትን ሁኔታዎች ስናይ ከተደራጁበት አይነት አኳያ ይህንን መርህ የሚጥሱ ሊኖሩ ይችላሉ።

ይህም የሚሆነው አንደኛ ግንዛቤ ካለመኖር አንፃር ሊሆን ይችላል፤ ሁለተኛ ደግሞ ሰው በተፈጥሮ ለሆነ አካል ይወግናል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ደግሞ መንግስት ጡንቻ አለው። አንዳንዶች የመንግስትን አቋም የማንፀባረቅ ነገር ታይቶባቸው ይሆናል፤ ሌሎች ለሚመስላቸው የሚወግኑበት ሁኔታ ይኖራል። ግን ይህ ውግንና በፍፁም ይሁን ብለን የምንተወው ነገር አይደለም። አሁንም ቢሆን በተለይ በመንግስት በኩል ውግንና ያላቸው ሲደገፉ እናያለን። ይሄ ለቁጥጥርም ያስቸግራል። በእርግጥ ይሄ ምክር ቤት የተቋቋመው በቅርቡ እንደመሆኑ ከዚህ በፊት የነበረውን ችግር መቆጣጠር የሚችል አካል አልነበረም። የእርምጃዎችንም ለመውሰድ አቤት የሚል የለም። እንደፈለጉ ወዲህና ወዲህ ሊያዟቸው ይችላሉ።

በአጠቃላይ የሲቪል ማህበራት የሚገባቸውን ቦታም ሆነ ነፃነት አግኝተው እስካልሰሩ ድረስ እንዲህ አይነት ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን አሁን ይሄ ምክር ቤት ማንኛውም ድርጅት ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ እንዲሰራ ፈፅሞ አይፈቅድም። የስነ-ምግባር ደንቡም ውግንናቸውን ይዘው መስራት እንደሌለባቸው ነው የሚደነግገው። ምክር ቤቱም ከምንም ውግንና ነፃ ሆነው እንዲሰሩ ግፊት ያደርጋል። ይህንን ተላልፈው ሲገኙ ተጠያቂ እናደርጋቸዋለን። በነገራችን ላይ የስነ-ምግባር ደንቡን ተፈፃሚነት የሚከታተል ኮሚቴ አለ። ይህ ኮሚቴ የሁኔታውን ደረጃ አይቶና መርምሮ ከፍ ያለ ከሆነ በህግም እስከማስጠየቅ ድረስ ሊደርስ ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታስ ድርጅቶቹ ነፃነታቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንግዲህ አስቀድመን እንዳነሳነው መንግስት ሊያደርግ የሚችለው ህግን ማሻሻል ነው። በነገራችን ላይ ገዳቢ የነበረውን ህግ ማንሳት በራሱ ትልቁ እርምጃ ነው። ይህም ማለት እንደችሮታም ባይሆንም መንግስት ግን አንድ ትልቅ ነገር አድርጓል ብለን እናምናለን። ሁለተኛው ጥሩ ነገር ደግሞ ይሄ ምክር ቤት መቋቋሙ ነው። ከዚህ ቀደም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ አልተፈቀደም፤ እንዲህ አይነት ምክር ቤት እንዲኖረውም በአዋጅ ስልጣን አልተሰጣቸውም። እነዚህ ነገሮች ከህግም ሆነ ከመደላደል አንፃር ስናያቸው በጣም ትልቅ የሚባሉ ናቸው። ከዚህ በኋላ ደግሞ የታሰበውን ዓላማ ነፃና ገለልተኛ ሆነው፤ አንቺም እንዳነሳሽ ነፃነቱ ኖሯቸው ለመስራት አንደኛ ድርጅቶቹ ራሳቸው ለዚህ የነቃ ተሳትፎ ማድረግና የተሰጣቸውን መብት ተጠቅመው አሳማኝ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ራሳቸውን ማሳደግና ማጠናከርም ይገባቸዋል።

ሁለተኛ መንግስትም ሆነ ሌላ አካል እንደመንግስት ሆነው እንዲሰሩ መጠበቅ የለባቸውም። ይህም ማለት ድርጅቶቹ ነፃነቱ ከተሰጣቸው በሚሰሩበት ጊዜ ሊገጥማቸው የሚችል ተፅዕኖ መኖር የለበትም። ከዚያ ይልቅ ገንቢና ተባባሪ ሆኖ መስራት ነው ከሁሉም የሚጠበቀው።

**አዲስ ዘመን፡- በስድስተኛ አገር አቀፍ ምርጫ የተሳተፉ የሲቪክ ማህበራት ምን ያህል ተልዕኳቸውን አሳክተዋል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ከተሳትፎ አንፃር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከዚህ ቀደም በነበሩትም ምርጫዎች ብዙ ሲሳተፉ ነበር። የተሳትፏቸውን ውጤታማነትን ለመለካት ግን የተከናወኑትን ምርጫዎች ምን ያህል ዲሞክራሲያዊ ነበሩ? የሚለውን ማየት አስፈላጊ ነው። አገራችን ምን አይነትና እንዴት አይነት ምርጫ ስታካሄድ እንደነበር ለሁላችንም ግልፅ ነው። ስለዚህ አንዱ እንዲሻሻል የምንፈልገው ጉዳይ ነው። ነፃ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለአገር ያስፈልጋል ብለን ስንታገል የቆየንበት ነው። በዚህ ረገድ ከተሳትፎው ባለፈ ስር ድረስ ገብተው በትክክል ታዝበው ያዩትንና ያገኙትን ሪፖርት ያቀርባሉ የሚለው ነገር አቅም ይጠይቃል። እንግዲህ አስቀድሜ እንዳልኩሽ



እንዲህ አይነቱ ጉዳይ ላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተሰሚነታቸው እንዳይኖራቸው ተደርገው ረጅም ጊዜ ቆይተዋል። በዚያ ውስጥ ተሳትፏቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል።

በአሁኑ ምርጫ ከዚህ ቀደሞቹ በተለየ «አገር መስርተዋል» ማለት የሚያስችል ስራ ሰርተዋል። ለምሳሌ በአሁኑ ምርጫ ከሌላው ጊዜ በተለየ የውጭ ታዛቢዎች አለመኖራቸውና በዚህ ወሳኝ ጊዜ ድርጅቶቹ ከ45ሺ በላይ የሚሆኑ ሰራተኞቻቸውን በምርጫ ትምህርት ላይ ተሰማርተው ሰርተዋል፤ ታዛቢም ሆነዋል። ይህም ማለት ፍፁም የሆነ ሥራ ሰርተዋል ማለት አይደለም። ግን ካየነው በአሁኑ ምርጫ የተሳተፈው ሰው ታዛቢም ሆነው ከዚያ በኋላም አገረ-መንግስት እንዲፀና ህዝቡም ከተለያየ ችግርና ስቃይ ከሚመጣ ብጥብጥ ለመታደግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል። ምርጫን ተከትሎ ከሚመጣ ብጥብጥ ለመታደግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ከዚያም ባለፈ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲ ጠርተው እውቅና ሰጥተዋል። በሰላም በመጠናቀቁ ሁላችሁም አሸናፊ ናችሁ በማለት አመስግነዋል። በአጠቃላይ ምርጫውን ለየት የሚያደርገው በሰላማዊ መንገድ ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ በሰፊው መስራታቸው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በምርጫ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ዝግጁ ያለመሆን ይስተዋላል፤ ከዚህ አኳያ ያለውን ችግር በቀጣዩ ምርጫ እንዳይደገም በምክር ቤቱ ምን ታስቧል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** አሁን ያነሳሽው ችግር በተጨባጭ የሚታይ ነው። በሲቪል ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በምርጫ ሃሳብ ሂደት ውስጥ በአገራችን ያለው ሁኔታ የአንድ ወቅት ስራ ነው የሚመስለው። እንዲህ አይነቱን ችግር ለመፍታት በቀጣይ በትኩረት መሰራት አለበት። አስቀድሞ ሕዝቦችን የማስተማር፣ ስለምርጫ የማወያየት ይገባል። ይሁንና የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ ማህበራቱ ምርጫ ሲደርስ ነው በደንብ የሚንቀሳቀሱት። ማን ምን አይነት ሃሳብ እንዳላቸው ሳናውቅ ነው ወደ ምርጫ የሚገባው። ስለዚህ ይህ አጠቃላይ ችግር ነው። እንዲህ ያሉ ነገሮች ለተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለምርጫ ሂደቱ በቋሚነት መሰራት እንዳለበት እናምናለን። እንዲህ ሲሆን ወደሚፈለገው ውጤት እንመጣለን። በአጠቃላይ የምርጫ ስራ የዘመቻ ስራ ሳይሆን ሁልጊዜ መሰራት ያለበት ነው። ሁልጊዜ ማህበረሰብ መንቃት፣ መረጃ ማግኘት፣ ማሰብ፣ መከራከርና መወያየት ይገባል። ይህ ሲሆን ውጤት ይመጣል፣ ያማረ ምርጫ ይኖራል፣ አገርን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገር ይቻላል።

ብዙ ጊዜ ምርጫን ተከትሎ ብጥብጥ፣ ሁከት የሚኖረው አስቀድሞ ግንዛቤ ማስጨበጥ ባለመቻሉ ነው። ማህበረሰቡ ውዥንብር ውስጥ ይገባል፤ ያን ጊዜ ስሜት ይነዳናል። ከመጀመሪያ ጀምሮ ያየናቸው የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሕዝቡ እያወቃቸው፣ ሃሳባቸውን እየተገነዘበ ቢሄድ ጠቃሚ ነው። ለማገዝም ሁልጊዜ ዝግጁ ነን። አንዳንዶች «የምርጫ ሥራ ሱሪ በአንገት ነው» የሚሉት እውነታቸውን ነው። ለሲቪል ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በአንድ ወርና በ15 ቀናት በርካታ ፓርቲዎች ፕሮግራማቸውን ሲያስተዋውቁ ሕዝቡ ለመለየት ያስቸግረዋልና መሻሻል ይኖርበታል ባይ ነን።

**አዲስ ዘመን፡- ከዲፕሎማሲ አኳያና በአገር ላይ ስጋት የሚደቅኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ምን አይነት ስራዎችን ነው የምታከናውኑት?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ምክር ቤቱ አዲስ እንደመሆኑ በዚህ ጉዳይ ብዙ አልሰራንም። ግን ከተመሰረተ ጀምሮ ባለን አቅም ዲፕሎማሲውን፣ በተለይም ትኩረት የምናደርገው ሕዝባችን እንደመሆኑ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ነገር ስለሚያሳስበን ሃሳባችንንም እንገልጻለን። በተለይም የወቅቱ ሁኔታ ላይ መግለጫዎች አውጥተናል፣ ውይይቶች አካሂደናል። ግጭቶችን ለማብረድ መንግስት እስከመጨረሻ የሰላም አማራጮችን እንዲጠቀም ምክረ-ሃሳብ ሰጥተናል። ሕዝቡ እንዲረዳዳ ተደርጓል። በውስጥ ጉዳዮቻችን በቂ መረጃ ሳይኖራቸው የሚደረገውን ያልተገባ የውጭ ጫና ተቃውመናል።

በአሜሪካ መንግስት ሊጸድቅ የቀረበው ኤች አር 6600ን የምናየው ከሕዝቡ አኳያ ነው። በአሜሪካ መንግስት በኩል ዴሞክራሲና ሰላም ለማስፈን የረቀቁ ሕጎች ቢገለፅም ይህ ህግ ከታሰበለት አላማ ወጥቶ ሕዝባችን ላይ ጫና ሊፈጥር ይችላል ብለን ገምግመናል፤ ያንጸባረቅነውም ይህንኑ ነው። አሁን ያለንበትን ሁኔታ ህጎቹ ቢተገበሩ የበለጠ ያባብሱታል እንጂ መፍትሄ አይሰጡም የሚል አቋም አለን። ሌሎች መፍትሄዎችም መከተል ይገባል ብለናል። አሁን የብሄራዊ መግባባት ኮሚሽን ተቋቁሟል። እገዛ ማድረግ ይቻላል፤ በጎ ነገር ሊያመጡ ይችላሉ የሚል እምነት አለን።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ አንዴ በጎሳ፣ ሌላ ጊዜ በሃይማኖት ስም በርካታ ችግሮች ሲፈጠሩ ይታያል፤ ሕዝቡ ተቻችሎ የመኖር እሴትን እንዲያጎለብት፣ አብሮነትን ለማስቀጠል ድርጅቶቹ ምን ያህል ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ለረጅም ጊዜ የሰላም ማስፈን፣ የግጭት አፈታት ስራዎችን መስራት ተገድቦ ነበር። በፊት ባህላዊ እሴቶችን የማጎልበት ስራ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰፊው ይሰሩ ነበር። ጥቂቶች ካልሆኑ በስተቀር እንዲህ አይነት ስራ የሚሰሩ አልነበሩም። አሁን ማህበረሰቡ በሰላም ጉዳይ ካልተወያየና ካልሰራ ውጤት አይኖርም። ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህገ-መንግስቱ በሰጣቸው መብት መሰረት ተደራጅተው በእነዚህ ጉዳዩች ላይ መስራት አለባቸው። ለዘመናት ተደራጅተው ያንን መስራት አልቻሉም። እንደ አገር እሴቶቻችንን እያጣናቸው መጥተናል። የሃይማኖታዊ በጎ እሴቶቻችንን አውጥተን፣ አልምተን ባለመጠቀማችን አሁን የሚታዩ በርካታ ችግሮች ተከስተዋል።

አሁንም ግን ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሰላምን ነው የሚሰብኩት፣ የቆሙትም ለእዛ ነው፣ የሕዝብ ደህንነትም ያሳስባቸዋል። በመሆኑም በሰፊው ወደ ስራ መግባት አለባቸው። ያም ሆኖ ውጤት በአንድ ጊዜ የሚመጣ ባለመሆኑ በጣም ረጅም ጣልቃ ገብነት የሚፈልጉ ናቸው። የአገርን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ያስፈልጋል። ይህ የሁሉም ስራ ነው። በተለይም ሁላችንም እርስ በእርስ ተጋምደን የምንኖር በመሆኑ የተወሰኑ ማስተካከያዎች ከተደረጉና ስራዎች ከተሰሩ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ አይሆኑም። ከዚህ አኳያ ወቅታዊ ጉዳዮች ሲመጡ እንደ ምክር ቤት ቅድሚያ እንሰጣለን። አሁንም የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን ለማገዝ፣ ከመንግስትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሰላም ለማስፈን ተቀራርቦ በመስራት ቅድሚያ ሰጥተን እየሰራን ነው። አሁን የተጀመሩ ጥረቶች አሉ። በቀጣይ ከፖለቲካ ፓርቲዎችና ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ ለመስራት አቅጣጫ አስቀምጠናል። ምክንያቱም ግጭት ሲመጣ ብቻ ሳይሆን የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ የዘወትር ተግባራችን ሊሆን ስለሚገባ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የምክክር ኮሚሽኑን የምታግዙት በምን መንገድ ነው፤ የያዛችሁት አቅጣጫ አለ?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ኮሚሽኑን ለማገዝ ጥርት ባለ መንገድ የኮሚሽኑን ሂደትና ሃሳብ መረዳት ቀዳሚ ተግባር ነው ያደረግነው። ከኮሚሽነሮቹ ጋር ተገናኝተን ምን ደረጃ እንዳሉ፣ ምን ሃሳብ እንዳላቸው ተወያይተናል። በቀጣይም ሲቪል ማሕበራት ድርጅቶች ምን አይነት ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባ ስብሰባ በማካሄድ ውይይት አድርገናል። ግንኙነቱ ቀጣይነት ይኖረዋል። ሊያማክር፣ ሊገመግም፣ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሚና እና ሂደቱንም የሚመረምር ቡድን እያቋቋምን እንገኛለን። የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እናካሂዳለን። የታሰበው ነገር እንዲሳካ ሚናችንን ለመወጣት እየተንቀሳቀስን ነው። ሚናችንን በመወጣት የምንሳተፍበት ሁኔታ መኖሩን ተገንዝበናል።

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በአገር አቀፍ ደረጃ መዋቅር አለ። መዋቅሩን በትክክል ማስተባበር፣ ማቀናጀትና የጠራ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ከተቻለ ትልቅ እገዛ ነው ብለን እናምናለን። ማህበራቱ ገለልተኛ የሆኑና ምንም አይነት ውግንናም የሌላቸው በመሆናቸው ከብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሃሳብ ጋር የሚሄድ ነው። በጣም ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ነው የምንሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- የምታመነጯቸው ሃሳቦች ለፖሊሲ ግብዓት ጠቃሚ መሆናቸው ይታመናል። የምታቀርቧቸው ምክረ ሃሳቦችን መንግስት ይቀበላቸዋል? እንደመፍትሄስ ጥቅም ላይ ይውላሉ?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ይህንን ከብዙ አቅጣጫ መመልከት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉ ጥናቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚደረጉ ምርምሮችን ማየት ያስፈልጋል። ከጥናቱም ባሻገር ማህበረሰቡም፣ መንግስትም ተጠቅሞባቸዋል ወይ? ይህ ባህልስ አለ? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። በርካታ ጥናቶች ይደረጋሉ፤ ግን ጥቅም ላይ አይውሉም። ብዙዎቹ የሼልፍ ማድመቂያ ናቸው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አሁን እያደረግን ያለነው እነዚህን እውቀቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ መምከር ነው። ለዚህ ግን ማለማመድም ይገባል። እውቀቱን ይዞ የሚሞግትም ያስፈልጋል። ከምክር ቤት ጋር ተቀራርቦ ለመስራት ጥያቄ አቅርበን ተቀብለውናል። በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ፈቃደኛ ሆነው ለመጀመሪያ ጊዜ ጠይቀውን ተሳታፊዎችን ስም ዝርዝር ልከናል። ፖሊሲ ሲወጣ ሌሎች ተግባራትም ሲከናወኑ የመገናኛ መንገዶች ያስፈልጋሉ።

ከእዚህ ባለፈ ግን በሚወጡ አዋጆችም የነቃ ተሳትፎ አድርገናል። የምክክር ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ ሃሳቦቻችንን ተካትተዋል። ይህ መዳበር አለበት። እንደምናስበው ስኬታማ ባይሆንም ተግባሩ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የተሰጠንም ቦታ ትልቅ ነው። እንደሲቪል ማህበራት ድርጅቶች መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ተደማጭነትም አግኝተናል፤ ይህ ለምንሰራው ስራ ሞራል ነው። በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 50 የሚደርሱ የሲቪል ማህበራት በረቂቅ አዋጆች ለማወያየት እድል አግኝተዋል። በጠቅላይ አቃቢ ህግ በኩል አፈጻጸማቸውን አብረን ገምግመናል። ሃሳባችንን ሰጥተናል፤ ይህ ጅምር ነው፤ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል።

እንደሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሕዝብ ጉዳይ ያሳስበናል። ልዩነቶች ሃሳቦች ወደ ጠረጴዛ መጥተው በሰላማዊ ሁኔታ የመፍታት ባህል ቢዳብር መልካም ነው። ልዩነቶች የሚፈቱበት መንገድ ሃይልና ጥፋት የተሞላበት ነው። በዚህ በጣም እናዝናለን። በየቀኑ በተለያየ መንገድ መረጃው ይደርሰናል። ዋጋ ያለው ሰው ልጅ እዚህም እዚያም ሕይወት እያጣን ነው፣ ሰው እየተፈናቀለና ንብረቶች እየወደሙ ይገኛሉ። እንደ አገር የመቀጠል ጉዳይ በጣም ያሳስበናል። የሃሳብ ልዩነቶችን ሰከን ባለ መንገድ በውይይት መፍታት ይገባል። ያለው አካሄድ መለወጥ ይገባዋል። ይህ ነገር ተለውጦ ማየት ስለምንፈልግ በዚህ ላይ መስራት አለብን። በፖለቲካ፣ በሃሳብ መሸናነፍ ያለ መሆኑን ሁሉም ማመን አለበት፣ ሰከን ማለት ያስፈልጋል። ዛሬ ከተሸነፈ አሻሽሎ ነገ አሸንፋለሁ በሚል በሰላማዊ ትግል ማመን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሄኖክ፡-** እኔም ለተሰጠኝ እድል ከልብ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ድጋፍና ስምምነት ኮሮናን ለመከላከል

**አስናቀ ፀጋዬ**



በኢጋድ የምስራቅ አፍሪካ ልማት በይነ-መንግስታት ከአውሮፓ ህብረት የኮቪድ-19 ምላሽ ፕሮግራም ጋር በመተባበር ለኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል የሚያግዙ የህክምና ግብአቶችን ባሳለፍነው ሳምንት በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመገኘት አበርክቷል። ከዚሁ ጎን ለጎንም ኮቪድን ለመከላከል የሚያስችል የሶስትዩሽ ስምምነት ተፈራርሟል።

ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተበረከተው ድጋፍ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚሰጠውን ምላሽ የሚደግፉ ሶስት አምቡላንሶች፣ አንድ ተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ እና ለህክምና ግብአት የሚሆኑ የእጅ ጓንቶች መሆናቸውም ታውቋል። በአውሮፓ ህብረት-ኢጋድ የኮቪድ-19 ምላሽ ፕሮግራም አማካኝነት የተገኙት ደረጃቸውን የጠበቁ ሁለት አምቡላንሶች እና አንድ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጠው አምቡላንስ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተጋላጭ የሆኑ የድንበር ተሻጋሪ ማህበረሰቦችን ለመደገፍ እንደሚረዱም ተጠቁሟል።

በድጋፍ የተበረከቱት አምቡላንሶቹ የጤና እንክብካቤ ምላሽን ለማሻሻል በኢትዮጵያ ድንበር ዘለል አካባቢ ወደሚገኙት ጋላፊ፣ መተማ እና ሞያሌ እንደሚላኩም ተነግሯል። ድጋፉ ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ ብሎም በምስራቅ አፍሪካ እያደረሰ ያለውን የጤና፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ለመቅረፍ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑም ተገልጿል።

ከዚሁ የህክምና ግብአቶች ድጋፍ ጎን ለጎን በኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር፣ በጂቡቲ ጤና ሚኒስቴርና በኢጋድ መካከል የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያስችሉ የመግባቢያ ሰነዶች ፊርማ ስነስርአት ተካሂዷል። የመግባቢያ ሰነድ ስምምነቱ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መካከል የድንበር ተሻጋሪ የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ላይ የኮቪድ-19 የክትባት ተደራሽነትን ማሻሻል ላይ ያተኮረ ስለመሆኑም ተነግሯል።

ስምምነቱ በጅቡቲ-አዲስ አበባ የንግድ ኮሪደር ላይ የሚመላለሱ 10ሺ 500 የንግድ መኪና አሽከርካሪዎችን እና ከእነዚህ ጋር ግንኙነት የሚኖራቸውን ሰዎች ለመከተብ የሚያስችል እንቅስቃሴን እንደሚያመቻችም ተገልጿል።

ከዚህ የሶስትዩሽ ስምምነት በተጨማሪ የኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ እና ኢጋድ በድንበር ተሻጋሪ አካባቢዎች ያለውን የኮሮና ቫይረስ ስርጭት ስጋት የሚከታተል የማህበረሰብ ተሳትፎ (RCCE) ጥናት ለማድረግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል። ይህ የጥናት ፕሮጀክት በኢጋድ የምርምር ክፍል እንደሚደገፍም ታውቋል።

የወቅቱ የኢጋድ ሊቀመንበር ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ እንደሚናገሩት በጤና መስከ የተደረጉ ስምምነቶች በኢጋድ አባል አገራት ውስጥ የሚገኙ ህዝቦችን ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በመከላከልና የበሽታውን ስርጭት በመግታት ረገድ ሚናቸው የጎላ ነው። ኢጋድ ለጤና ሚኒስቴር በድጋፍ መልክ ያቀረበው የኮቪድ-19 መከላከያ ግብአትም የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት በሚደረገው ጥረት ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

በቀጣይም፣ ኢጋድ ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚረዱ ወሳኝ የህክምና ግብአቶችን ከአውሮፓ ህብረት የኮቪድ-19 ምላሽ ፕሮግራም ማስተባበር ጋር በመተባበር የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል። አገራቱ ከኮቪድ-19 ለማገገም የሚያደርጉትን ጥረትም ይደግፋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በጤና፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሮ ቆይቷል። ከዚህ አኳያ ወረርሽኙ ያሳደረውን ተፅእኖ ለመቅረፍና ተፅእኖውንም ለመቀነስ በአገራት መካከል ጠንካራ ትብብርና በጋራ መስራት ወሳኝ መሆኑ ታይቷል።

በኢጋድ በኩል የተደረገው ለኮቪድ-19 መከላከያ የሚውል የህክምና መሳሪያዎች ድጋፍ ወቅታዊና የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመግታት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ነው። የላብራቶሪ ተደራሽነት በኮቪድ-19 ወርሽኝ ወቅት ቁልፍ ችግር የነበረ በመሆኑ ይህ ድጋፍ ይህን ችግር በመቅረፍና ድምበር ተሻግሮ የወርሽኙን ሰርጭት በመዋጋትና ሌሎች በሽታዎችንም በመከላከል ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። በተጨማሪም በዚህ ቀጣና ለሚገኙ ነዋሪዎች የኮቪድ ምርመራና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትን ለመጨመር የሚደረገውን ጥረትም ይደግፋል።

በኢትዮጵያና በጅቡቲ ጤና ሚኒስቴርና በኢጋድ መካከል የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት በወሳኝ ወቅት የተደረገና በጅቡቲ-አዲስ አበባ የንግድ ኮሪደር ላይ የሚመላለሱ የመኪና አሽከርካሪዎችንና ከእነዚህ አካላት ጋር ግንኙነት የሚኖራቸውን ሰዎች ለመከተብ የሚያስችል ይሆናል።

የአውሮፓ ህብረት-ኢጋድ ኮቪድ-19 ምላሽ ፕሮጀክት ከአውሮፓ ህብረት የሚደረግለት የ60ሚሊየን ዩሮ ድጋፍ በUNOPS እየተዳደረ በምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን፣ በዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት (IOM)፣ በTrade Mark East Africa (TMEA) እና በተባበሩት መንግስታት የህጻናት ፈንድ (ዩኒሴፍ) አማካኝነት ለጅቡቲ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን እና ዩጋንዳ አገራት ለተቀናጀ የኮቪድ-19 ምላሽ ትግበራ እንደሚውል ይታወቃል።

መርሃ ግብሩ በምስራቅ አፍሪካ ወሳኝ በሆኑ የድንበር አቋራጭ አካባቢዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የኢጋድን የማስተባበር አቅም ማሳደግ፣ የጤና እና የውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ የጤና እና ንፅህና አጠባበቅ አገልግሎትን ማሳደግ፣ ሥርዓተ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መዋጋት፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ድንበሮች ለንግድ አስተማማኝ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት እንደሚከናወኑበትም ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም በጀርመን መንግስት የሚደገፈው ዲጂታል የጤና መፍትሄዎች አካል በGIZ ራሱን ችሎ የሚተዳደር እና የሚተገበር ሲሆን በአጠቃላይ መርሃ ግብሩ በሰባት አገራት 45 ጣቢያዎችን በማቋቋም 8ሚሊዮን 196ሺህ 321 የግል የኮሮና መከላከያ መሳሪያዎች እና 208ሺህ 977 የኮቪድ-19 መመርመሪያ መሳሪያዎችን ለኢጋድ አባል አገራት አቅርቧል።

እስካሁን የአውሮፓ ህብረት-ኢጋድ ኮቪድ-19 ምላሽ ፕሮግራም ለኢትዮጵያ 1ሚሊዮን 074ሺህ 762 የግል የኮሮና መከላከያ መሳሪያዎችን ማበርከቱ የሚታወስ ሲሆን እነዚህ የህክምና መገልገያዎችም ለኮሮና ቫይረስ የሚጋለጡ፣ በድንበር አካባቢ ያሉ ሰራተኞችን፣ ድንበር ተሻጋሪ ማህበረሰቦችን እና ተጋላጭ ህዝቦችን ከኮቪድ-19 ለመከላከል አግዘዋል።

ይህ መርሃ ግብር በኢትዮጵያ በስፋት ባከናወናቸው ተግባራት 864ሺህ 974 ሰዎችን ተደራሽ በማድረግ 731 ሰዎችን ከኮቪድ-19 መከላከል እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ያስቻለ ሲሆን፤ 10ሺህ 240 የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎችንም ለተጠቃሚዎች አቅርቧል።

# ለጤንነትዎ

## ሄፒታይተስ "ቢ" እና "ሲ" ምንድን ናቸው?

**አስናቀ ፀጋዬ**


ሄፒታይተስ ቢ ጉበትን የሚያጠቃ የቫይረስ ኢንፌክሽን ሲሆን አጣዳፊና ሥር የሰደደ በሽታን ሊያመጣ ይችላል። የዓለም ጤና ድርጅት እኤአ በ2019 በወጣው መረጃ መሰረት 296 ሚሊዮን ሰዎች ሥር በሰደደ የሄፒታይተስ ቢ በሽታ ሲያዙ በየዓመቱ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን አዳዲስ ኢንፌክሽኖች እንደነበሩ ገልጿል። እኤአ እስከ 2019 ሄፒታይተስ ቢ 820ሺህ ለሚገመቱ ሰዎች ሞት መንስኤ እንደነበር፤ ይህም በአብዛኛው ከ‹‹ሲርሆሲስ›› እና ከ‹‹ሄፓቶሴሉላር ካርስኖማ›› በተሰኘ የጉበት ካንሰር ምክንያት እንደሆነም ጠቁሟል።

**የሄፒታይተስ "ቢ" እና "ሲ" ምልክቶች ምንድን ናቸው?**

ብዙ ሰዎች መጀመሪያ ሲያዙ ምንም አይነት የሄፒታይተስ ቢ እና ሲ ምልክት አይታይባቸውም። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሰዎች የቆዳ እና የዓይን ቢጫ ቀለም (ጆንዲስ)፣ ጥቁር ሽንት፣ ከፍተኛ ድካም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ እና የሆድ ቁርጠትን ጨምሮ ለብዙ ሳምንታት የሚቆዩ አጣዳፊ የሕመም ምልክቶች ይታዩባቸዋል።

**መተላለፊያ መንገዶች**

የሄፒታይተስ ቢ እና ሲ ዋነኛ ምልክቶች ከእናት ወደ ልጅ በወሊድ እና በእርግዝና ጊዜ፣ በቫይረሱ በተበከለ ደም ወይም ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች ጋር በመገናኘት፣ በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ደህንነቱ ያልተጠበቀ መርፌ ወይም ለሌሎች ሹል መሳሪያዎች በመጋለጥ ናቸው።




**ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ እንዳለ እንዴት ሊታወቅ ይችላል ?**

ሄፒታይተስ ቢ እና ሲ በላብራቶሪ የደም ምርመራ በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል።

**ህክምናውስ?**

እስካሁን ድረስ ለከባድ ወይም አጣዳፊ ሄፒታይተስ ቢ የተለየ ህክምና እንደሌለ በዘርፉ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች አስታውቀዋል። ስለዚህ እንክብካቤው ምቾትን እና በቂ የሆነ የተመጣጠነ ምግብ ሚዛንን ለመጠበቅ የታለመ ሲሆን ይህም በማስታወክ እና በተቅማጥ የጠፉ ፈሳሾች እና ንጥረ ነገሮችን ለመተካት ያግዛል። አላስፈላጊ መድሃኒቶችን ታካሚው ከመውሰድ መታቀብ አለበት። ይህም እንደ ፓራሲታሞል እና ማስታወክን የሚከላከሉ መድሃኒቶች ናቸው።

**ሥር የሰደደ የሄፒታይተስ "ቢ" ኢንፌክሽን በመድሃኒት ሊታከም ይችላል?**

ሥር የሰደደ የሄፒታይተስ ቢ ኢንፌክሽን በፀረ-ቫይረስ መድሃኒቶች ሊታከም ይችላል። ሕክምናው የሲርሆሲስን እድገት ሊያዘገይ ይችላል፣ የጉበት ካንሰር የመፈጠር እድልን ይቀንሳል፣ በሕይወት የመኖር ጊዜንም ይጨምራል ተብሎ ይታመናል።

ለ"ሄፒታይተስ ቢ" ክትባት ቢኖርም ለ"ሄፒታይተስ ሲ" ግን ምንም አይነት ክትባት የለም። የፀረ-ቫይረስ መድሃኒቶች ከ95 ከመቶ በላይ የሄፒታይተስ ሲ ኢንፌክሽንን ይፈውሳሉ፣ በዚህም በሲሮሲስ እና በጉበት ካንሰር የመሞት እድልን ይቀንሳል። ይህ ሂደት በሚወሳሰብበት ጊዜ የጉበት በሽታ (ሲርሆሲስ)፤ የጉበት ካንሰርን ጨምሮ ሞትን ሊያስከትል ይችላል።

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## “እሺ” - መዘዙ ሺህ!

**ብሂላችን ሲብላላ፤**

የጽሑፉ ርዕስ የተዋቀረው “እሺ ይበልጣል ከሺህ!” የሚለው ነባሩ ብሂላችን መነሻ ሆኖ ነው። ከታዳጊነት እስከ ሽምግልና በአንደበታችን ታዝሎ የኖረው ይህ ዕድሜ ጠገብ ሸበቶ አባባል አንድም ትዕዛዝ ቀመስ ነው፤ ሁለትም መደለያና ማመስገኛ ይሉት ብጤ ነው፤ ሦስትም የእምቢታ ተቃራኒ ነው። “ከእሺታ” ይገኛሉ የተባሉት የሺህ ምንትስ “ምርቶች” የትኞቹ እንደሆኑ እንኳንስ ተቀባዩ ቀርቶ ምኞቱን የሚገልጸው ሰው ራሱ ስለማወቁ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

እንደ ብዙዎቹ ባህሎቻችንና ሥነ ቃሎቻችን ሁሉ በትርጉሙ ጉዳይ ላይ “ተከድኖ ይብሰል” በማለት ካልተጽናናን በስተቀር፤ ላይ ላዩንም ሆነ ውስጠ ምሥጢሩን ዘልቀን እንመርምር ብንል ትርፉ ድካም ስለሚሆን ሰሙን እንደ ወርቅ ቆጥረን ለጎሽታ እና ለምርቃት መገለጫነት መዋሉን ብቻ በማስታወስ ማለፉ ይበጃል። ያለበለዚያ በአባባሎችና በተረታ ተረቶች “እንዴት? ለምን? ማንስ ተናገረው?” ብለን በፍቺያቸውና በትርጉማቸው ዙሪያ ብንሟገት ገላጋይ ዳኛም ሆነ በቂ ምላሽ ለማግኘት ያዳግታል። ስለሆነም ብሂሉን የጠቀስነው ለማዋዣነት እንጂ ጫን ብለን የምናሰላስላቸው በርካታ ጉዳዮች ስላሉ እነርሱን ወደ መጠቃቀሱ ማዝገሙ ይበጃል።

“ልማድ ውሎ ሲያድር ባህል ይሆናል” እንዲሉ ምርቃት አይሉት እርግማን “ከጅማት በጠነከረ እምነት”፤ “እሺ ይበልጣል ከሺህ” አባባልን በሕይወታችን ውስጥ በትንሹም በትልቁም ጉዳዮቻችን አዘውትረን ስለምንገለገልበት ለእምቢታና ለእውነት ቆመን ለመሟገት አቅም ማግኘት አልቻልንም። በአኗኗራችን ውስጥ ሥር ሰዶ በተንሰራፋው በዚህ የእምቢታና የመራርነት ተቃራኒ ይትባሃል ዳፋ መንስኤነትም በበርካታ ጉዳዮች አሳራችንን እየበላን እንደኖርን ከታሪክም ሆነ ከተሞክሮ አንዳንድ ማሳያዎችን እየጠቃቀስን ለማየት እንሞክራለን። “መቼም አላለልኝ ከዘሩ ቁይልኝ”፤ አለ ይባላል፤ መከራው ተደራርቦ ተስፋው የተፈተነ የአገሬ አርሶ አደር። እኛም እንደዚህ ምስኪን ገበሬ ጭንቀታችን መላውን አሳጥቶን በብሂሎች መጽናናቱን ስራዬ ብለን ይዘነዋል።

**“እሺና ገለባ ባይከብድም” - ለእኛ ግን እንደ መርግ ከብዶናል፤**

ሕዝብንና ነባር ባህሎችን ሽቅብ እየተንጠራሩ መሄስ በእጅጉ እንደሚከብድ አይጠፋንም። በአገራዊ ታሪኮቻችን ውስጥ “በእሺታ” የፈሊጥ ማምለጫነት አንገት ደፍተን “ውሻን ምን አገባው ከእርሻ” በሚል ስጋትና ምንግዴነት በርካታ መከራዎችን ስንጋት ኖረናል። የደርግ መንግሥት “ሶሻሊዝም” ይሉትን የተውሶ አይዲዮሎጂ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ አሽከሞ ምድሪቱንና ትውልዱን ቁም ስቅል እያሳየ የደም ዋጋ ሲያስከፍል ጠብመንጃውና ጭካኔው አንገት አስደፍቶን “በእሺታ” ስንዘምርለትና ስናወድሰው ዘመናችን ጨሶና ተቃጥሎ ስንለበለብ ኖረናል።

ደርግን እንቃወማለን የሚሉት ጀብደኞቹ የፖለቲካ ቡድኖችም ሳይቀሩ ወጣቱን በየጎራው አቧድነው ይመንበትም አይመንበትም፤ በአግባቡ አስቦበትና አጢኖበት ርእዮተ ዓለማቸውንና ግባቸውን ሳይመረምርና ሳይፈትን “እሺ በማሰኘት ብቻ” የእሳት እራት ሲያደርጉት ኖረዋል። በአሜንታና በፍርሃት መተብተቡ እንደ ቀኖና ተቆጥሮ “እምቢ!” ብሎ እንዳይቃወም እንኳን “በእሺታ መንፈስ” አእምሮውን ሰልበውት ነበር።

“እሺ ይበልጣል ከሺህ”፣ “ከፉ ቀንንና ቅዝምዝምን የሚያሳልፉት ዝቅ ብለው ነው” ወዘተ. የሚሉትን ብሂሎች እንደ መጽናኛ በመቁጠርም ብዙው ሕዝብ ያንን ክፉ ዘመን የተሻገረው ግራ አጋብተውት ግራ ስለገባው ነበር። “ባለ ጠብመንጃውን ደርግንም ሆነ ቀስተኞቹን የወቅቱን የፖለቲካ ቡድኖች ጨክነን ብንቃወም ኖሮ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችል ነበር?” የሚለው ጥያቄ አካሄዱ ወዴት እንደሚያደርስ ስለሚገባን እንካ ሰላንትያውን አናደምቅም።

> **ፖለቲከኞቻችን በአደባባይ ሲዋሹን፣ አንቂዎች ነን ባዮች ማስተዋላችንን አንቀው የራሳቸው የድብቅ አጀንዳ መፈጸሚያ በማድረግ “በሳጠራ ውስጥ እንደታፈኑ ጫጩቶች” ሲያንጫጩን እየዋሉ “እምቢ!” ብለን ከማምረር ይልቅ መወድስ የምናቀርብላቸው በእሽታችን ማረጋገጫነት ከሆነ ውሉ አድራል። ጫን እንበል ካልንም ምክንያታዊ ከመሆን ይልቅ በስሜት እየተሳጋን “ለጠራን ሁሉ አቤት እያሉ እሺታን መግለጽ” ወደ ባህል ደረጃ አድጎ የተዋሃደን ይመስላል**

ወያኔ ኢህአዴግም ለሦስት ዐሥርት ዓመታት ያህል በብረት በትሩ እየቀጠቀጠ ሲገዛን ከሚሊዮኖች መካከል ጥቂቶች መገኘታቸውን ባንዘነጋም አብዛኛው ሕዝብ ግን አሜን ብሎ “እየተነካካም ሆነ እየተሽማቀቀ” የኖረው ለሥርዓቱና ለሥርዓቱ “ጌቶች” “እሺ ይበልጣል ከሺህ” በሚል ይትበሃል ተቀፍድዶ የግፋቸው ትርዒት እያስነባው ነበር።

ባለጊዜዎቹ ሹመኞችና የቅርቦቻቸው “ብዙኃን” እንደፈለጉ በአገሪቱ ሥልጣንና ሀብት ሲፋንኑና ሲዘባነኑ መመልከት የአደባባይ ገሃድ እውነታ መሆኑ እየታወቀ አብዛኛው ሕዝብ የትርዒቱን ትራጄዲ ይከታተል የነበረው በእንባው ጅረት እየታጠበ ነበር። የተወሰኑት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች፣ ሚዲያዎችና ብዙ ስም አይጠሬዎች ሕዝቡን ይሸነግሉ የነበረው “ይደልዎ!” በማሰኘት ጭምር “እሺ” አሰኝተው ነበር።

በእሺታና በአሜንታ ሥር ሰደው ወደ ዛሬው አገራዊ መከራ የተሸጋገሩ አንዳንድ የማሕበራዊ ነቀርሳ ማሳያዎችን እናመላክት። “ሹም እሺ እንጂ እምቢ አይባልም!” እንዲሉ፤ በየመስኩ ብዙ የመንግሥት “አደራ በል ልጆች” እንዳሻቸው በስልጣናቸው ሲጨማለቁና ሕዝብ ሲያስለቅሱ እያየን እንዳላየ የምናልፈው “በእሺታችን” እየተጽናናንና “ምን ማድረግ እችላለሁ?” በሚል ምክንያት እያሳበብን ነው።

ይህ ጸሐፊ ባለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት በአገሩ ጉዳይ አምርሮ መጮኹን የሚያውቁ የቅርብና የሩቅ ወዳጆቹም ሆኑ በጎ የሚመኙለት ሁሉ የተመካከሩ ይመስል “ለመሆኑ የአንተን የቁራ ጩኸት፣ ማሕበራዊ ሂስና በአገራዊ ጉዳዮች ላይ እዬዬ ከቶ ማን ይሰማል? ለመሆኑስ ይህንን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋናዎቹ ያነቡታል? ወዘተ” የሚሉትን ጥያቄዎች ደጋግመው ይጠይቁታል። ያሳሰባቸው የአገሬንና የሕዝቤን አበሳ እያየሁ በእሺታ ያለማሳለፌ እንደሆነ ተረድቻለሁ። “እሺ!” ብዬ ነገሮችን እንደ አመጣጡ ብቀበል ይህንን መሰል ጥያቄ እንደማልጠየቅ ይገባኛል።

የጸሐፊው መልስ አጭርና ግልጽ ነው። “ሁሉን እንዳላዩ መስሎ በማለፍ አንደበትንና ብእርን መዘጋቱ አልጠፋኝም። የእኔ ድርሻ የማሕበረሰቡ ህሊና ሆኖ ገንቢ ሃሳቦችን መዝራት ብቻ ነው። ዘሩ በተወሰኑ ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች ሕይወት ውስጥ ውጤት ሊያመጣም ሆነ ላያመጣ ይችል ይሆናል። በአንድ ነገር ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ለእውነት ኖሮ መሞት፣ ህሊናን አድምጦ መታዘዝና ለተከታዩ ትውልድ ጩኸትን አጋብቶ ማለፍ በራሱ ከክብር የበለጠ ክብር ነው። ”

ይበልጥ ሃሳቡን እናግዝፈው ከተባለም የእያንዳንዱ ዜጋ ሥራ በፈጣሪ ፊት የሚመዘነው በተቀበለው መክሊት ልክ ሕዝቡንና አገሩን ሳይታክት ምን ያህል በፍጽምና አገልግሎ እንዳለፈ እንጂ ኢትዮጵያዊ መሆኑ በራሱ እርባና ኖሮት “አበጀህ/ሽ” አያሰኝም። ይህ የማሕበረሰብ ድምጽ የመሆን ብርታትና ትዕግሥት የሚገኘው በግል ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን በፈጣሪ ፀጋ ጭምር መሆኑን ማስተወሱም ይበጃል።

**እየጠዘጠዘ ፋታ ወደነሳን የዛሬው መከራች እናቅና፤**

ድህነት የአገሬን ሕዝብ ያህል የተጫወተበት ሌላ ሕዝብ ስለመኖሩ ተገቢ ጥናት ያደረገ ሞጋች በድፍረት ወጥቶ ሃሳባችንን ፉርሽ እስካላደረገ ድረስ መልሱ “አይኖርም!” የሚል ይሆናል። “እምቢዮ!” ለማለት ድፍረትም ሆነ እምነትን አጥተን “በእሺታ” የተኮላሸንባቸውን አንዳንድ “መርገምቶቻችንን” እናስታውስ። ለምሳሌ፡- ተፈጥሮ ምንም ሳትበድለን ቆላና ደጋውን፣ ክረምትና በጋውን፣ የተፈጥሮ ሃብትንና ጸጋዎችን አመቻችታ ብትሰጠንም ዛሬም ድረስ “የልመና አኮፋዳችንን አንጠልጥለን” በጥረታቸው በልጽገው ሕዝባቸውንና አገራቸውን ከድህነት ያላቀቁ መንግሥታትን ከመማጠን ነጻ አልወጣንም። ድህነት ሲያሳክከን፣ ርሃብ ሲያቆራፍደን፣ የፍትሕና የርትዕ ጥማት ሲያንገበግበን፣ በስመ ዲሞክራሲ የፖለቲካኞች ጩኸት ሲያደናግረንና ሲያደናቁረን ቆም ብለን ነገሮችን በሰከነ መልኩ ከመመርመር ይልቅ መልሳችን አሜንታና “እሺታ” ስለሆነ እነሆ እንደ ትናንቱ ዛሬም የእለት ዳቦ እንኳን ብርቅ ሆኖብን ራሳችንን ነጻ ለማውጣት ተስኖናል።

ትንሽ ደፈር እንበል። ፖለቲከኞቻችን በአደባባይ ሲዋሹን፣ አንቂዎች ነን ባዮች ማስተዋላችንን አንቀው የራሳቸው የድብቅ አጀንዳ መፈጸሚያ በማድረግ “በሳጠራ ውስጥ እንደታፈኑ ጫጩቶች” ሲያንጫጩን እየዋሉ “እምቢ!” ብለን ከማምረር ይልቅ መወድስ የምናቀርብላቸው በእሽታችን ማረጋገጫነት ከሆነ ውሎ አድራል። ጫን እንበል ካልንም ምክንያታዊ ከመሆን ይልቅ በስሜት እየተላጋን “ለጠራን ሁሉ አቤት እያሉ እሺታን መግለጽ” ወደ ባህል ደረጃ አድጎ የተዋሃደን ይመስላል።

ድፍረታችንን መረር እናድርገው። የሃይማኖት ቤተ እምነቶች ምዕመናኖቻቸው በሥራ ጠንክረው ከጉስቁል ኑሮ እንዲላቀቁ በአስተምህሮም ሆነ በውግዘት እየገሰጹ ቀኖቻቸው በከንቱ እንዳይባክኑና ፍሬያማ እንዲሆን ከማጀገን ይልቅ በባህልና በበዓለት አፍቃሬነት እንዲልፈሰፈሱ ማድረጋቸው የዘመናት ውርሳችን ሆኖ ዛሬም ድረስ እንደገዛን አለ። ፈጣሪ ይህንን ማመካኛችንን ሲመለከት ምን እንደሚሰማው ከቅዱሳት መጻሕፍት ንባባት መልሱን ባናገኘውም በሰውኛ ስሜታችን ግን፤ “ስሜንና ክብሬን መመከቻ አድርጋችሁ በስንፍና እየኖራችሁ፤ ስትራቡና ስትጠሙ ወደ እኔ እየጮኻችሁ ታደነቁሩኛላችሁ” እያለ የሚገስጻን ይመስላል። ድርቅ መታወቂያው የሆነ ሕዝብና ርሃብ መዘባበቻ ያደረገው አገር እንዴት እንቅልፍ አግኝቶ ሊያንኮራፋ ይችላል? ቢመርም እውነታውን እንጎንጨው። “እሺ ይበልጣል ከሺህ” ሺህ ቦታ ጠፍንጎ እንደተበተበንም ልብ እንበል።

በመንግሥታዊ ተቋማትና በአገልግሎት ሰጭዎች ዘንድ የደለቡት አውሬ ጉበኞች ጉዳይም ከአሳሳቢነት አልፎ “እንደ ለማዳ እንስሳት” እየታዩና እየተጎበኙ መታለፋቸው ሌላው የኢትዮጵያ የወቅቱ ፈተና ነው። ዱሮ ጉቦና ሌብነት ይፈጸም የነበረው በድብቅና በአቀባባዮች በኩል ስቅቅ ታክሎበት ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ጉቦና ጉበኝነት “የክብር አክሊል ተደፍቶላቸው” ካስገበሩን ሰነባብቷል። የጉበኞች ኔትወርክ እንደ ቀዳሚ ዘመናቱ በስውር የተዘረጋ ሳይሆን “እወቁን እየተባለና” በፋንፋር እየተደለቀለ ጭምር ነው።

ይህንን ለማረጋገጥ ሰሞኑን በየክፍለ ከተማው ሄዶ ብቻ እውነቱን ማጣራት ይቻላል። “በዘጠና ቀናት ሥሩን ነቅዬ ምላሽ እሰጣለሁ” ያለን ገዢያችን ብልጽግና ፓርቲ፤ የጉቦን ነቀርሳ በዘጠና ቀናት ነቅሎ እንኳን ሊፈውሰን ቀርቶ ደዌው ክፉኛ በርትቶ እንደ ክረምት ችግኝ በመራባት ስለበከለን ሕዝቡ ጫናውን መቋቋም ተስኖት ምርር እያለ በማንባት ላይ ነው። “ጉዳይህ እንዲፈጸምልህ ከፈለግህ ይህንን ያህል ገንዘብ አምጣ?” እየተባለ ሲወሰንበት “እሺ ይበልጣል ከሺህ!” እያለ ከእንባው ጋር ደሙን ቀላቅሎ እየሰጠ መሆኑን ገዢዎቻችን አላወቁ ከሆነ ይወቁት። መዋቅራቸው ውሸት እያመረተ የሃሰት ሪፖርት ይመግባቸው ከሆነም እውነቱን ከእኛ ከግፉዓን ጠይቀው ይረዱ። አልሰማ ካሉም “ምከረው ምከረው፤ እምቢ ያለ እንደሆነ መከራ ይምከረው!” ብለን በብሂላችን “እናሚርትባቸዋለን። ”

በሰሞኑ አሳሳቢ ሃይማኖት ለበስ የጥላቻ ክፉ ድርጊቶች መከሰትም ጥቂት አጥፊዎችን ብቻም ሳይሆን የየሃይማኖቱን እልፍ አእላፍ ምዕመናንንና የሃይማኖቶቹን መሪ አገልጋዮች መሞገቱም ተገቢ ይመስለናል። በቂያቸውና በቤታቸው ውስጥ ሴራው ሲውጠነጠን እውነት አልሰሙም? አላወቁም? ምን እርምጃስ ወስደው ነበር? የልጆቻቸውን ትንፋሽ በቅርበት የሚውቁት እናቶች፣ ተከባሪ አባቶች፣ አንጋፋ ወንድሞችና እህቶች፣ ታናናሽ ተደማጭ የቤት ልጆች አጥፊ ልጆቻቸው ሴራ እያውጠነጠኑ ሲመክሩና ሲመካከሩ አላወቁም ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል? አይመስለንም።

ከግዙፎቹም ሆነ ከመለስተኞቹ ታሪክና ወቅት ወለድ ጉዳዮቻችን መካከል እንደወረዱ የጠቃቀስናቸው አገራዊ አበሳዎቻችን እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። ብዙ ናቸው - እጅግ ብዙ! ከብዛታቸው የተነሳ ፈጣሪም፣ መንግሥትም ሆነ ሕዝብ የየግላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጸሎቱን ለፈጣሪ፣ በሕግ አምላክን ለመንግሥት፣ አደራውን ለሕዝብ ሰጥተን ነገን በተስፋ እንጠባበቃለን። “እሺ” መዘዙ ሺህ” ያልነውም ስለዚሁ ነው። ሰላም ይሁን!

## ተናጋሪው ዶሴ

# ለእናት ውለታ ...

መልካምሥራአፈወርቅ

ጠዋት ማታ መሬት እየጫረ የሚተክዘው ጎልማሳ ነገር ሆዱ ከገባ ሰንብቷል፡፡ ሁሌም ቢሆን አይኖቹን አያምንም፡፡ በቤታቸው የሚገቡ የሚወጡ ሁሉ አይመቹትም፡፡ ወጪ ገቢውን በጥርጣሬ እየቃኘ ጥርሱን ይነክሳል፡፡ ባሻገር እያስተዋለ ይተክዛል፣ ይናደዳል፡፡ በየቀኑ ምክንያት እየፈለገ የሚብከነከንበት ጉዳይ ሰላም እያሳጣው ነው፡፡

ሁኔታውን የተረዱ ወላጅ እናት ከአጠገቡ ሆነው ይመክሩታል፡፡ እሱ ዘወትር የሚጨነቅበት ነገር እሳቸውን አሳስቦ አያውቅም፡፡ በየቀኑ ጉዳዩን እያነሳ ሲናደድ በእርጋታ ያዩታል፡፡ ባልተገባ ግምት ከሌሎች እዳይጠላ፣ እንዳይጋጭ ሲጥሩ ከርመዋል፡፡ ምክራቸውን ቢሰማም ቃላቸውን አያምንም፡፡ የሚሉትን ይጠራጠራል፣ የሚናገሩትን ያጣጥላል፡፡

እናቱ መልካም ሴት ናቸው፡፡ እሳቸውን የሚያውቁ ሁሉ ከልብ ያከብሯቸዋል፤ እህት ወንድሞቻቸውን ጨምሮ መላው ቤተሰብ ለወይዘሮዋ የተለየ ግምት አላቸው፡፡ ታላላቅ ወንድሞቻቸው ስለእሳቸው ሲናገሩ ቃላቸው አንድ ነው፡፡

በታናሽ እህታቸው አመኔታና ፍቅር አላቸው፡፡ ልጆቻቸው ለእናታቸው በእጅጉ ይሰስታሉ፡፡ ሁሉን በእኩል ዓይን እያዩ አሳድገዋቸዋል፡፡ ዛሬን ኖረው ለቁምነገር የበቁት፣ ትዳር መያዝ ጎጆ መቀለስ የቻሉት በደጓ እናታቸው ጥረትና ልፋት ነው፡፡

ወይዘሮዋ ልጆቹ እንዲዋደዱ፣ ተከባብረው እንዲዘልቁ በጎ ምሳሌ ናቸው፡፡ የመንደሩ ነዋሪም ቢሆን በእኚህ መልካም ሴት በጎነት ሲጠቀም መኖሩን መስካሪ ነው፡፡ እሳቸው የተቸገረን ጠያቂ፣ የተጣላን አስታራቂ ናቸው፡፡ ሁሌም የተናገሩት ይሰማል፡፡ ያሉት ሁሉ ይፈጸማል፡፡

ጎልማሳው የወይዘሮዋ የበኩር ልጅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እሱ ማለት ለእሳቸው የትዳራቸው የመጀመሪያ ፍሬ፣ የህይወታቸው አዲስ ምዕራፍ ነው፡፡ መቼም ቢሆን ሀዘን ትካዜውን አይወዱም፡፡ መጨነቅ ማዘኑ በገባቸው ጊዜ ጠጋ ብለው ሀሳብ ንግግሩን ያጤናሉ፡፡ ከሚለው፣ ከሚናገረው ተነስተው መፍትሄ ያሉትን ያጋራሉ፡፡

ልጃቸው የእናቱን መልካምነት አሳምሮ ያውቃል፡፡ አንዳንዴ የሚሉትን ሊሰማ ይሞክራል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ቃላቸውን አምኖ ለመቀበል፣ እንደሀሳባቸው አድሮ ለመፈጸም ይቸግረዋል፡፡

እናት የሰሞኑን የልጃቸውን ኩርፊያና ጥያቄ ካወቁት ሰንብተዋል፡፡ ከቅያሜ አልፎ ቂም የያዘበትን ጉዳይ መላ ለማለት ሲለፉ ቆይተዋል፡፡ እሳቸው እንዳሰቡት ጉዳዩ ባይሳካም ተስፋ አልቆረጡም፡፡ የሚናገረውን ክፉ ቃል በደግ እየመለሱ፣ የሚያስበውን አጉል ጉዳይ እያስታመሙ፣ ሊያሳምኑት ሞክረዋል፡፡

እናት በእሳቸውና በእህት ወንድሞቹ ላይ ያሳደረው ጥርጣሬ ሲያሰጋቸው ቆይቷል፡፡ ሀብትና ንብረትን ሰበብ አድርጎ የሚያስበውን አጉል ጉዳይ መቀበል አይሹም፡፡ ከሚላቸው ተነስተው ለማሳመን ያደረጉት ጥረት ፍሬ አልያዘም፡፡ ያም ሆኖ ዛሬም ዝም አላሉም፡፡ በተቻላቸው ሁሉ የልጃቸውን ክፉ ስሜት በበጎ መንፈስ ሊተኩ ጥረታቸውን ይዘዋል፡፡

**የቂም መነሻ ...**

ጎልማሳው ራህማቶ ከድር በሚኖርበት የገጠር ቀበሌ ከአያቱ የተቸረውን አራት ጥማድ መሬት ሲያርስበት ቆይቷል፡፡ መሬቱ ከዓመት እስከ ዓመት ያሰበውን ያሳፍሰዋል፡፡ ለም መሬቱን በርትቶ ባረሰ ጊዜ የልቡን መሻት አያጣም፡፡ በምርቱ በረከት እንዳሻው ሲጠቀም የኖረው ጎልማሳ ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ስጋት ገብቶት ትካዜ አብዝቷል፡፡

ራህማቶ ታናናሽ እህት ወንድሞቹን በጥላቻ ማስተዋል ጀምሯል፤ ሰብሰብ ብለው ካያቸው ውስጡን ደስ አይለውም፡፡ መገናኘት ማውጋታቸውን በበጎ አይተረጉመውም፡፡ የእነሱ በአንድ መሆን ለአንዳች ምክር እየመሰለው ይጠራጠራል፡፡

ራህማቶ ከአያቱ ያገኘውን መሬት ሌሎች እንዲያዩበት አይሻም፡፡ እስከዛሬ ማናቸውም የጥቅም ተካፋይ እንዳይሆኑ ሲሞግት፣ ሲያከላክል ቆይቷል፡፡ እናቱ ከእህት ወንድሞቹ እንዲስማማና፣ ጥላቻና ቂምን እንዲተው እየመከሩ፣ እየዘከሩ ነው፡፡ እሱ ግን ይህ አይነቱን ቃል ፈጽሞ መስማት አይፈልግም፡፡ ማንም በዚህ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ለማሳወቅ ጥላቻውን አሳይቷል፡፡

ወላጅ እናቱ ሰሞኑን ከልጃቸው አንደበት ያረጋገጡት



እውነታ በእጅጉ እየረበሻቸው ነው፡፡ ራህማቶ ከእሱና ከእሳቸው በቀር በቤቱ ማናቸውንም ማየት እንደማይሻ መናገር ጀምሯል፡፡ እህት ወንድሞቹ የሀብት ንብረቱ ስጋት መሆናቸውን ከመናገር አልፎ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይዟል፡፡

እናት ልጃቸው ራህማቶ እህት ወንድሞቹ በግቢው «አይድረሱብኝ» ማለቱን አልወደዱትም፡፡ ቤቱ የጋራቸው በመሆኑ ሀሳቡን መቀበል እንደማይችሉ ነግረውታል፡፡ በየአጋጣሚው ጥላቻውን የሚያሳየው ጎልማሳ በእናቱ ውሳኔ ተበሳጭቶ ጉዳዩን በሌላ ተርጉሞታል፡፡

አሁን ራህማቶ በወላጅ እናቱ ተናዶ ውስጡ እያቄመ ነው፡፡ ለንብረቱ ስጋት ከሆኑ እህት ወንድሞቹ «ተስማማ» የመባሉ እውነት አልተመቸውም፡፡ በግቢው «አይድረሱብኝ» የማለቱ ሀሳብ በእናቱ ዕውቅና ያለማግኘቱ እያበገነው ያተከነው ይዟል፡፡ እናት ደጋግመው ‹እነሱ እንዳይመጡ መከልከል አልችልም› ብለውታል፡፡ እንዲህ የማለታቸውን ጉዳይ በበጎ ያላየው ጎልማሳ የእሳቸውን ሀሳብ ከእነሱ አዛምዶ በአንድ ደምሯቸዋል፡፡

ጎልማሳው ራህማቶ እናቱን ማድመጥ ትቶ የጎሪጥ ማየት ከጀመረ ሰንብቷል፡፡ እሳቸው «የራሴ» የሚለውን ንብረት ለእህት ወንድሞቹ ሊያካፍሉ መሆኑን ጭምር እያስወራ ነው፡፡ እናት ሌሎች ልጆቻቸው ከቤት እንዲርቁ አይሹም፡፡ ሁሉም ተሰባስበው ማየት ፍላጎታቸው ነውና «ተው፣ እረፍ» ማለቱን ቀጥለዋል፡፡ የራህማቶን ስጋት የሚያስወግዱበት ጥረት ባይሳካም በየቀኑ ሊያሳምኑት፣ ሊያግባቡት ይተጋሉ፡፡

ራህማቶ እያደር ጠባዩ መቀየር ይዟል፡፡ «የግሌ ነው» በሚለው መሬት መነሻ በእህት ወንድሞቹ ያሳደረው ቂምና ጥላቻ በርትቷል፡፡ ጥቂት ቆይቶ ያስከተለው አዲስ ወሬ ደግሞ ቤተዘመዱን እያነጋገረ ነው፡፡ ጎልማሳው እናቱ ለእህት ወንድሞቻቸው ጭምር መሬቱን ሊሠጡበት መሆኑን ላገኛቸው ሁሉ ማውራት፣ ማስወራቱን ቀጥሏል፡፡

ይህ ወሬ በስፋት መዛመቱን ተከትሎ የእናት ስጋት መጨመሩ አልቀረም፡፡ ልጃቸው ከእህት ወንድሞቹ አልፎ ወደ አክስት አጎቶቹ ማለፉ አሳስቧቸዋል፡፡ አሁን ጉዳዩን ለመፍታት ሌላ አማራጭ ያሻቸዋል፡፡ ራህማቶ ከጀመረው አጉል ጥርጣሬና ጥላቻ መውጣት አለበት፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግ ወይዘሮዋ ሽማግሌዎችን ሰበሰቡ፡፡ ቤተዘመድ ጠርተው ትልልቅ ሰዎች ይዘው ልጃቸውን ጠየቁ፣ አስጠየቁ፡፡

ራህማቶ በሽምግልናው ቀን ውስጡ ያለውን ስጋት ደጋግሞ ተናገረ፡፡ እህት ወንድሞቹን ጨምሮ አክስትና አጎቶቹ የራሱን መሬት ሊቀራመቱ ማሰባቸውን በስጋት አወጋ፡፡ ለዚህ ችግር ሰበብ ሆናለች ያላቸውን እናቱን እየወቀሰ፣ ተጠያቂ አደረገ፡፡ እናት አሁንም የሚለው ሁሉ ከእውነት የራቀ መላ ምት መሆኑን ገለጹ፡፡ የሚሉትን እንዲሰማና፣ እንዲቀበል አሳሰቡ፡፡ ጎልማሳው ልጃቸው ቃላቸውን አላመነም፡፡

ሽማግሌዎቹ ሀሳቡን ሰምተው የሚለው ሁሉ ሀሰትና የተሳሳተ መሆኑን አሳወቁት፤ ራህማቶ ለጊዜው ጉዳዩን በግማሽ ልቡ ተቀበለ፡፡ ይህን ያዩት እናት እፎይ ብለው ሰነበቱ፤ እስካሁን የተነሳው የመሬት ጉዳይ ከእንግዲህ ርዕስ ሆኖ ጠብ እንደማይዘራ አሰቡ፡፡

ውሎ አድሮ በራህማቶ ውስጥ የከረመው ጥርጣሬ ዳግመኛ አገረሸ፡፡ በየቀኑ በሚያነሳው ተቃውሞና ወቀሳም እናቱን ተጠያቂ ያደርግ ያዘ፡፡ እናት አሁንም ልጃቸውን እየለመኑ የሚያስበው ሁሉ ከእውነት የራቀ ጥርጣሬ መሆኑን ሊያስረዱት ሞከሩ፡፡ ራህማቶ ከሚያርሰው ለም መሬት በየአመቱ ከበቂ በላይ ገንዘብ ያገኛል፡፡

ይህ ገቢ ለጎልማሳው ርካታ ሆኖ አያውቅም፡፡ ሁሌም ከወገኖቹ እየተጣላ በርካቶችን እየተቀየመና እያስከፋ ነገውን በአጉል ተስፋ ያልማል፡፡ ተስፋው አልያዝ፣ አልጨበጥ ባለው ጊዜም ጥላቻው እያየለ፣ ውስጡ እየጎሸ አርቆ ያስባል፡፡ ሁሌም የሀሳቡ መጨረሻ በበጎ ተደምድሞ አያውቅም፡፡ በዚህ ስሜት እንደተያዘ ሰአታት ይነጉዳሉ፣ ቀናት ያልፋሉ፡፡

በሽማግሌዎች እርቅ በእፎይታ የከረመው ቤተሰብ ሰላሙ መናጋት ሲጀምር ጎልማሳው ወንድም ታናናሾቹ ከቤት እንዲወጥሉት ጠየቀ፡፡ ይህ መሆን ካልቻለም ነገሮች በዚህ እንደማይቀጥሉ አሳሰበ፡፡ ጉዳዩን በመፍትሄ የቋጩት ሽማግሌዎች በሌሎች ላይ ፈርደው የእሱን ሀሳብ አጸደቁ፡፤ ልጆቹ ከቤት ወጥተው ሌላ ቦታ ካለው የአባታቸው ቤት እንዲቆዩ ወሰኑ፡፡

እንደሀሳቡ የሆነለት ራህማቶ አሁንም ለጥቂት ቀናት ሰላማዊ መስሎ ሰነበተ፡፡ ሁኔታውን ያስተዋሉም እፎይታ አግኝተው ከረሙ፡፡ ጎልማሳው ዛሬም የውስጡን የረሳ አይመስልም፡፡ ነግቶ በመሸ ቁጥር የክፉ አይኖቹ ምልከታ እንደቀድሞው ቀጠለ፡፡ ጥላቻና ጥርጣሬው ብሶም በወላጅ እናቱ ማቄም መቀየሙ ታወቀ፡፡

እናት አሁንም ከአጠገቡ አልራቁም፡፡ በውስጡ ያደረውን ጥላቻ አርቀው በፍቅር ሊያቀርቡት ሞከሩ፡፡ ራህማቶ እጅ አልሰጣቸውም፤ ልቡ አልሳቀላቸውም፡፡ እናቱን ከእህት ወንድሞቹ ፈርጆ፣ የሀብት ንብረቱ ጠንቅ፣ የማንነቱ ዕንቅፋት አድርጎ ሳላቸው፡፡

ራህማቶ በእጁ ያለው ለም መሬት፣ በውርስ ያገኘው ሀብት ለሌሎች ማለፉን አምኖ በጥላቻ ይብከነከናል፡፡ ማንም በዚህ ጉዳይ ሊመክርና ሊያሳምነው ቢሞክር ሊሰማና ሊቀበል አይፈልግም፡፡ ጠዋት ማታ የሚጨነቅበት የውርስ ጉዳይ ሰላም ነስቶ ጥርስ አስነክሶታል፡፡ ለዚህ ተጠያቂ የሚያደረጋቸውን እናቱን ባየ ቁጥር ውስጡ ይጋያል፣ ጥላቻው ይጨምራል፡፡

አሁን ጎልማሳው ራህማቶ በእናቱና በእህት ወንድሞቹ ላይ ያሳደረው ጥላቻ በርትቷል፡፡ ባገኛቸው ቁጥር አጠገቡ እንዳይቀርቡ፣ ወደግቢያቸው እንዳይዘልቁ የማይሆነው የለም፡፡ በየጊዜው ለዕርቅ ጣልቃ የሚገቡ ሽማግሌዎች የዕለት ድርጊቱን እንደልማድ ቆጥረው ትተውታል፡፡ ምክርና ተግሳጽ የማይገባው ሰው ዛሬም በማንአለብኝነት መራመዱን፣ በትዕቢት መታበዩን ቀጥሏል፡፡

ወንድሞቹ መኖሪያቸውን ለቀው ከወጡ በኋላ ውስጡ ያልረካው ራህማቶ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ቂምና ጥላቻውን ሊያሳይ ይሞክራል፡፡ ሰበብ የሚያደርጋቸው እናቱን ሲያገኝም በወቀሳ ሲያሸማቅቃቸው ይውላል፡፡ እናት የሚያውቁትን እየነገሩ ልጃቸውን ይመክራሉ መስማትና ማመን የማይሻው ራህማቶ ልቡ በጥላቻ እንደተሞላ ፊቱን ያዞርባቸዋል፡፡

**ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም**

ይህ ዕለት ከሌሎች ቀናት የተለየ አልነበረም፡፡ የሚያዚያ ሙቀት ያረፈበት ውሎ በወበቁ እንደታጀበ አመሻሹ ደርሷል፡፡ የራህማቶ እናት ወይዘሮ ጠጂቱ ከእራት በኋላ በስራ የደከመ አካላቸውን ሊያሳርፉ ጋደም ይላሉ፡፡ የልጃቸው ራህማቶን ኩርፊያና ግልምጫ ለምደውታል፡፡ በማደጎ የሚያሳድሯት ትንሽ ልጅ ገና በጊዜ ዕንቅልፍ እያዳፋት ነው፡፡

እሳቸውም ቢሆኑ ተቀምጠው መቆየትን አይሹም፡፡ በድካም ዝለዋል፡፡ በዕንቅልፍ አምሮት የጠበቡ አይኖቻቸው፣ ወደመኝታ እየመሯቸው ነው፡፡ ጠጂቱ ደጋግመው እያዛጉ ከትንሽዋ ልጅ አጠገብ ደረሱ፡፡ ከባድ ዕንቅልፍ ጥሏታል፡፡ ጥቅልል ብላ ከተኛችው ታዳጊ ትከሻ ብርድልብሱን ገልጠው ከጎኗ ጋደም አሉ፡፡ አፍታ አልቆዩም፡፡ ራሳቸውን ለዕንቅልፍ አሳልፈው ሰጡ፡፡

አሁን እኩለ ሌሊቱ ተጋምሶ የንጋቱ መንገድ ጀምሯል፡፡ እስካሁን በአይኑ ዕንቅልፍ ያልዞረው ራህማቶ ዓይምሮው ነገር እንዳመላለሰ አስር ሰአት ደርሷል፡፡ ገና በጊዜ ዕንቅልፍ የጣላቸው እናቱ በዓይኑ ውል አለቡት፡፡ ለእሱ ዕንቅልፍ ማጣት ሰበብ ሆነዋል፡፡ ሀብት ንብረቱን ለእህት ወንድሞቹ፣ ለአክስት ለአጎቶቹ መስጠታቸው አይቀርም፡፡ ይህን ቆሞ ከሚያይ ሞት ይሻለዋል፡፡

ራህማቶ በዚህ ጉዳይ ሌሊቱን ሲያስብበት አድሯል፡፡ ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ከእናቱ ሌላ ተጠያቂ አላገኘም፡፡ ሰአቱን ደጋግሞ አስተዋለው፡፡ ከለሊቱ አስር ሰአት እያለፈ ነው፡፡ ንዴት እንደዋጠው ወደ እናቱ መኝታ ቤት ተንደረደረ፡፡ እናቱ ትንሽዋን ልጅ በክንዳቸው እንዳቀፉ በእንቅልፍ ወድቀዋል፡፡

እናቱን ሲያያቸው ሰውነቱ ጋለ፣ የተለየ ብሽቀት ብልጭ አለበት፡፡ በመጣበት ፍጥነት ጎናቸው ደርሶ ልጅቷን ከእጃቸው ፈልቅቆ አነሳት፡፡ ዕንቅልፍ የረታቸው ወይዘሮ ፈጽሞ አልሰሙትም፡፡ ህጻኗን ሌላ ክፍል አስተኝቶ ያዘጋጀውን ወፍራም ቆመጥ ይዞ ወደ እናቱ ተመለሰ፡፡

አሁንም ወይዘሮዋ በዕንቅልፍ እንደተሸነፉ ነው፡፡ ራህማቶ የእናቱ ሁኔታ አላሳዘነውም፡፡ ያመጣውን ዱላ እንዳጠበቀ ወደ አናታቸው ሰነዘረ፡፡ ዱላው ዒላማውን አልሳተም፡፡ አይምሮው ያሰበውን አልዘነጋም፡፡ ቆመጡን የያዙ እጆቹ ድርጊቱን ደግመው፣ ደጋግመው ፈጸሙት፡፡

ራህማቶ በደግ እናቱ ላይ የፈጸመው ድርጊት ያስደነገጠው አይመስልም፡፡ በእልህ እንደተሞላ ጠጋ ብሎ አስተዋላቸው፡፡ እናት ከዕንቅልፋቸው ሳይነቁ በደም ተነክረው አሸልበዋል፡፡ ልጃቸው መሞታቸውን ሲረዳ ጊዜ አልፈጀም፡፡ በሩን የኋሊት ጠርቅሞባቸው በጥድፊያ ከመንደሩ ተሰወረ፡፡

**ሲነጋ...**

ያለልምዱ ተከርችሞ ያረፈደው የእማወራዋ በር የብዙዎችን ዓይን ስቧል፡፡ ለወትሮው ወይዘሮዋ በዚህ ሰአት በስራ ሲጣደፉ ማየት የተለመደ ነበር፡፡ ባተሌዋ እናት ሁሌ ማለዳ ወዲያ ወዲህ ሲሉ የሚያውቋቸው ጎረቤቶች በድምጻቸው መጥፋት ተጨንቀዋል፡፡ አንገታቸውን በአጥሩ አስግገው፣ ድምጻቸውን ዘለግ አድርገው በስማቸው ተጣሩ፡፡ ምላሽ አላገኙም፡፡ ግቢው ዝምታ እንደዋጠው ባወቁ ጊዜ ስጋት ገባቸው፡፡

ሰዎቹ ግቢውን አልፈው የተዘጋውን በር ከፍተው ገቡ፡፡ ያዩትን ማመን አልቻሉም፡፡ ቅን አሳቢዋ ወይዘሮ በዱላ ተቀጥቅጠው ህይወታቸው አልፏል፡፡ ጉዳዩን ፈጥነው ለፖሊስ አመለከቱ፡፡ ፖሊስ በአስፈላጊው ጥንቃቄ አስከሬኑን እንዳነሳ በእማኞቹ ምስክርነትና ጥርጣሬ ተፈላጊውን ማሰስ ጀመረ፡፡ ብዙ አልቆየም፡፡ ራህማቶ ርቆ ሳይሄድ እጁን ለዱራሜ ፖሊስ መስጠቱን አረጋገጠ፡፡

**የፖሊስ ምርመራ...**

የከምባታና ጠንባሮ ዞን ፖሊስ ተጠርጣሪውን አቅርቦ ስለወንጀሉ ድርጊት ጠየቀ፡፡ ራህማቶ ወላጅ እናቱን ስለመግደሉ አልካደም፡፡ የፈጸመውን ድርጊት አንድ በአንድ በማስረዳት አመነ፡፡ በበቂ መረጃዎች ማስረጃዎችን የሰነደው ፖሊስ ጉዳዩን ለዓቃቤ ህግ አሳልፎ ክስ እንዲመሰረት መዝገቡን አቀረበ፡፡ ዓቃቤ ህግ ከፖሊስ የቀረበለትን ዶሴ በጥልቀት መርምሮ በተጠርጣሪው ላይ ክስ መሰረተ፡፡

## ውሳኔ...

ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም በችሎቱ የተሰየመው የከምባታ ጠንባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሹ ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስጠት በቀጠሮው ተገኝቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ራህማቶ ሀጂ በወላጅ እናቱ ላይ በፈጸመው አሰቃቂ፣ ከባድና የነውረኝነት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በዕለቱ በሰጠው ውሳኔም እጁ ከተያዘበት ጊዜ አንስቶ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራትን በመወሰን መዝገቡን ዘግቷል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ይቺ ሙጃ አጨዳ....

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

በአገራችን ዋና ዋና ከተሞች በወር መጨረሻ አካባቢ ደመወዝ ወጣ አልወጣ እያሉ ሰራተኞች የሚጠያየቁትን ያህል ምን አልባትም ከዚያም በላይ በሌላ አንድ ትእይንት የወሩ መጨረሻ ሲታሰብ ይስተዋላል። ይህን ወቅት አንዳንዶች በጉጉት ሲጠብቁት ሌሎች ደግሞ በስጋት ይርዱበታል። መኪኖች በብዛት ተሰልፈው ተራ ሲጠብቁ የሚታዩበት ነው። ነዳጅ ለመቅዳት ወረፋ መያዝ።

ይህን ትእይንት በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች የተንቀሳቀሰ ሁሉ ይመለከተዋል፤ በአገር አማንም ይህ እየሆነ ነው። የወሩ መጨረሻ የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ የሚከለሰበት መሆኑን ተከትሎ ነው ይህ የሚሆነው። ብቻ ምን አለፉችሁ ነዳጅ ለመቅዳት በየወሩ ተራ መያዝ ተለምዷል።

የነዳጅ ዋጋ ሊጨምር ይችላል ከሚል ስጋት ነዳጅ ሸሚያው ይጦፋል። ሁሉም በመኪናው ሊያቁር፣ ህገ ወጦች በአንጻሩ ነዳጅ የለም፣ ዋጋ ይጨምራል ተብሏል፣ ወዘተ. እያሉ ከነዳጅ ማደያዎች ጋር እየተሻረኩ ነዳጅ በበርሜል፣ በጀርካን፣ በሌላም በሌላም መንገድ ሲያሸሹ ይታያሉ። እናም ይህ ወቅት በውድ ዋጋ የሚቸበችቡበት ህገወጥ ንግድ የሚያጦፉበት ነዳጅ የሚይዙበትና የሚሸጡበት አርገውታል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን መንግስት ከሁለት ወራት በኋላ በሚተገብረው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ አሰራር ላይ ከትናንት በስቲያ በአዳማ ከተማ ለጋዜጠኞች ባዘጋጁት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ እንደተጠቆመው፤ አገሪቱ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ የምታስገባውና ለዜጎች ከዓለም ዋጋ በእጅጉ ባነሰ ዋጋ እያደረሰች ያለችው ይህ ነዳጅ ለከፍተኛ ህገወጥ ንግድ ተዳርጓል።

የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው አካባቢዎች ነዳጅ በተለያዩ መንገዶች ቢደርስ እኔ ብዙም ችግር አለው ብዬ አላስብም፤ ባለሀብቶች ወይም መንግስት እነዚህ አካባቢዎች ነዳጅ እንዲያገኙ ለማድረግ ማደያ ባልገነቡበት ሁኔታ እዚህ አካባቢ ያለውን ህገወጥነት መከላከልም ሊያስቸግርም ይችላል። ነዳጁ ለተጠቃሚው የሚሸጥበት ዋጋ ተጠቃሚውን በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑ ላይ ነው የበለጠው ክፋቱ። ነዳጁ የሚጓጓዝበት፣ የሚከማችበትና የሚሸጥበት መንገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት አለመሆኑ ሌላው ችግር ቢሆንም የዛሬው ጉዳዬ አይደለምና አቆይቼዋለሁ።

ህገወጥ ግብይቱ እየተስፋፋ ያለበት ሁኔታ በእጅጉ አሳሳቢ እየሆነ ነው። ጥቂት በማይባሉ የአገሪቱ አካባቢዎች በቅርበት የነዳጅ ማደያዎች እያሉም ጭምር ነዳጅ ከማደያ ውጭ በየመንደሩ በውሃ መያዣ ፕላስቲክ ኮዳዎች ሳይቀር በአደባባይ በውድ ዋጋ መቸብቸቡ ግብይቱ ምን ያህል ህገወጥ እየሆነ መምጣቱን ያመለክታል።

አንድ ጓደኛዬ በቅርቡ ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ አቅጣጫ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነዳጅ በሚገባበት መስመር ከዋናው መስመር ጥቂት ኪሎ ሜትሮችን ገባ ብሎ ለስራ ጉዳይ ተገኝቶ ነበር። በአንድ የጥቃቅን ንግድ ስፍራ በሚመስል ቦታ የታሸገ ውሃ እንዳለ አይቶ ለመግዛት ይጠይቃል፤ ውሃ እንደሌለ ይነገረዋል፤ ያ ታዲያ ምንድነው ሲል ቤኒዝን ይባላል፤ ሌላ ሰው እንዲሁ፣ እነዚህ መረጃዎች የነዳጅ ህገወጥ ግብይቱ ሄዶ ሄዶ የት እንደደረሰ ጥሩ ማሳያዎች ይሆናሉ።

በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ነዳጅ በጀርካን፣ በበርሜል ወዘተ እየተጓጓዘ መቸብቸብ ከጀመረ ቆይቷል፤ ይሄ ብዙም አዲስ አይደለም፤ አዲስ የሚሆነው እዚህም እዚያም በፕላስቲክ የውሃ ኮዳ ጭምር እየተፈጸመ መሆኑ ላይ ነው።

የነዳጅ ህገወጥ ግብይቱ በእዚህ ላይ ብቻ አላቆመም። በኢትዮጵያ ያለው የነዳጅ ዋጋ ከጎረቤት አገሮች አንጻር ሲታይ በጣም ርካሽ መሆኑም ህገወጥነቱ ይበልጥ እንዲስፋፋና ወደ ኮንትሮባንድ ንግድ እንዲሸጋገር እያረገው ነው። ነዳጃችን ለኮንትሮባንዲስቶችም ተዳርጓል። ኮንትሮባንዲስቶች ይህን ነዳጅ፣ ነዳጅ በውድ ዋጋ ወደሚሸጥባቸው ጎረቤት አገሮች እያስወጡ ናቸው።

ሁኔታው ከመሀል አገር ወይም ነዳጅ ማደያዎች በስፋት ከሚገኙባቸው ከተሞች በበርሜል፣ በጀርኪን እየተገዛ ወደ ውጭ የሚላክበት ብቻ እንዳልሆነ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት። መቼም የነዳጅ ቦቴ እየተጠለፈ ነው ማለት ያስቸግራል። ተጠለፈም ሲባል ተሰምቶ አይታወቅም። ነዳጅ ለየማደያው የሚልከው የመንግስት አካል እንደመሆኑ በምንም መልኩ ማደያዎችም ካልተላከላቸው ቦቴ ነዳጅ አያወርዱም። ባለቦቴውም ያልተባለበት ቦታ ወስዶ ያራግፋል ተብሎ አይታሰብም። የሰነድ ርክክብም አለና።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ከትናንት በስቲያ ከሁለት ወራት በኋላ በሚጀመረው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ ስርአት ላይ የሚመከር መድረክ ባካሄደበት ወቅት እንደተጠቆመው፤ በአገሪቱ የነዳጅ ማደያ ተደራሺነት ችግር በስፋት ይስተዋላል፣ በአብዛኛው የአገሪቱ አካባቢ የነዳጅ ማደያ የለም። በአሁኑ ወቅት ደግሞ እንደ ባጃጅ ያሉ ተሽከርካሪዎች በአገሪቱ በስፋት እየተንቀሳቀሱ እንደመሆናቸው ለእነዚህ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ነዳጅ ያስፈልጋል። በእዚህ ላይ እጥረት ሳይኖር እጥረት እንዳለ አድርገው የሚያናፍሱ፣ የነዳጅ ማጓጓዝ ሂደቱ መጠነኛ መጓተት ሲታይበት ትልቅ ችግር እንደተፈጠረ አድርገው የሚያናፍሱት ወሬ እና የመሳሰሉት በነዳጅ ግብይቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳረፉ ሲሆን፣ የነዳጅ ህገወጥ ግብይት እንዲጦፍ ምክንያት እየሆኑ ናቸው።

የነዳጅ ህገወጥ ግብይቱ የበለጠ እየጦፈ ይገኛል። የዚህ አንዱ ምክንያት ደግሞ ነዳጅ ወደ ውጭ አገር በኮንትሮባንድ እንዲወጣ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ነው። በውጭ ምንዛሬ ከውጭ እንዲገባ እየተደረገ፣ ህዝቡን ከኑሮ ውድነት ለመታደግ በሚል ከዓለም ገበያ ዋጋ በታች ለተጠቃሚ እንዲተላለፍ እየተደረገ ያለን ነዳጅ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር መላክ እየተለመደ መጥቷል።

ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት በአገሪቱ የነዳጅ ማደያ ተደራሽነት ችግር በስፋት ይስተዋላል። ከፍተኛ የትራፊክ እንቅስቃሴ ያላቸው እጅግ በርካታ ወረዳዎች የነዳጅ ማደያ እንደሌላቸው ይነገራል። በአንጻሩ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት የሌላቸው አንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ላይ ደግሞ ነዳጅ ማደያ በስፋት እየተገነባ መሆኑ ይገለጻል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በነዳጅ ግብይት የትርፍ ህዳግ በየጊዜው በማይስተካከልባትና ይህን ተከትሎ ባለነዳጅ ማደያዎች ሁሌም ቅሬታ እያነሱ፣ ይህም ለነዳጅ ማደያ መሰረተ ልማት አለመስፋፋት ዋና ችግር መሆኑ እየተገለጸ ባለበት ሁኔታ በእነዚህ አካባቢዎች የነዳጅ ማደያ በስፋት እየተገነባ ነው። የክልል መንግስታት በነዳጅ ማደያ ግንባታ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች የመሬትና የመሳሰሉትን ማበረታቻዎች በማድረግ በነዳጅ ማደያ ተደራሽነት ላይ በትኩረት እንዲሰሩ ጥሪ እየቀረበ በአንጻሩ ብዙም የትራፊክ እንቅስቃሴ በሌላባቸው በተወሰኑ የአገሪቱ ጠርፍ አካባቢዎች የነዳጅ ማደያዎችን በስፋት እየተገነቡ ናቸው።

ይህ ለምን ሆነ ተብሎ ሲጠየቅ ነገሩ ወዲህ ነው እየተባለ ነው። ነገሩ "ይሄ ሙጃ አጨዳ ዱባ ለመስረቅ ነው" የሚለውን አባባል ያስታውሳል። ይህን ያህል ኢንቨስትመንት በእነዚህ ጠርፍ አካባቢዎች ስራ ላይ ማዋል በእርግጥም የሙጃ አጨዳው አይነት ነው። ማደያዎቹ እየተገነቡ ያሉት ነዳጅ በኮንትሮባንድ ወደ ጎረቤት አገሮች ለማሻገር ነው እየተባለ ነው። የሚገርም አፍራሽ ሂሳብ ነው።

ደግነቱ መንግስትም በዚህ ላይ ነቅቷል፤ ነብር አያኝ በሉ ብሏል። ለአካባቢው የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ታውቆ ያ መጠን እንጂ በተከፈተው ማደያ ሁሉ ነዳጅ እንደማያስገባ አስታውቆ እየሰራ ነው። የህገወጦቹ ተግባር ግን አሁንም በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል።

መንግስት በቅርቡ የሚያደርገው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ አሰራር በነዳጅ ዋጋ ላይ ተጥሎ የነበረውን ድጎማ ቀስ በቀስ በማንሳት የነዳጅ ዋጋው በዓለም ገበያ ዋጋ መሰረት እንዲከናወን ሲያደርግ በነዳጅ ላይ የሚታዩት እነዚህ ህገወጥ ተግባሮች ሊቆሙ እንደሚችሉ ይጠበቃል። እዚያው ድረስ ግን ችግሩ ግዙፍ አገራዊ ችግር እንደመሆኑ ቁጥጥርና ክትትሉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

# ዓለም አቀፍ



## ለመጀመሪያ ጊዜ ለዋይት ሀውስ ጥቁር ሴት ቃል አቀባይ ተሾመች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ካሪን ጃንፒሬ የመጀመሪያዋ ጥቁር፣ ሴት፣ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ቃል አቀባይ ሆና በፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ተሰይማለች።

ካሪን ጄን-ፒይር የመጀመሪያዋ ጥቁር፣ ሴት፣ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ቃል አቀባይ ሆና በፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ተሰይማለች።

የ44 ዓመቷ ካሪን ቦታውን የምትረከበው ከጄን ሳኪ ነው። ከቀጣዩ ሳምንት በኋላ ከዋይት ሀውስ ዘገባ ለሚሠሩ ጋዜጠኞች መረጃ መስጠት ትጀምራለች።

ጄን ሳኪ ግራ ዘመሙ ኤምኤስኤንቢሲ ውስጥ በቅርቡ ሥራ እንደምትጀምር ተገልጿል።

ቦታዋን የምትረከበውን ቃል አቀባይ "በሥነ ምግባር የታነጸች ድንቅ ሴት" ስትል ገልጻለች።

"የራሷ የአሠራር ስልት አላት። ድንቅና የላቀ ችሎታዋን እንደምታሳይ አልጠራጠርም" ስትለም አክላለች።

የዋይት ሀውስ ቃል አቀባይ የአሜሪካ መንግሥት ፊት ሆኖ ለአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም ለመላው ዓለምም ይታያል።

ማንኛውም ፖለቲካዊ ቀውስ ወይም ብሔራዊ አደጋ ሲከሰት ቀድመው የሚታዮት እነዚህ ቃል አቀባዮች ናቸው።

ቃል አቀባዮች ፖሊሲ ባያረቁም አንድ የአሜሪካ አስተዳደር በሕዝቡ ዘንድ በምን መንገድ እንደሚታይ ይቀርጻሉ።

የባይደን አስተዳደር እስከ ዛሬ ድረስ በፖለቲካው መድረክ ገሸሽ የተደረጉ ጥቁር ሴቶችን በማሳተፍ ቀጥሏል።

ምክትል ፕሬዝዳንቷ ካሚላ ሐሪስ፣ የአገር ውስጥ ፖሊሲ ካውንስል ቃል አቀባይ ሱዛን ራይስ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ኬታንጂ ብራውን ጃክሰን፣ በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር ሊንዳ ቶማስ ግሪንፊልድን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

ካሪን ጄን-ፒይር ከዚህ ቀደም በኤምኤስኤንቢሲ ተንታኝ ነበረች።

በፖለቲካው የሁለት አሥርታት ተሞክሮ አዳብራለች።

በፍሬንች ካረቢያና ማርቲኒኪው ደሴት ተወልዳ ኒው ዮርክ አድጋለች። በኦባማ አስተዳደር ቁልፍ ቦታ ከነበራቸው አንዷ ናት።

እአአ በ2016 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ሲካሄድ ሙቭኦን የተባለው ብሔራዊ ንቅናቄ ቃል አቀባይ ነበረች።

ባይደን ካሚላ ሐሪስን ምክትላቸው አድርገው ከመረጡ በኋላ በቃል አቀባይነት ሠርታለች።

የፊታችን ጥቅምት በአሜሪካ የአስተዳደር አጋማሽ ምርጫ ይካሄዳል። ይህም ባይደን ፕሬዝዳንት ሆነው የሚቀጥሉበት ዓመታት በምን አቅጣጫ እንደሚጓዙ ይወስናል።



## ሩሲያ የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ አገሯ እንዳይገቡ አገደች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳን ወደ አገሯ እንዳይገቡ እገዳ መጣሏን ገልጻለች።

ከጠቅላይ ሚኒስትር ኪሺዳ በተጨማሪም በርካታ የጃፓን ባለስልጣናት ወደ ሞስኮ መግባት እንዳይችሉ ማዕቀብ ተጥሎባቸዋል ሲል ሮይተርስ ዘግቧል።

ሩሲያ በጃፓን ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ እቀባውን ያስተላለፈችው አሜሪካ እና የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ በሩሲያ ላይ ከ6 ሺህ በላይ የተለያዩ ማዕቀቦችን ማስተላለፋቸውን ተከትሎ ነው።

ዩክሬን የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ጦርን እቀላቀላለሁ ማለቷን ተከትሎ ሩሲያ በኪቭ ልዩ ዘመቻ በሚል ይፋዊ ጦርነት መጀመሯ ይታወሳል።

ሩሲያ ጎረቤቷ ዩክሬን ኔቶን እቀላቀላለሁ ማለቷን ተከትሎ ከፈረንጆች የካቲት 24፤ 2022 ጀምሮ ወታደራዊ ዘመቻ ማካሄድ መጀመሯ ይታወቃል።

በየሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት ከ6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች አገራቸውን ለቀው ወደ ጎረቤት አገራት ለመሰደድ እንደተሰደዱም ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት ያወጣው ሪፖርት ያመለክታል።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ እየወሰደች ያለውን ወታደራዊ እርምጃ ከጅምሩም ቢሆን የተቃወሙት ምዕራባውያን፤ ሩሲያን ያዳክማሉ ያሉዋቸው ማዕቀቦች ሲጥሉ እየተስተዋሉ ነው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት(ተመድ) ጠቅላላ ጉባኤ ባደረገው ስብሰባ ሩሲያ ዩክሬንን መውረሯን የሚያወግዘውን የውሳኔ ሀሳብ በአብላጫ ድምጽ ማጸደቁም እንዲሁ የሚታወስ ነው።

የተመድ ጠቅላላ ጉባኤም ሩሲያ ተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ እንድትታገድ ያደረገ ሲሆን ሩሲያም ይህን ተከትሎ ከም/ቤቱ አባልነት መውጣቷን ማስታወቋ ይታወሳል።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ስሜ ማን ነው?

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

ወርሃ መስከረም ውስጥ ነው፤ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምዝገባ የሚያደርጉበት ወቅት። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት በትምህርት ቤት ቅጥር ጊቢ ውስጥ የተገኘ የበጎፈቃድ ሰራተኛ ወጣት በአርሶአደሮች አካባቢ ባለ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ወላጆቻቸው ሊያስመዘግቧቸው የቀረቡትን ተማሪዎችን እየመዘገበ ነው። የሚመዘግባቸው ተማሪዎችን ስም፣ እድሜ፣ የቀደመ የክፍል ደረጃ፣ ወዘተ እየጠየቀ ይመዘግባል። አንዱ ተመዝግቦ ሲያልቅ ሌላኛው እየተከተለ ምዝገባው እየተከናወነ ነው። አስመዝጋቢው ቤተሰብ ማስረጃውን አቅርቦ ልጁን በስሙ ከማስመዝገብ ባለፈ፤ ለምን ልጃችሁን እከሌ አላችሁት የሚል ጥያቄ የለም። የወላጆች መብት ነውና ወላጆች ይዘውት የቀረቡትን ስም መመዝገብ የመዝጋቢው ግዴታ ስለሆነ።

ጥያቄው ግን በመዝጋቢው በጎፈቃደኛ ወጣት አእምሮ ውስጥ ግን ይመላለሳል። አንዳንዱን ስም ሲሰማ “ለምን ወላጆች ልጃቸውን እከሌ አሉት?” ብሎ ራሱን ይጠይቃል። እያንዳንዱን ወላጅ እየጠየቀ እንዳይረዳ ሰዓቱ አይፈቅድለትም፤ በጥድፊያ እየተከናወነ የሚገኝ ምዝገባ ነውና። አንዳንዱ ስም ሆን ተብሎ ከአባት ጋር እንዲስማማ ሆኖ የወጣ ይመስላል፣ አንዳንድ ስም ደግሞ የአንድን ወቅት አገራዊ ሁኔታ ታሳቢ አድርጎ የወጣ፣ አንዳንዱ ደግሞ የሆነን የጭንቅ ወቅት አመላካች ይመስላል ሌላው ደግሞ ዛሬን አሻግሮ ነገን በተስፋ መመልከትን። ብዙ ስም፣ ብዙ ተስፋ፣ ብዙ መልእክት።

ስንቶቹ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ስለስማቸው ጠይቀው መረዳት ያላቸው መሆኑን እርግጠኛ መሆን ባንችልም በልማድ እንደምናውቀው ብዙ ሰው ቤተሰቡ ያወጡለትን ስም ትርጉም ጠይቆ የመረዳትና ለሌሎች ሰዎችም የማስረዳት ልማድ አለን። በስም ትርጉሙ ደስተኛ መሆኑን የሚገልጽ እንዲሁም ሚያዝንሰው ሊገጥመን መቻሉም አያጠያይቅም። በስማቸው ደስተኛ ያልሆኑ ስማቸውን እስከማስቀየርም ድረስ የደረሰ ስራን ሊሰሩ እንደሚችሉም እንረዳለን፤ በተጨባጭ የሚገጥመንም ስለሆነ።

የተማሪዎቹ ምዝገባ እንደቀጠለ አንድ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ከእናቱ ጋር ሊመዘገብ የበጎፈቃድ መዝጋቢው ፊት ወረፋው ደርሶት ቀረበ። እናቱ የልጁን ስም ተናገረች፤ ታዳጊውም በመነጫነጭ “እማ በዚህ ስም መጠራት አልፈልግም ብዬሽ የለም እንዴ፤ አዲስ አመት መጥቶ ትምህርት ቤት ስትመዘገብ እንቀይረዋለን ብለሽኝ ነበር እኮ?” አለ። እናትም ደጋግመው በማስረዳት የደከመ በሚመስል ድምጸት “ልጄ ልክ ነህ፤ ግን ከበደኝ። ደጋግሜ እኮ አስረዳሁህ፤ ለምን አትረዳኝም። እኔ ስምህን መቀየር አልፈልግም፤ በጠራሁህ ጊዜ ትርጉም የምሰጥህ በዚሁ ስምህ ስጠራህ ነው። የእኔ የእናትህን ሃሳብ መቀበል ካልቻልክ በቃ እኔ ስሞት ራስህ ታስቀይረዋለህ” ብለው ተናገሩና ከአይናቸው እምባ ዱብ አለ። ልጅም ደነገጠ፤ በአቆሙ ጸንቶ “እንግዲያውስ በዚህ ስም የምታስመዘግቢኝ ከሆነ ትምህርት አልማርም እንድታውቂው” ለማለት አስቦ የእናቱን እምባ ሲያይ አፉ ላይ አድርሶ መለሰው። መዝጋቢው እናት ፊት ላይ ያየው የስሜት መረበሽ ተጋባበትና ተረበሸ። መዝጋቢውም ስሙን ጠየቀ። ስሙ በህይወቱ ውስጥ ስላለው ስሜት። ከመደበኛ ስሙ በተጨማሪ በህይወት ጉዞው ስለወጡለት አያሌ የግብር ስሞች ሁሉ አሰበ።

በዚህ የምናብ ታሪካችን ውስጥ ያገኘናቸው እናትና ልጅ በስም ጉዳይ የጀመሩት ክርክር መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ለራሳችን አስበን እንለፈው። ዋናው ፍሬ ነገሩ በዚህ ደረጃ የስም ጉዳይ የቤተሰብ መነጋገሪያም እስከመሆን ሊደርስ እንደሚችል እንድናስብ፤ በስም ውስጥ አልፎ የሚፈጠረው የስሜት ቁርኝት ቀላል አለመሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ግን እንረዳ። አንድ እውነተኛ ታሪክ አንስተን እንቀጥል። ሰላም የሚባል ስም የምትጠራ ነገርግን በስሟ ደስተኛ ያልሆነች ሴት አስታውሳለሁ። በእናትና አባት መካከል በነበረው ከፍተኛ ያለመግባባት ወቅት የተወለደች በመሆኑ በቤተሰቡ ውስጥ ያለው ሰላም ማጣት በእርሷ መምጣት ይፈታል ተብሎ በመታመኑ የወጣላት ስም ነው። ነገርግን እናትና አባት በልጅቱ ዘመንም ሰላም ኖሯቸው አልተመለከተችምና ሰላም በሌለበት ሰላም መባሏ፤ ሰላም ታመጣለች ተብላ ታምኖባት ባለመሆኑ አዝና ስሟን ጠላችው። አንባቢው

> **በተፈጥሮ በተቀበልነው ነገር ሳይ የቱንም ያህል ወጥተን ብንገባ ልንቀይረው እንደማንችል ተገንዝቦ መቀበል የተሰኘን ፖሲሲ ማስተናገድ አማራጭ የሴለው ነው**

ስሜ ማን ነው? ብሎ ራሱን እየጠየቀ በስምና በመሆን መካከል ያለውን እርቀት ስለማጥበብ እያሰበ አንድ ሁለት እንላለን። በቅድሚያ ...

**የተቀበልከው እና የሰራኸው**

በህይወት ጉዞ ውስጥ እንዲሁ የተቀበልናቸው እና እና በተግባር እራሳችን የሰራናቸው ወይንም ዘርተናቸው በቅለው ከእጃችን የሚገኙ ነገሮች አሉ። አንድ ልጅ አባቱንና እናቱን መርጦ አልተወለደም፤ እንዲሁ የተቀበለው እንጂ። አገር መርጦም የተወለደ የለም፤ እንዲሁ ሆኖበት ያገኘው እንጂ። የደም አይነቱን የመረጠ የለም፤ ከሆነ በኋላ አወቀው እንጂ።

የተቀበልከው እና የሰራኸው መካከል ስላለው ነገር የሚኖር የምልከታ ልዩነት ስማችንን ተሻግሮ የሚመጣ ጓዝ በአግባቡ ሰድረን ለማስቀመጥ ይረዳል። ልንቀይረው የማንችለው እንዲሁ የተቀበልነው ነገር ላይ የሚኖር መኮፈስ ሆነ መሸማቀቅ ትርጉም የለሽ ነው። በንጉሣዊ ስርዓት ወቅት የነበረው ማህበረሰባዊ መስተጋብር በተቻለው መጠን ከንጉሳዊ ስርዓቱ ጋር በደም ለመገናኘት መሞከር የተለመደ ነበር። የዘር ሃረግን ጠምዝዞም ቢሆን እንደምንም ከንጉሳዊ ስርዓት ውስጥ ራስን ለመጨመር መሞከር የሚስተዋልበት ልፋት። ወደ መሪነት መምጣት የሚፈልጉ ደግሞ የሚሄዱበት እርቀት ሩቅ የሆነ።

“ስምህ እንዴት ባህሪህ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል” በሚል ርእስ በbbc.com/future ላይ በሜይ 26፣ 2021 ላይ የወጣ ጽሁፍ ላይ እንዲሁ በነጻ ከወላጆች ልጆች የሚቀበሉት ስም ያለውን የሥነልቦና ተጽእኖ ባለሙያዎችን ዋቢ በማድረግ ያትታል። የሰዎች የራሳቸው ጥረት ነገራቸውን መወሰኑ እንዳለ ሆኖ ስምን ተከትሎ የሚመጣው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ግምት ውስጥ መግባት እንዳለበትም ይሞግታል። የሰዎች ስም አንዳንዴም ብሔርን እንዲሁም እምነትን አመላካች ስለሚሆን በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ጫና መፍጠሩ አይቀርም። በዚሁ ጽሁፍ ውስጥ የአሜሪካ መንትያ ህንጻዎችን ያወደመው የሽብር ጥቃትን ተከትሎ የአረብ ስም ያላቸው ሰዎችን ከስማቸው ተነስቶ የማግለል ወይንም የመፍራት አካሄዶች እንደተስተዋለ ይጠቅሳል።

በተፈጥሮ በተቀበልነው ነገር ላይ የቱንም ያህል ወጥተን ብንገባ ልንቀይረው እንደማንችል ተገንዝቦ መቀበል የተሰኘን ፖሊሲ ማስተናገድ አማራጭ የሌለው ነው። ልንቀይረው ከምንችለው ባሻገር ያለ በተግባር ስራችን ቀይረነው ልናይ በምንችለው አቅጣጫ ላይ ማተኮር ግን ተገቢነት ያለው። ሰርተን ከእጃችን ያደረግነው የላባችን ፍሬ ምን ሊሆን እንደሚችል መረዳት። ከቤተሰብ በተቀበልነው ማናቸውም ነገር ላይ የሚኖረን መመጻደቅ ሆነ እፍረት የዛሬ ኑሯችንን እንዳይጎዳ ማድረግ።

ስማችን የቱንም ያህል አስደሳችና ምርጥ ስም ቢሆን ግብራችን እንደስማችን ካልሄደ የፊደሎች ጋጋታ ከመሆን ያለፈ ሊሆን አይችልም። እንዲሁ ከተቀበልነው ከስማችን ባሻገር ትርጉም ያለው ነገር በተግባር ማከናወን የቻልነው የተግባር ህይወታችን ማሳያ እርሱ ነውና። የተግባር ህይወታችን ድምር ውጤት የህይወት ዘመናችን መከናወንም ነውና። አንባቢው በህይወት ዘመኑ በክንውን ዘመኑን መጨረስ ይፈልጋል፤ ጸሐፊውም እንዲሁ። አንባቢው አንዳች አቅም ሰው በመሆኑ ውስጥ ብቻ አለው፤ ሌላውም ሰው እንዳለው። አቅሙ ወደ ፍሬ ሊቀየር የሚችለው ስሙን ጠይቆ በስሙ ውስጥ ያለውን የትኛውንም መልእክት ቀንና ማታ ማሰብ ሳይሆን ዛሬ ላይ ወደ ውጤት የሚያደርስ ነገር መዝራት ሲችል ነው።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወደ ኋላ መቶ አመታትን በመሄድ በተሰራው ስራ እከሌ እኮ ከእኔ ወገን ነው የሚል አጉል ሽለላ፤ በሌላው አንጻር ደግሞ ከመቶ አመታት በፊት የተፈጸመን ጥፋት የሆነ ወገን አድርጎ እከሌ ላይ ድንጋይ ማንሳት ይስተዋላል። ይህ ስምን ጠይቆ በራስ ስም ትርጉም ላይ መደሰትና ማዘን ብቻ ያልሆነ ለዛሬው ተጨባጭ ህይወት አንዳች ፋይዳ የሌለው ነው። በተቀበልነው እና በሰራነው ላይ የሚኖር የተሳሳተ ትርጉም የሚፈጥረው ለራስ ስም አወጣጥ።

**ያወጡልህና ያወጣህላቸው**

ማርከስ አውሪሊስ የተባለ ሰው፤ “ማንኛውም የምንሰማው ነገር አስተያየት እንጂ ተጨባጭ መረጃ ሊሆን አይችልም፤ ማንኛውም የምናየው ነገር እይታ እንጂ ተጨባጭ እውነት ሊሆን አይችልም” በማለቱ ይጠቀሳል። ይህ አባባል የምንሰማውና የምናየውን ሁሉ ተቀብለን የምንወስደው እርምጃ ወደተሳሳተ ድምዳሜ ሊያደርሰን እንደሚችል የሚያሳይ ነው። በህይወት ጉዞ ውስጥ አስተውለነውም ይሁን ሳናስተውል ከምናደርጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ለሌሎች ስም ማውጣት ነው። የመዝገብ ስም ኖሯቸው ነገርግን የግብር ስም እናወጣላቸዋለን። ከመጠሪያ ስሙ ላይ የምንጨምረው የፍርደኝነት ስም። ገንዘብ በማባከን ካየነው “አባካኙ” ብለን ስም አውጥተን ባወጣነው ስም በውስጣችን እየጠራነው በአፋችን መደበኛ ስሙን አቆላምጠን እንጠራዋለን። በጾታዊ ግንኙነቱ አንዳች ክፍተት ካየንበት እድሜ ልኩን በዚያው መንገድ እየሄደ እየማገጠ እንደሚኖር ቆጥረን ስም እናወጣለታለን። በንግግሩ ውስጥ አንዳች ነገር መደነቃቀፍን ከፈጠረ የተፈጠረችውን መደነቃቀፍ አጉልተን በመሳል መጠሪያው እናደርጋለን።

የማህበራዊ ሚዲያ ገጾቻችን ስም የወጣላቸውን አያሌ ሰዎች አስተዋውቆናል። በአንዳች ነገር ጎድለው የተገኙ ሰዎች ከሆኑ መጠሪያቸው ያጎደሉት ነገር ሆኖ ሲሸከረከር ይውላል። “ምንም ኃጢአት የሌለበት ሰው የመጀመሪያውን ድንጋይ ይወርውር”ተብሎ ቢጠየቅ ሰው ሁሉ ወደራሱ ቢመለስ የማያደርገው የሚመስል፤ ነገርግን ቅጽበታዊ በሆነ ወሬን ከአንድ ጫፍ ወደሌላ ጫፍ የማጋባት ልማድ ይህን እያደረገ እናገኛለን። የአንድ ግለሰብ የግል ጉዳይና ሌሎች ነገሮችን መለየት እስካይቻል ድረስ የማህበራዊ ሚዲያ መወያያ ሆኖ እናስተውላለን። በህይወት መንገዳችን ላይ ፍጹም የሆነን እርምጃ ለመራመድ አስበን የምናደርገው ጉዞ ያለውን ፋይዳ እረዳለሁ፤ የጥንቁቅ ሰውነት ህይወት። እንደ ኃይማኖት አስተማሪ ሰው ሁሉ ለመልካም ነገር ሁሉ ራሱን እያዘጋጀ እንዲኖር አስተምራለሁ። ነገርግን የሰው ልጅ ፍጹም የሆነ እንከን አልባ የሆነን ኑሮ መኖር የሚችልበት አቅም ላይ አለመሆኑንም እረዳለሁ። የኃጢያት ስርየት ወይንም ኃጢያተኛ ነኝ ብሎ የቀረበን ሰው ይቅር ማለት ያስፈለገበት ምክንያቱም፤ ስለ ስርየትም መስዋእት ይሆን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር እንደመጣ የምናስተምረው ሰው በራሱ ወደ ፍጹምነት መድረስ ባለመቻሉ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታን ከጠየቀ ከፈጣሪው ይቅርታን ሊያገኝ ስለተገባው ነው።

የማህበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ ያለውን ምልልስ ስንመለከት ሁሌ ራሳችን እንከን አልባ ሌላኛውን ወገን ደግሞ በእንከን ውስጥ ውሎ የሚያድር አድርገን እናቀርባለን። እውነታው ግን ሰው ሁሉ ደካማም መሆኑ ነው፤ በሁላችንም ውስጥ ስህተት የሚገኝ መሆኑ ነው።

በመሆኑም ሰዎች ባወጡልን ስም ተደናግጠን ከጉዞ የምንገታ ከሆነ እኛም ጥፋተኞች እንሆናለን። ሰዎች ስለራሳቸው ጥፋት ሳይሆን ስለሌላው መመልከት የሚቀናቸው ሆነው በተገኙ ቁጥር ራሳችንን ጎድተን፤ ጊዜያችንን በማይገባ ሁኔታ ውስጥ ስናሳልፍ እናያለን።

ዛሬ ስሜ ማንነው ብለን በምንጠይቅበት ጊዜ ቤተሰቦቻችን ካወጡልን ስም ባሻገር ሰዎች ከሆነው



ተነስቶ ያወጡልንን ስም እንመልከት? በዚያስ ምን ያህል አእምሮችን ተይዞ ከጉዞችን ተስተጓጎልን። መስተጓጎል አስቀምጦን ከሆነ እንድናነሳ፤ ዝለን ከሆነ እንድንበረታ፤ ተስፋ ቆርጠን ከሆነ ተስፋችንን እንድናድስ፤ ተደብቀን ከሆነ እንድንወጣ ይገባል።

**መሻሪያው ሳይ ማተኮር**

በሰዎች ዘንድ ስላለው ስም አብዝቶ ከመጨነቅ ስለመሻሪያው ማሰብ የተሻለ ነው፤ እርሱም መልካሙን ስራ ማድረግ። ሰዎች ያወጡልን የቱንም ስም ቢኖር በክርክርና በሌሎች መንገዶች ለማጥፋት ከመሄድ በተግባር ስራ ማሸነፍ የተሻለው ነው። ሰዎች በሌብነት ስም ያወጡለት ሰው ሌባ አለመሆኑን ለማስረዳት ከሚደክመው ድካም ሌባ ሆኖ የተገኘ ከሆነ ከድርጊቱ መመለስ እንዲሁም በንጽህና መኖር ትክክለኛው መንገድ ነው። ሁልጊዜ በቅድሚያ ለራሳችን ታማኝ መሆኑ አስፈላጊ ነው። በጾታዊ ግንኙነት ችግር ውስጥ የገባ ሰው ሰዎች ስለ እርሱ ከሚሉት ነገር ይልቅ ትክክል መሆን አለመሆኑን ራሱ መበየን፤ ትክክል አይደለሁም በሚልበት አግባብ ላይ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ነው። ከትዳሩ ውጪ የሚሄድ ስህተቱን ተመልክቶ በፍጥነት የሚያደርገው መመለስ የተሻለ ነው የተበላሸ ስሙን ለማደስ በውሸት ጋጋታ ውስጥ ከመዋኘት። ስህተትን መቀበል ይዞት የሚመጣው አደጋ ቢኖርም ቢያንስ በራስ ደረጃ ስህተትን ተቀብሎ ለመፍትሔው መስራት የተሻለው ነው።

የህይወት ጉዞ አስደሳች የሚሆነው በሆነው እንጂ በተናገርነው ልክ አይደለም። ልንሆን የተገባውን ማወቅ፤ ልንሆን የተገባውን መሆን፤ ልንሆን የተገባውን እንዳንሆን የሚያደርጉ አንገትን ለሚያስደፉ ድምጾች አንገትን በመድፋት ምላሽ ከመስጠት ቀና ብሎ መመላለስ። ይህ ማለት ጥፋትን እያጠፉ እፍረት የለሽ መሆን ማለት ሳይሆን ያለፈውን አስተካክሎ ወደፊት በንጽህና የመራመድ ቀና ማለት ትርጉም ነው።

ወደ ማጠቃለያ ሃሳባችን ስንመጣ ደግመን ደጋግመን ስማችንን እንጠይቅ። ስሜ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ቤተሰብ የሰጠንን ስም ትርጉም መነሻ አድርገን በስሙና በእኛ ወቅታዊ ሁኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ተመልክተን ልዩነቱን የሚያጠብ የተግባር ሰውነትን ስናስቀድም ትጋት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ በሌላው ጫማ ውስጥ ራስን መጨመር፣ ስኬት ማለት አንድ ነገር ብቻ አለመሆኑን፣ ከሰው ጋር በሰላም መኖር ያለውን ቦታ፣ ወዘተ እንረዳለን። የተሰጠን ስም ትልቅን ተስፋ አመላካች ቢሆን ወደታየው ተስፋ ለመድረስ የሚገባውን ዛሬ ላይ ማድረግ ከተቀበልነው ስም በላይ ለውጤት አቅም ይሆነናል።

በትላንት ጉዟችን ላይ ተመርኩዘው ሰዎች ያወጡልን ስም ዛሬ ላይ ወደፊት ከመራመድ አቁሞን እንደሆነ ሰው ሁሉ ስህተት እየሰራ የሚኖር፣ የፍጽምና አቅም የሌለው መሆኑን ተረድተን፣ ፈጣሪ የምንሻውን መልካም የመሆንን አቅም እንዲያበዛልን እየለመንን ወደፊት ለመራመድ ስለመነሳት ተመለከትን። ሰዎች ምንም ቢደረግ የሚሉት አያጡምና በሰዎች አስተያየት ላይ የተመሰረተን የህይወት አቅጣጫን ከመምረጥ መታገስ እንዳለብን ይህን አልን።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የቡናው ዘርፍ ደጀን- ለአራት አስርት ዓመታት የዘለቀ ሙያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ቡና በአገሪቷ ካሉ የግብርና ምርቶች መካከል ቀዳሚው የኢኮኖሚ ምንጭ ነው። ባለፉት ዓመታትም ይሁን በአሁን ወቅት ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታና ማገር በመሆን የላቀ ድርሻ እያበረከተ ይገኛል። በተለይም አገሪቷ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በውጭ ምንዛሪ እጥረት እየተፈተነች ባለችበት በዚህ ወቅት ከቡና ምርት የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

‹‹የኢኮኖሚዋ ዋልታ ቡና ቡና…›› የተባለለት የኢትዮጵያ ቡና ከቀደመው ጊዜ በበለጠ በአሁን ወቅት በዓለም ገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እየሆነ በመምጣቱ አገሪቷም የዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደቻለች በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ያነሳሉ። ከቡና ምርት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ቡና አምራች በሆነው አርሶ አደር ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት የግድ መሆኑንም ባለሙያዎች አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ።

የዕለቱ እንግዳችንም በቡና ልማት እንዲሁም በግብይት ሰፊ ልምድ ያላቸው፤ የትምህርት ዝግጅታቸውም ከግብርናው የተዋደደና በሥራ ዓለም ዘመናቸው ሙሉ በቡና ልማት፣ ዝግጅትና ግብይት ላይ በማድረግ አንቱ የተባሉ አንጋፋ ባለሙያና የዘርፉ አማካሪ ናቸው። የሥራ ዓለምን ‹‹ሀ›› ብለው ሲቀላቀሉ ጀምሮ ስለ ቡና ጠርቀም ያለ ዕውቀት ከማከማቸታቸው ባለፈ ለዘርፉ ጥልቅ ፍቅር ያላቸው ናቸው።

እንግዳችን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ኦሮሚያ በምስራቅ ወለጋ ዞን ጊዳ አያና ወረዳ ተወልደው አድገዋል። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም እንደማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ በአቅራቢያቸው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በሻምቡ፣ በአምቦና በነቀምት ተከታትለዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደብረ ዘይት እርሻ ኮሌጅ በመግባት በግብርና ዘርፍ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የእርሻ ኮሌጅ ትምህርታቸውን አጠናቀው የመጀመሪያ የሥራ ቅጥራቸውን በቀድሞው ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ያደረጉት የዕለቱ እንግዳችን የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ደሳለኝ ጀና ናቸው።

አቶ ደሳለኝ ሰፊ አበርክቶ ያላቸውና ዛሬም ድረስ ሙሉ ጊዜያቸውን ለሙያው በመስጠት እያገለገሉ ያሉ ሲሆን በተለይም በቡና ልማትና ግብይት ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ለአርሶ አደሩና በዘርፉ ለተሰማሩ አባላት በሙሉ በማካፈል ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በሙሉ አቅማቸው እያገለገሉ ይገኛሉ።

በቀድሞ አጠራሩ በሲዳሞ ክፍለ አገር ይርጋለም ከተማ አካባቢ የቡና ልማት ሥራን የጀመሩት አቶ ደሳለኝ፤ በተሰማሩበት ሙያ ውጤታማ ሥራ መሥራት በመቻላቸው በአካባቢው በኃላፊነት ቦታ ላይ ሆነው አገልግለዋል። በወቅቱም አርሶ አደሩ ቡናን በስፋት ማምረት እንዲችልና ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ህብረት ሥራ ማህበራትን በማቋቋም ጭምር የጎላ ድርሻ እንደነበራቸው ይናገራሉ።

1985 ዓ.ም በአዲስ አወቃቀር ክልል በተመሰረተበት ወቅትም በየክልሉ የቡናና ሻይ ቢሮዎች የተከፈቱ ሲሆን በጊዜው ለኦሮሚያ ክልል ቡናና ሻይ ቢሮ ግንባር ቀደም ሠራተኛ ሆነው ተመድበዋል። በወቅቱም ቢሮዎችን በማደራጀት እንዲሁም ባለሙያዎችን ከየአቅጣጫው በመመልመል ቢሮው የተፈለገውን ሥራ መሥራት እንዲችል አድርገዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የቡናና ሻይ እንዲሁም የግብርና ቢሮ በሚዋሀዱበት ጊዜም በህብረት ሥራ ኦዲተሮች አስተባባሪ በመሆን አገልግለዋል።

የህብረት ሥራ አገልግሎት ዘርፍ ከአንድ ክፍል በመውጣት ወደ ቢሮ ሲያድግም የኦሮሚያ የህብረት ሥራ ቢሮ የኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ኃላፊ ሆነው የተመደቡት አቶ ደሳለኝ፤ በወቅቱ በኦሮሚያ ክልል ዞኖች ውስጥ የሚገኙ የህብረት ሥራ አይነት አደረጃጀት ያላቸውንና በማናቸውም ዘርፎች የተሰማሩ አርሶ አደሮችን በህብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀት ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋል። በኦሮሚያ ክልል በሚመረቱ ቡናን ጨምሮ በሌሎች ምርቶች ዙሪያ እንደየአይነታቸው ማህበራትን በማደራጀት አርሶ አደሩ ምርታማ መሆን እንዲችልና ከዘርፉም ተጠቃሚ እንዲሆን አድርገዋል።

በተለይም በቡና ምርት ላይ የተሰማሩ አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራትን ውጤታማ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራት መከናወናቸውን ያነሱት አቶ ደሳለኝ፤ ወቅቱ የዓለም የቡና ገበያ እያሽቆለቆለ የመጣበት ወቅት በመሆኑ የህብረት ሥራ ማህበራት አባላቱን ለመታደግ በሚል ቡናን በአገር ውስጥ ከመሸጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ ማቅረብ መጀመሩን አስታውሰዋል። ለዚህም ማህበራቱን በአንድ በማዋሃድ የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒዮንን በመመስረት በዩኒዮን የተዋሃዱት ማህበራትም ቡናን በስፋት ማምረት እንዲችሉና በስፋት ያመረቱትን ቡናም ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉ የማድረግ ትልቅ ኃላፊነትን ተወጥተዋል።



አቶ ደሳለኝ ጀና

በዚህ ወቅትም ህብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀትና በማጠናከር ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው አቶ ደሳለኝ፤ በ34 ህብረት ሥራ ማህበራት የተጀመረው የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒዮን ምክትል ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል። ዩኒዮኑም በአንድ ዓመት ውስጥ እንደታሰበው ቡናን ወደ ውጭ ገበያ መላክ በመቻሉ የመጀመሪያው ዩኒዮን በመሆን የተፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። ውጤቱን በማየትም ዩኒዮኑን የሚቀላቀሉ ማህበራት በየዓመቱ ቁጥራቸው እየጨመረ ሄዶ ዛሬ ላይ ከአምስት ሚሊዮን የሚልቁ አርሶ አደሮችን ማቀፍ ችሏል።

በወቅቱ የዓለም ገበያን በማጥናት የተፈጥሮ የሆነና የተመዘገበ ቡና የተሻለ ዋጋ የሚያወጣ መሆኑን መረዳት በመቻላቸው አስፈላጊውን ሂደት ሁሉ በማለፍ ዩኒዮኑ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ቀዳሚ ከመሆኑም ባለፈ የተፈጥሮ ቡና ሰርተፊኬት በማግኘትም የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒዮን በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዩኒዮን እንዲሆን አስችለዋል።

በመሆኑም ቡናው የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣና ገበሬውም ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን እንዲችልና አገሪቷም ከዘርፉ በምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ተጠቃሚ እንድትሆን አስችለዋል። ከዚህ በተጨማሪም ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ዩኒዮኑ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የልማት ሥራዎችን መሥራት የቻለ መሆኑንና በዚህም ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው መሆኑን ያስታወሱት አቶ ደሳለኝ፤ ዩኒዮኑ ከሠራቸው የልማት ሥራዎች መካከል መንገድ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ 100 የሚደርሱ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 30 የሚደርሱ የጤና ተቋማት፣ የቡና ማጠቢያና መቀሸሪያ እጥረት ባለባቸው ክልሎችም እንዲሁ 50 የሚደርሱ የቡና ማጠቢያና መቀሸሪያ ጣቢያዎችን ማቋቋም እንደቻሉ ለአብነት አንስተዋል።

አቶ ደሳለኝ፤ በዩኒዮኑ ብቻ ለ18 ተከታታይ ዓመታት በምክትል ሥራ አስኪያጅነት ያገለገሉ ሲሆን በዘርፉ ሰፊ ዕወቀትና ልምድ ማካበት ችለዋል። ያካበቱትን ዕውቀትም ወደ ሥራ በመለወጥ በዘርፉ ሰፋፊ ኢንቨስትመንቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ የቡና ምርት በአገሪቱ ውጤታማ እንዲሆንና አምራቹም ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ትልቅ አበርክቶን አድርገዋል። አሁንም እያደረጉ ይገኛሉ። ለበረከተው አገልግሎታቸውም በዘርፉ መቆየት መቻላቸው ቀዳሚው ምክንያት ቢሆንም የትምህርት ዝግጅታቸውም እንዲሁ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

ከግብርና ኮሌጅ ትምህርታቸው ባለፈም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግና በፋይናንስ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። ለትምህርት ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳም ከአገር ውስጥ ባለፈ በህንድ አገር በሩራል ዴቨሎፕመንት፣ በእስራኤል አገርም እንዲሁ የሩራል ኢንዱስትሪያላይዜሽን ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን ኮፕሬቲቭ ኮሌጅ በአገሪቱ ያልነበረ በመሆኑ በኬኒያ የኮፕሬቲቭ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ትምህርታቸውን ተከታትለው አድቫንስ ዲፕሎማ አግኝተዋል።

‹‹የተከታተልኳቸው የትምህርት ዝግጅቶች በአብዛኛው ከግብርና እንዲሁም ከዴቨሎፕመንት ጋር የተቆራኙ ነው›› የሚሉት አቶ ደሳለኝ፤ ሌላ መስሪያ ቤት የማያውቁና በጠቅላላው ከአራት አስርት ዓመታት በላይ በቡናና ሻይ መስሪያ ቤት አገልግለዋል። ልምድና ዕውቀታቸውን በቡና ልማትና ግብይት ዘርፍ በማተኮር በተለይም በቡና ምርትና ንግድ ላይ ለተሰማሩ አርሶ አደሮችና ነጋዴዎች ያላቸውን ከፍተኛ ልምድ በማካፈል ዘርፉን እየደገፉ ይገኛሉ።

ምንም እንኳን ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ቡና ከቤት ፍጆታ አልፎ ለገበያ የሚወጣ ባይሆንም ቡናን በአካባቢያቸው እየተመለከቱ ያደጉት አቶ ደሳለኝ፤ ነብስ ካወቁበት ጊዜ ጀምረው በዘርፉ መሰማራት በመቻላቸው ለቡና ልማት ጥልቅ ፍቅር አላቸው። ታዲያ በከፍተኛ ልምዳቸውና በትምህርት ዝግጅታቸው ዘርፉን ጠንቅቀው ቢያውቁትም ከግል ጥቅማቸው በበለጠ በስፋት ለሚያመርተው አርሶ አደር ሙሉ ጊዜያቸውን ተጠቅመው ዕውቀታቸውን በማካፈል አገር ከዘርፉ ማትረፍ እንድትችል ያቅማቸውን አድርገዋል።

ከራስ ጥቅም ይልቅ አርሶ አደሩ የሚጠቀምበትና ሥራ በመሥራት ሙሉ ጊዜያቸውን ያሳለፉት አቶ ደሳለኝ፤ በተለይም በውጭው ዓለም ኢትዮጵያ ያላትን ገጽታ መቀየር የሚቻለው ሰፊው ህዝብ መለወጥ ሲችል እንደሆነ ያምናሉ። ለዚህም ዋናውና ሰፊ ድርሻ ያለው ገበሬው በመሆኑ በተለይም ቡና አምራች ገበሬው ምርቱን በስፋትና በጥራት አምርቶ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆንና አገርም ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንድትሆን ቁጭት ያላቸው መሆኑን ያነሳሉ። በዚሁ ቁጭታቸው ልክም አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ እያደረጉ ይገኛሉ።

በአሁን ወቅትም ለአራት አስርት ዓመታት ከሰሩበትና ከፍተኛ ልምድ ካካበቱበት ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከጡረታ አስቀድመው በመውጣት የቡና ላኪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት በመሆን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሰማርተው እያገለገሉ ይገኛሉ። በዘርፉ የተሰማሩ የተለያዩ አካላትንም እንዲሁ ካላቸው ልምድና እውቀት በመነሳት ያማክራሉ። በተጨማሪም የተቆላ ቡና በማዘጋጀት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እያቀረቡ የሚገኙ ሲሆን በዘርፉም አስር ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ደረጃ ታዋቂና ተወዳዳሪ ሆኖ እስካሁን ባለው ሂደትም በከፍተኛ ዋጋ መሸጥ እንዲችል ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒዮን መመስረቱ አንዱ መሆኑን ያነሱት አቶ ደሳለኝ፤ ለዚህም ትልቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑንና የዩኒዮኑ መስራች በመሆን ለ18 ዓመታት ማገልገል በመቻላቸውና ባስመመዘገቡት ውጤትም እጅጉን ደስተኛ እንደሆኑ ይናገራሉ።

ከግል ስኬታቸው በበለጠ ያላቸውን ልምድና ዕውቀት ለብዙሃኑ በማካፈል ቡና አምራች አርሶ አደሮች ምርታማ ሆነው ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ ቡናን በብዛትና በጥራት ማቅረብ እንዲችሉ ማድረጋቸው ትልቁ ስኬታቸው እንደሆነም አጫውተውናል። አያይዘውም በሥራ ዓለም ምንም የሚቆረቁራቸውን ሥራ ያልሰሩና ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ በሙሉ ተጠቅመው ብዙሃኑንና አገርን ለመጥቀም ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ መሆናቸውን ሲናገሩ የነበራቸውን በራስ መተማመን የፊት ገጽታቸውም በግልጽ ይናገር ነበር።

ከቡና ልማት እስከ ዓለም ገበያ ድረስ በዘርፉ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ያካበቱት አቶ ደሳለኝ፤ ቡና በሚያመርቱና በሚሸምቱ አገራት ተዘዋውረው የተለያዩ ጥናት ማድረግ በመቻላቸው አገሪቷ ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን እንድትችል እየሰሩ ይገኛሉ። በተለይም በአሁን ወቅት በአገሪቱ ያለው ፖሊሲ ማሠራት የሚችል በመሆኑ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ በመጠቆም ቡና በዓለም ገበያ የሚሸጥ ምርት እንደመሆኑ ምርቱ ለኢትዮጵያ እጅጉን አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ አሁንም ይሁን በቀጣይ አጭር ጊዜ ቡናን የሚተካ ምርት የሌለ እንደሆነ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል። ረጅም መንገድ ከቡና ጋር በመጓዝ ከቡና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለመጠቀም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ከልባቸው ሆነው በእውነት መሥራት እንዳለባቸውም አመላክተዋል።

በቅርቡም በአሜሪካን አገር በየዓመቱ በሚካሄድ የቡና ኤግዚብሽን ላይ ከተለያዩ ዓለም አገራት የቡና ተመራማሪዎችን ጨምሮ ቡና አምራቾችና እሴት ጨምረው ለገበያ የሚያቀርቡ አገራት በተገኙበት 100 የሚደርሱ ቡና ላኪዎች ተሳታፊ መሆን ችለዋል። በኤግዚብሽኑ ላይ ተሳታፊ ከሆኑት መካከልም አብዛኞቹ ወደ ውጭ ተጉዘው የማያውቁ ቡና ላኪዎች በመሆናቸው አጋጣሚው መልካም ነው። ላኪዎቹ ቡና ገዢ ከሆኑ አገራት ጋር ተገናኝተው የገበያ ትስስር መፍጠር የቻሉ ሲሆን ውጤቱም በቀጣይ የሚታይ እንደሆነ አመላክተዋል።


የቡና ዘርፍ ችል የሚባልና የሚተው አለመሆኑን የገለጹት አቶ ደሳለኝ በቀጣይም ሌሎች በርካታ የሚሰሯቸው ሥራዎች ቢኖሩም ከዘርፉ ሳይለዩ ከኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ፕሬዘዳንትነት ባለፈ የዘርፉ አምባሳደር መሆንና የጀመሩትን የተቆላ ቡና በአገር ውስጥና በውጭ ገበያ የማቅረብ ሥራ አጠናክረው የመቀጠል ዕቅድ አላቸው። እኛም ዕቅዳቸው እንዲሰምር በመመኘት አበቃን።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የሙከጡሪ-ኮከብ መስክ እና ኮከብ መስክ-ዓለም ከተማ የመንገድ ሥራ

መሳኩ ሔርሴ




የመንገድ መሰረተ ልማት ‹‹መንገድ ይወስዳል መንገድ ይመልሳል›› ከሚባለውም በላይ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን የሚያስገኝ ልማት ነው። የዜጎችን የዕለተ ዕለት እንቅስቃሴ ከማሳለጥ ባሻገር፤ የአገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ፣ አንድን ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በባህል፣ በቋንቋ እና በሌሎችም ማህበራዊ እሴቶች ለማስተሳሰር፤ የተሻለ አካባቢ ለመፍጠር፣ አገርን ለማበልጸግ የጎላ ሚና አለው። ይህን ታሳቢ በማድረግ የሚከናወን የመንገድ ሥራ ለትውልድ ሽግግርም እንዲሁ ይጠቅማል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት ክልሎችን ከክልሎች፤ ዞኖችን ከዞኖች፣ ከተሞችን ከከተሞች ጋር የሚያገናኙ አለፍ ብሎም ከጎረቤት አገራት ጋር የሚያገናኙ የመንገድ መሠረተ ልማት በማከናወን ግንባታው ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቧ ይታወቃል።

አሁንም የመንገድ ሥራው ተጠናክሮ በርካታ የመንገድ ፕሮጀክቶች ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ባለፉት ጊዜያቶች ከተገነቡ መንገዶች መካከል አንዳንዶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ የተጠናቀቁ ቢሆኑም ከዚህ ቀደም ተገንብተው ወደ ስራ የገቡ እና አሁን በግንባት ሂደት ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግን በተባለላቸው ጊዜ የመጠናቀቅ ችግር የሚስተዋልባቸው እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በርካታ ፕሮጀክቶች በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ። የዛሬው የመሰረተ ልማት አምዳችን በግንባታ ላይ ከሚገኙትና ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው ተስፋ ከሚደረግባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች አንዱ በሆነው የሙከጡሪ- ኮከብ መስክ እና ኮከብ መስክ ዓለም ከተማ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። እነዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች የኦሮሚያ ክልልን ከአማራ ክልል ጋር የሚያስተሳስር ናቸው።

ለመንገዶቹ የግንባታ ስራ አመቺነት ሲባል በሁለት ኮንትራት ተከፍሎ እየተሰራ ሲሆን፤ ኮንትራት አንድ የሙከጡሪ-ኮከብ መስክ እና ኮንትራት ሁለት ደግሞ ኮከብ መስክ-ዓለም ከተማን ያካልላል። ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው ሙከጡሪ - ኮከብ መስክ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ግንባታ ግንቦት 15 ቀን 2009 ዓ.ም ነው የተጀመረው። የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ግብ ተቀምጦለት ነበር ወደ ሥራ የተገባው። ይህ ፕሮጀክት 59 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። የመንገድ ግንባታው በገጠር 10 ሜትር ፣ በቀበሌ 12 ሜትር፣ በወረዳ ደግሞ 21 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፣ መንገዱን ለመገንባት የሚስፈልገው ገንዘብ ሰባት መቶ ስልሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ብር ነው። ወጪው የተሸፈነው በኢትዮጵያ መንግስት ነው።

ግንባታውን እያከናወነ የሚገኘው ዓለም-አቀፉ የስራ ተቋራጭ ቻይና ሪልዌይ ቁጥር ሶስት ኢንጂነሪንግ ግሩፕ፣ የማማከሩን እና የቁጥጥሩን ስራ ደግሞ ኤልዳ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንት ከዳምራ ኮንሰልቲንግ ጋር በጥምረት እያከናወኑት እንደሚገኝ የአስተዳደሩ መረጃ ያመለክታል።

በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክቱ 40 ኪ.ሜ የሚሆን የአስፓልት ንጣፍ ስራው ተጠናቋል። አጠቃላይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ደግሞ 80 በመቶ ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክቱን ቀሪ ስራዎችን ጨምሮ የማጠቃለያ ስራዎችን ለመፈጸም በትኩረት እየተሰራ መሆኑንን እንዲሁም ለመንገድ ደህንነት የሚጠቁሙ የተለያዩ የትራፊክ ምልክቶችም በመመረት ላይ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በቅርቡ በማህበራዊ ድረ ገጹ(ፌስቡክ)ላይ ያሰራጨው ዘገባ አመላክቷል።

በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ የመጠናቀቅ ችግር ካጋጠማቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ይህ ፕሮጀክት መሆኑን እላይ በዘገባው ውስጥ ከተጠቀሱት መረጃዎች መረዳት ይቻላል። በ2012 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ እቅድ ተይዞለት የነበረ ይህ ፕሮጀክት በ2014 ዓ.ም 80 በመቶ አፈጻጸም ላይ ነው የሚገኘው።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን ወንድሙ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ለስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ ተሰጥቶታል። ለተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ምክንያት የሆነው ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዙ ችግሮች በማጋጠማቸው ነው። የመንገድ ግንባታ በሚካሄድበት አካባቢ የነበሩ ቤቶች እና ንብረቶች በወቅቱ አልተነሱም ነበር። የካሳ ክፍያ ተከፍሎአቸውም እንኳን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ሊነሱ አልቻሉም። የወሰን ማስከበር ችግሩ የተፈጠረው የግለሰብ ቤቶች ባለመነሳታቸው ብቻ አይደለም። የመብራት ምሰሶዎች፣ ትራንስፎርመሮች አለመነሳታቸው ጭምር ነው። እነዚህ ችግሮች ሥራ ተቋራጩ ሥራውን በወቅቱ አጠናቅቆ እንዳያስረክብ እንቅፋት ሆነውበታል። በመሆኑም ለተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት ግድ ሆኗል ብለዋል ዳይሬክተሩ።

> **ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ለስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ ተሰጥቶታል። ለተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ምክንያት የሆነው ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዙ ችግሮች በማጋጠማቸው ነው። የመንገድ ግንባታ በሚካሄድበት አካባቢ የነበሩ ቤቶች እና ንብረቶች በወቅቱ አልተነሱም ነበር**

ይህ ብቻም አይደለም። መጀመሪያ ላይ ከታሰበው ተጫማሪ ስራዎችም እንዲሰሩ ተደርጓል። መጀመሪያ ከነበረው ተጨማሪ ስራዎች መስራት ደግሞ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ ነው። ይህም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ ሌላው ምክንያት ነው። አሁን በተያዘው በጀት አመት መጨረሻ ድረስ ዋና ዋና ስራዎቹን ለማጠናቀቅ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ነው አቶ ሳምሶን ያብራሩት ።

የሙከጡሪ-ኮከብ መስክ እና ኮከብ መስክ-ዓለም ከተማ ፕሮጀክት አካል የሆነው ኮከብ መስክ-ዓለም ከተማ የመንገድ ፕሮጀክት 47 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያለው ሲሆን፣ በአስፓልት ደረጃ እየተገነባ ይገኛል። የግንባታ ወጪውም አንድ ቢሊየን ስድስት መቶ ዘጠና አምስት ሚሊየን ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ሲሆን፤ የግንባታው ወጪ በኢትዮጵያ መንግስት ሙሉ ለሙሉ ይሸፈናል።

የመንገዱ መነሻ ኮከብ መስክ ቀበሌ ሲሆን፣ መረሃ-ቤተ ወረዳ ዓለም-ከተማ ላይ ያበቃል።

ፕሮጀክቱ የመንገዱ ትከሻን ጨምሮ በወረዳ 21 ሜትር፣ በከተማ 15 ሜትር በገጠር ደግሞ 10 ሜትር የጎን ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ ነው በመገንባት ላይ የሚገኘው። በ2012 ዓ.ም ነው የተጀመረው። ይህ የመንገድ ፕሮጀክት መስከረም 8 ቀን 2015 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ግብ ተቀምጦለታል። መንገዱን እየገነባ የሚገኘው ቻይና እስቴት ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሊሚትድ ነው። የማማከርና ቁጥጥር ስራውን ደግሞ ቫሊዩ ኢንጂነሪንግ እያከናወነ ይገኛል። በእስካሁኑ የሥራ እንቅስቃሴ የዲዛይን ስራ፤ ቅየሳ ስራ፣ የአፈር ቆረጣ፤ ሙሌት፤ ጠረጋና ድልዳሎ ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝ የአስተዳደሩ ዘገባ ያመላክታል ።

በዚህ ፕሮጀክት በአጠቃላይ 3.5 ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የአፈር ቆረጣ ያለው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የአፈር ቆረጣ ስራው ተጠናቋል። ቀጣዩም እየተከናወነ ነው። 105 ሜትር ርዝማኔ ያለው የጀማ ወንዝ ድልድይ የዚህ ፕሮጀክት የግንባታ አካል ነው። የጀማ ወንዝ ላይ ከሚገነባው ድልድይ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ አራት ድልድዮችን፣ 126 የከልቨርቶች ስራንም በማካተት እየተሰራ መሆኑን የአስተዳደሩ መረጃ ያሳያል። የዚህ ፕሮጀክት መጠናቀቂያ ጊዜ ገና ቢሆንም፣ የወሰን ማስከበር ችግሮች አጋጥመዋል። የወሰን ማስከበር ችግሩ ተቋራጩ የኮንትራት ጊዜው እንዲራዘም ከወዲሁ ጥያቄ እንዲያቀርብ መንገድ ከፍቷል። ተቋራጩ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት እየታየ ነው። ታይቶ ተገቢ መሆኑ ሲታመንበት ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠዋል። ካልሆነ ግን የግንባታ ሥራው በተያዘለት የጊዜ ገደብ አጠናቅቆ እንዲያስረክብ ይደረጋል።

አጠቃላይ ፕሮጀክቶቹ ተገንብተው ሲጠናቀቁ ሙከጡሪን ከእንሳሮ ወረዳና ከመርሃ ቤት ወረዳ ጋራ በቅርበት ያስተሳስራሉ። ፕሮጀክቶቹ የአካባቢ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ምቹ በማድረግ በአካባቢው የሚገኘውን እምቅ አቅም ለመጠቀም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታሰባል። ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን አሟጦ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። አካባቢዎቹ የጤፍ ምርትን ጨምሮ በርካታ የአዝዕርት እህሎችን በማምረት የሚታወቁ በመሆናቸው አምራችን ከሸማች ጋር በማቀራረብ ግብይት ይበልጥ ያቀላጥፋል ።

ከመንገድ ግንባታው በቅርብ ርቀት ቡርቃ ወንዝ ላይ ከበልበሊት የመስኖ ግድብ ጋር በማስተሳሰር የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቱን ወደ መሃል ገበያ ለማድረስ ሁነኛ አበርክቶም ይኖረዋል። በተጨማሪም በአካባቢው የሚገኙትን በርካታ የቁም እንስሳት እና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን በፍጥነት ወደ ገበያ ለማድረስ ያግዛል።

የሙከጡሪ-ኮከብ መስክ እና ኮከብ መስክ ዓለም ከተማ መንገዶችን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ የወሰን ማስከበር ችግሮችን በዘላቂነት መቅረፍ ወሳኝ ነው። በቀጣይም የመንገድ ፕሮጀክቶች በወሰን ማስከበር ችግሮች ምክንያት እንዳይጓተቱ የወሰን ማስከበር ስራዎች የፕሮጀክቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚጠናቀቅበትን አካሄድ መከተል ያስፈልጋል። የወሰን ማስከበር ችግሮች ሳይቀረፉ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ማስጀመር መቆም ይኖርበታል።

ከዚህ ጎን ለጎን የመንገድ ፕሮጀክቶች ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት የሚኖረውን የላቀ አስተዋጽኦ ከግምት በማስገባት ህብረተሰቡ ንብረቱን በወቅቱ በማስነሳት የበኩሉን ሊወጣ ይገባል። ለራሱ ጥቅም የሚሰጠው የመንገድ ፕሮጀክት እንዲጓተት ምክንያት መሆን የለበትም። የካሳ ክፍያ በተፈጸመበት ማግስት ንብረቱን በማንሳት የመፍትሄ አካል ሊሆን ይገባል።

ወሰን የማስከበር ችግር ከግለሰቦች ባሻገር በመንግስት ድርጅቶች ዘንድም በግልጽ ይታያል። ለአብነት ያህል የውሃ መስመር፣ የቴሌ መስመሮች፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች እና ስልክ መስመሮች በሚፈለገው ወቅት አለመነሳት ለመንገድ ግንባታ መጓተት ምክንያት መሆኑን የመንገዶች ባለስልጣን እና ኮንትራክተሮች ሲናገሩ ይደመጣል። እንዲህ ያሉ ችግሮች የቆዩና የቀጠሉ ናቸው። ተቋማቱ ለአንድ ዓላማ የሚንቀሳቀሱ እንደመሆናቸው ተናብበው ሥራውን የጋራ አድርገው መሥራት ይኖርባቸዋል። መልዕክታችን ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለአገርና ሕዝብ እንጂ ለግል ብልጽግና አንድከም!

ነጻ አገር፤ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ፤ ሥነጽሑፍ፣ ኪነ ሕንጻ፣ ጥበብና ሌሎችም ታላላቅ ሥልጣኔዎች፤ በደም የተጻፈ ደማቅ ታሪክና ገድሎች፣… ሁሉም በየዘርፉ የሚገለጽባት ኢትዮጵያ፤ የሺህ ዓመታት ሥልጣኔዋ፣ ታሪክና ነጻነቷ በየመንግስታቱ ውስጥ እየተገለጸ ዛሬ ላይ ደርሷል። ንጉሳዊ ሥርዓትን ለዘመናት ያኖረች፤ በስር ነቀል አብዮት የተቃኘውን የሶሻሊዝም ርዕዮትን ለሁለት አስርት ዓመታት ለተጠጋ ጊዜ ያስተናገደች፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ከእነ ከፋፍለህ ግዛ እሳቤው ለሦስት አስርት ዓመታት ወገቧን እስኪጎብጥ ያዘለች፤ ዛሬም በመደመር ፍልስፍና የተቃኘውን የለውጥ ርዕዮት ይዛ እየተራመደች ያለች መልከ ብዙም ናት።

በዚህ ሁሉ ሂደት በሚገለጸው ገጸ ብዙ መልኳ አገር እና ሕዝብ እንዲሁም ሥርዓተ መንግስትና የሥርዓቱ መሪዎችና ተከታዮቻቸው የየራሳቸውን አሻራ አኑረው፤ የየራሳቸውን ታሪክ ጽፈው ማለፋቸውም እውነት ነው። በእነዚህ ሥርዓቶች መፈራረቅ ውስጥ ለሹመትና ኃላፊነት የበቁ ግለሰቦች፣ በአንድ በኩል ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ብልጽግና፤ በሌላ በኩል ስለ ግል እና ቡድናቸው ልዕልና ሲሰሩ ኖረዋል። ይሄው ምግባራቸውም በሕዝብ ሲያስወድስ አልያም ሲያስወቅሳቸው ቆይቷል።

ኢትዮጵያ፣ ለአገር ክብርና ሉዓላዊነት ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉ እልፍ አርበኞች ያሏትን የነበሯትን ያህል፤ ከባዕዳን ጋር ተሻርከው፣ ከወራሪዎች ጋር አብረው አገር የከዱ፣ ባንዳ ሆነው ለጠላት ያደሩ ልጆችም ነበሯት፤ አሏት። ለአገራቸው ሁለንተናዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ቀን ከሌት የሚተጉ ብርቅ ልጆች ያሏትን ያህል፤ በድህነት የነተበውን መቀነቷን ፈትተው ጾሟን ያሳደሯት ሌቦችም በጉያዋ ስር ይገኛሉ። ለከፍታዋ የጥበብ አበርክቷቸውን፣ የፍልስፍናና ሌላም ከፍ ብሎ የሚገለጽ አሻራቸውን ያሳረፉ ውድ ልጆች ያሏትን ያህል፤ የተሰራውን የሚያፈርሱ የእናት ጡት ነካሽና የበሉበትን ወጪት ሰባሪ ልጆችም አፍርታለች።

በዚህ ረገድ በዓድዋ፣ በማይጨውና በሌሎችም ስለ አገርና ሕዝባቸው ተዋድቀው ታሪክ የሚዘከራቸው፤ አክሱምን፣ ላሊበላን፣ ፋሲለደስን፣ የሐረር ግንብና ሌሎቹንም አንጽው ዛሬም የአገር ኩራት ሆነው የሚተረክላቸውን ያህል፤ በባንዳ ተግባራቸው፣ በእናት መቀነት ፈቺነታቸው፣ ወጣንበት የሚሉትን ሕዝባቸውን ከማገልገል ይልቅ የጭቃ ውስጥ እሾህ ሆነው የሚያደሙና የሚያስነቡትም ጥቂት አይደሉም። ይህ እውነት ትናንት የነበረ፤ ዛሬም ያለ፤ ምናልባትም ወደፊትም ሊኖር የሚችል ነው።



ይሄን ከታሪክ አጣቅሶ ለማየት ያህል፤ ጣሊያን ለዳግም ወረራ መጥታ ዳግም ተሸንፋ በወጣች ማግስት የጀግኖች አርበኞች ድል በተበሰረበት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ንጉሰ ነገሥት አፄ ኃይለሥላሴ ለሕዝብ ባስተላለፉት መልዕክት ላይ፣ "ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነጣጠሉ በሕግ ፊት ትክክለኛነትና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን። አገር የሚለማበትን፣ ሕዝብ የሚበለፅግበትን፣ እርሻ፣ ንግድ፣ ትምሕርትና ጥበብ የሚስፋበትን፣ የሕዝባችን ሕይወቱና ሀብቱ የሚጠበቅበትን፣ ያገር አስተዳደርም ባዲሱ ሥልጣኔ ተለውጦ ፍፁም የሚሆንበትን ይህን ለመሰለው ለምንደክምበት ሥራ አብሮ ደካሚ መሆን አለባችሁ።… የሕዝብንና የሕሊናን ነፃነት በመፍቀድ ለሕዝብና ለሐገር የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት ብርቱ ምኞታችንና አሣባችን ነው፤" ሲሉ መግለጻቸውን የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ይህ የድል ወቅት የታላቋ አገር መሪ መልዕክት የሚያስረዳን አንድ እውነት፤ መነጣጠል ለየብቻ መጓዝ የአገር በሽታ እንደነበረም ነው። በአንድ በኩል ለአገር ብልጽግና የሚበጁ ሥራዎችን ያለመታከት የሚከውኑ፤ ሕዝብ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ ሳይታክቱ የሚተጉ፤ ለሕዝቦች እኩልነትና ነጻነት ከፍ ያለ ዋጋ የሚከፍሉ የመኖራቸውን ያህል፤ በሌላው ገጽ ከልማቱ የሚሰርቁ፣ ሕዝቡን የሚያማርሩና የሚበድሉ፣ አገርንና ሕዝብን አፍነው የራሳቸውን ከፍ ማለት የሚሹ ስለመኖራቸው ነው።

ዛሬም ይሄው በሽታ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን እንደ መዥገር ተጣብቆ አልለቅ ብሎ እያሰቃያቸው ነው። እንደ አገርና ሕዝብ በጋራ እንበልጽግ ሲባል ብቻውን ለመበልጸግ (ያውም በኢኮኖሚው ብቻ) የሚሯሯጥ፤ ሕዝቦች በአንድ ቆመው ሕብረታቸውን እንዲያጠናክሩ ደፋ ቀና በሚባልበት ሁነት የግል ጥቅሙን ለማስቀጠል ሲል ብዙሃኑን ለማጋጨት የሚያሴርና የሚያጋጭ፤ ዜጎች የመልካም አስተዳደር ችግር ተወግዶላቸው ያለ እጅ መንሻ አገልግሎት ያግኙ ተብሎ ስራ ሲጀመር፣ ሂደቱን ሁሉ ዙሪያ ገደል የሚያደርጉ፤ በጥቅሉ ጉዞና ሕልማቸው ሁሉ ስለ አገርና ሕዝብ ሳይሆን ስለ ራሳቸውና ቡድናቸው ብልጽግና ብቻ የሆኑ ሹማምንትና ባለሙያዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። ይህ ደግሞ አሁን ላለንበት የብልጽግና መስመር የማይመጥን፤ ለአገርና ሕዝብም የማይበጅ እንደመሆኑ፤ ከዚህ አይነት አካሄድ መታረም ይገባል። ልፋትና ድካማችን ሁሉ ለግል ጥቅም ሳይሆን ለአገርና ሕዝብ ብልጽግና ሊሆን ያስፈልጋል።

ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

## ባሳገሩ፤ እፎይ ብሎ ይኑር በአገሩ!

ሶሎሞን በየነ

እንኳን ለሰው ለእንስሳ እሚራራው፤ በስህተት ክበድ (እርጉዝ) በግ ካረደ ንስሃ እሚገባው፤ ሐቀኛና ባለ ኃይማኖቱ፤ ባይኖረውም ማማረር እማይወደው፤ ባለው ነገር ተመስገን ብሎ የሚኖረው፤ ካለው ደግሞ ተቋርሶ እሚበላው፤ አደራ ብትሰጠው አደራ ማይበላው፤ "እውነቴን ነው ስልህ" ካለ ደግመህ እማታስምለው፤ ልበ ሙሉ፤ ቀጥተኛው፤ ኩርፊያውንም ደስታውንም ፊቱ ላይ የምታውቅበት፤ ወድቀህ ልትታሽ ቤቱ ብትሔድ "እኔን ለኔ ያርገው" እያለ ቁስልህን እሚያሽልህ፤ እምነት አክባሪው ህዝቤ፤ እንግዳ መጣ ብሎ አልጋውን ለቆ ዝቅ ብሎ እግር አጥቦ የሚያስተኛ፤ "እፈልግሃለሁ" ብለህ ተቆጥተህ ቤቱ ብትመጣ "እረ መጀመሪያ እህል ካፍህ አርግ" ብሎ ገበታ አቅራቢው፣ ባላገሩ ገጠሬው ወገኔ ነው።

ባላገሩ ዝክሩም ምክሩም በዝናብ አብቅሎ፣ በፀሐይ አብስሎ፣ በነፋስ አድርቆ፣… ከሚመግበው ከፈጣሪው ጋር ነው። ፈጣሪውን አምኖ በሰኔ ከጎተራው ዘሩን አውጥቶ ይዘራል። ፈጣሪም "የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ቢኖርህ ያልከው ይሆንልሃል" ብሎ በገባው ቃል መሰረት እርሱን አምኖ ከጎተራው አውጥቶ ዘሩን በማሳው ለበተነው አርሶ አደር የምህረት ዝናቡን ይልካል። ቃል ኪዳኑንም አያጓድልበትም። ባላገሩም ቢደላውም ቢከፋውም ሲነጋ ሲመሽ "ተመስገን" እያለ የፈጣሪውን ቸርነት ያመሰግናል። ሲከፋው "አንተ ታውቃለህ" ብሎ ለፈጣሪው አሳልፎ ይሰጣል እንጂ ጣቱን በማንም ላይ አይቀስርም።

ታዲያ ይህ ኩሩና ኃይማኖት ወገኔ በሰኔና ሐምሌ አንደፋርሶ አርሶ፣ በነሃሴና መስከረም አሽኮትኩቶ አርሞ፣ በህዳርና ታህሳስ አበራይቶ ወቅቶ ያመረተውን ምርት "ይሄ ከኔ ወገን ነው፤ ያ ከኔ ወገን አይደለም" ሳይል ምርቱን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለምንም አድሎ ገበያ አውጥቶ ያቀርባል። እርሱ ተጎሳቁሎ አምርቶ ሌላውን አጥግቦ ያሳድራል።

ነገር ግን ይህ ኩሩና ባለማተብ ወገኔ ጫማ ሳይለብስ እንቅፋት እየመታውና እሾህ እየወጋው ባስተማረ፤ በመርፌ የተጠቀመ (የተጣጣፈ) ልብስ ለብሶ እየሄደ "ፋሽን" እያለበሰ ባስተማረ፤ ኩርማን እንጀራ እና እፍኝ ቆሎ በልቶ እያደረ አጥግቦ ሳይማር ላስተማረ ውለታው ሲመለስለት ተወልዶ፣ ተዋልዶ፣ ታጋብቶና ታጋምዶ በሚኖርበት ቀየው ሲሳደድ፣ ሲፈናቀል፣ ሲገደል… ማየት ቅስም ይሰብራል። ከእጁ እሸት በልቶ፣ ከማጀቱ እርጎ ጠጥቶ… አድጎ በእርሱ ላይ ሰይፍ ማንሳትስ ምን አይነት የጭካኔ ጥግ ነው። ግፉስ ነገ ምን ያመጣብን ይሆን የሚለውን ሳስበው ጭንቅ ጥብብ ይለኛል።

> **ባሳገሩ ዝክሩም ምክሩም በዝናብ አብቅሎ፣ በፀሐይ አብስሎ፣ በነፋስ አድርቆ፣… ከሚመግበው ከፈጣሪው ጋር ነው። ፈጣሪውን አምኖ በሰኔ ከጎተራው ዘሩን አውጥቶ ይዘራል**

አርሶ አደሩ ሳይማር አፈር ገፊ ሆኖ መቅረቱ ቢያንገበግበውም፤ ልጆቹ ነገ የእርሱ እጣ ፈንታ እንዳይደርስባቸው እና ተምረው ተመራምረው ችግሩን እንዲቀርፉለት እንዲሁም ለአገር ለወገን አለኝታ እንዲሆኑ ነው ሳይማር ያስተማረው። ነገር ግን አርሶ አደሩ "ቀለም ቆጥረው ነገ ለአገራቸው ብሎም ለወገናቸው አለኝታና ጠበቃ ይሆናሉ" ብሎ ሳይማር ያስተማራቸው ልጆቹ በጎነጎኑት ሴራ ከቀየው ሲፈናቀልና ሲገደል ይስተዋላል። ደጉ ወገኔ አምርቶ አገርን አጥግቦ እንዳላሳደረ ተፈናቅሎ በሚገኝባቸው የመጠለያ ጣቢያዎች ከዚህ ግባ የሚባል ሰባዊ ድጋፍ አጥቶ ሲራቆት ማየት ደግሞ በጣም ያማል።

ያ ባላገሩ ኩሩ ወገኔ አርሶና አርብቶ አገርን ከማብላት ውጭ የፖለቲካ ዱካውን አያውቀውም። ነገር ግን ሳይማር ያስተማራቸው ልጆቹ አንዴ የብሄር ሌላ ጊዜ የኃይማኖት፣ የቋንቋ ወዘተ. የግጭትና የልዩነት ካርድ እየመዘዙ ደጉን ወገኔን በማያውቀው ተወልዶ ባደገበት አገሩ መቆሚያ መቀመጫ አሳጥተውት ይገኛሉ። እንዲሁም አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው ነጻነቷን ጠብቀውና ዳር ድንበሯን አስከብረው ያቆያትን አገር፤ ዛሬ ላይ ተምረው ያልተማሩ ማህይማንና ሆዳቸው አምላካቸው የሆኑ ፖለቲከኞች ህብረተሰቡ ለእልፍ ዘመናት የገነባውን የአንድነትና የመተባበር ድልድይ በመናድ አገሪቱን ለማፈራረስ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር እየሰሩ ይገኛሉ። ለዚህም ከሰሞኑ በአገሪቱ የሚስተዋለው በኃይማኖት ሽፋን ለዘመናት ተከባብሮ በሰላም የኖረውን ህዝብ እርስ በእርስ ለማባላት እየተደረገ ያለው የሽብር ተግባር አንዱ ማሳያ ነው።

እንደሚገባኝ፣ መማር የመጀመሪያው የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው። ከፍ ሲል ደግሞ የራቀውን አቅርቦ፣ የረቀቀውን ገልጦ፣ ለችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ በማፍለቅ ለአገርና ለወገን አለኝታ መሆን ነው። በዓለም ላይ በስልጣኔና በቴክኖሎጂ ማማ ላይ የሚገኙ አገራት ዜጎቻቸው ተምረው ተመራምረው ለችግሮቻቸው መፍትሄ በማበጀታቸው ነው እንደ ህዝብ ከፍ ያሉት። ነገር ግን በአገራችን ማወቅ ወይም መማር "መሰይጠን" ሆኖብን የተማረው ክፍል ሴራ እየጎነጎነ ለዘመናት ተከባብሮና ተዋዶ በሚኖረው ህዝብ ላይ የጥላቻና የመለያየት ግንብ ሲገነባ ይስተዋላል።

ተማርን የሚለው አካል፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በበሬ የሚያርሰውን አርሶ አደር ባላባት አገር "እስኪ የአርሶ አደሩን ሕይወት እናቅል" ከማለት እና ችግር ፈች ምርምር አድርጎ የወገኑን ችግር ከመቅረፍ ይልቅ በሴራ ህዝብን ከህዝብ ሲለያይ ነው የምናየው። ከዚህ አኳያ ተምረናል ብለን የምናስብ ሰዎች በተማርነው ትምህርት የወገናችን ችግር መቅረፍ ቢሳነን እንኳን የችግሩ ምንጭ ግን አንሁንበት።

በአንጻሩ የመንግስት ቀዳሚና በህገ መንግስቱ የተሰጠው ዋነኛ ኃላፊነቱ ሕግን በማስከበር የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ነው። በመሆኑም መንግስት በታሪክ አጋጣሚ እጁ ላይ የወደቀችን አገር እንደአባቶቻችን ነጻነቷን ጠብቆና ዳር ድንበሯን አስከብሮ ለመጪው ትውልድ ማስረከብ ይኖርበታል። ስለዚህ መንግስት የታሪክ ተወቃሽ እንዳይሆን ሕግን በማስከበር የዜጎችን በሰላም ወጥቶ የመግባት ጉዳይ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ሊሠራ ይገባል። ተልዕኮ ባላቸው ግለሰቦች በኅብረተሰቡ መካከል ሊቀሰቅሱ የሚታሰቡ ግጭቶችን ቀድሞ በማምከን የኅብረተሰቡን ለዘመናት ተከባብሮ የመኖር እሴት ሊጠብቅ ይገባል።

ሌላው መርከቧ ከሰመጠች የሚተርፍ ሰው እንደሌለ ኅብረተሰቡ ልብ ሊል ይገባል። ከዚህ አንጻር ሁሉም ዜጋ ማንንም ሳይጠብቅ የሚጠበቅበትን ለአገሩ የሚበጀውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል። ጥሩ ለመሥራት አቅም ባይፈቅድ እንኳን ለከፋ እና አገር ለሚያፈርስ አጀንዳ ተባባሪ ከመሆን መቆጠብ ይገባል። በጥቅሉ ያለ ሀጥያቱ በማያውቀው የገፈቱ ቀማሽ የሆነው ደጉና ኩሩው ባላገሩ ወገኔ ግፍና በደሉ ይበቃዋል። በሰላም ከቀየው ወጥቶ የመግባት ጥያቄው ሳይውል ሳያድር ተመልሶለት ባላገሩ እፎይ ብሎ ይኑር በአገሩ።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።



እንቁላል ፋብሪካ አደባባይ ላይ "መኖሪያ ቤታቸው"



አቶ አብዱልከሪምና ቤተሰቦቻቸው (ትምህርት ቤት የሄዱትን ሁለቱን ሳይጨምር)

## ዘጠኝ ነፍስ በጎዳና

ግርማ መንግሥቴ

ነጠላ በየፈርጁ ይለበሳል፤ ሕይወትም ያው ነው። እዚህ ሞቀ ሲሉት እዚያ ይቀዘቅዛቀል፤ እዚያ ቀዘቀዘ ሲሉት እዚህ እንፋሎቱ ይፋጃል። በመሆኑም "ፈርጁ ብዙ ነው" ብቻ ሳይሆን ቁጥሩ እራሱ የዓለምን ህዝብ ቁጥር ነው ማለት ይቻላል። ለምን? የእያንዳንዱ ሰው የሕይወት ፈርጅ የራሱና የራሱ ብቻ ስለሆነ። ይህ የትኛውም ዓለም ቢኬድ፤ ቢወጣም ሆነ ቢወረድ - የአይነት፣ ደረጃና ጥራት ልዩነት ካልሆነ በስተቀር፣ ያው ነው። ምናልባት ልዩነት አለ ከተባለ ሕይወት እንደ ሀብታምና ደሀ ("ም" ከንፈር (አፍ) ይገጠማል፤ "ሀ" ከንፈር (አፍ) ይከፈታል)፤ የጎዳና ሕይወት እንደ ግለሰብ፤ የጎዳና ሕይወት እንደ ቤተሰብ ሲታሰብ ነው።

ኑሮም ቢሆን ያው የሕይወት አካል ነውና አሁንም ያው ነው። መቃብር ይሙቅ አይሙቅ ባይታወቅም "…. መቃብር ይሞቃል" ስለ ተባለ ይሞቃል ማለት አይደለምና ኑሮ ሁሉ የሞላ፣ የደላና የተደላደለ አይደለም። ሁሉ በእጅ፤ ሁሉ በደጅ ... ሲሉት በእጅም በደጅም የሌለ ይኖራልና አለም ሙሉ ሆኖ አያውቅም ባዮች ትክክል ናቸው ማለት ይሆናል። ለምን ? ያው ከላይ እንዳልነው ነውና ባለቤትና ቤት አልባው፤ ጎዳና ተዳዳሪውና ባለ እልፍኝ ካዳራሹ በምንም መለኪያ አንድ ስለማይሆኑ። በተለይ ሕፃናት ሲጨመሩበት ጉዳዩ ይብሳል፤ ሲበዛም ሆድ ያስብሳል፤ አንጀትም ያላውሳል።

ምን አልባት ይህንን ታሪክ ስናነብና ባለታሪኮችን ስንመለከት ያ አንድ ሰሞን በየ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው ሲዘወተር፤ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የጎዳና ተዳዳሪዎች ብሶታቸውን ሲቆዝሙበት የነበረውና ሕፃናት ጥሩ አድርገው ያዜሙት "ጎዳና ነው ቤቴ ... / ... ችጋር ጎረቤቴ ..." ዜማ ጉዳዩን የበለጠ ያብራራዋልና እኛም እሱን ታስታውሱ ዘንድ እያስታወስን ወደ ታሪካችንና ባለታሪኮቻችን እንሂድ።

የዛሬው እንግዳችን አብዱልከሪም መሀመድ ይባላል። የ"ከ30 በላይ ..." እድሜ ያለው እና የወይዘሮ ኪላ ሽኩሪ ባለቤት ሲሆን፤ የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀ፤ የአራት (በተቀራረበ እድሜ የተወለዱ ህፃናት) አባት ነው። እህቱ (ዘምዘም መሀመድ)ን ከሁለት ልጆቿ ጋር ከመኖሪያ አካባቢያቸው አምጥቶ አብረው እየኖሩ ይገኛሉ። ባጠቃላይ፣ ከራሱ ጋር ዘጠኝ ቤተሰብ በአንድ ላስቲክ ቤት (ጎዳና) ይኖራሉ፤ አብዱልከሪም መሀመድም ዘጠኝ ቤተሰብ ያስተዳድራል። ይህንን አጠቃላይ መረጃ ይዘን ወደ ዝርዝሩ እንሂድ።

**አዲስ ዘመን፡- መቼ ነው ወደ እዚህ የመጣኸው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ከስምንት አመት በፊት።

**አዲስ ዘመን፡- እንዴት ልትመጣ ቻልክ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አንድ መንገድ ተቋራጭ ነበር፤ እሱ ጋ ተቀጥሬ።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ'ዚህ ከመምጣትህ በፊት የት ነበርክ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ሻሸመኔ። ከሻሸመኔ ነው የመጣሁት። የትውልድ አካባቢዬ እዛ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዛስ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** እየሰራን እያለ እሱ ስራውን አቋርጦ ጥሎ ጠፋ። በቃ፣ ከዛ ስራ አጥ ሆንኩ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ምን እየሰራህ ነው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ይህ ነው የምለው ቋሚ ስራ የለኝም። ተባራሪ ስራ ነው የምሰራው። አንዳንዴ እዚህ አካባቢ ለሊት ለሊት ጥበቃ። በወር እስከ 600 ብር አገኛለሁ። በቃ ይሄው ነው። አልፎ አልፎ እኔ ጀምሬ የነበረውን ስራ አሁን ባለቤቴ እየሰራች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምንድን ነው ስራው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ልብስ ማጠብ።

**አዲስ ዘመን፡- ከባለቤትህ ጋር ነው ወደ አዲስ አበባ የመጣኸው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አይ፣ አይደለም። እሷ በኋላ ነው የመጣችው። የተጋባነው ግን እዛ ነው። ስልክ ደውላ ችግር ሎይ ነኝ ና ውሰደኝ አለችኝ፤ ሄጄ አመጣኋት።

**አዲስ ዘመን፡- ልጆቹ ይማራሉ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አዎ የደረሱት ሁለቱ ይማራሉ። አንድ የእኔና አንድ የእህቴ ልሎች ይማራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ማስተማሩ አልቸገረህም? ማለትም ወጪው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አይ መንግስት ነው የሚያስተምርልኝ። በዚህ በኩል መንግሥት በጣም ነው የረዳኝ። እኔ ምንም አላወጣም። ከጫማና ዩኒፎርም ጀምሮ ቁርስና ምሳ ጭምር መንግስት ነው የሚችላቸው። እኔ እራት ብቻ ነው የማስበው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለኸው አደባባይ ላይ ነው። ተነስ ብትባልስ ምንድን ነው የምታደርገው፣ ወዴ'ትስ ትሄዳለህ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** የት እሄዳለሁ። ምንም መሄጃ የለኝም። እነዚህን ልጆች ይዤ ወዴት ነው የምሄደው፤ ምንም መሄጃ የለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- ተነስ ተብለህ አታውቅም?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አውቃለሁ። እናፀዳለን ብለው ሁሉ መጥተው ነበር። ነገር ግን እኔን ወደ የትም መውሰድ አልቻሉም። እነዚህን ሁሉ ልጆች ምንም ሊያደርጓቸው ስላልቻሉ ተመልሰዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግሥት አካላትን ጠይቀህ ታውቃለህ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አዎ። ያልገባሁበት ቀበሌና ወረዳ የለም። ሁሉም ጋ ሄጃለሁ፤ የቀረኝ ክፍለ ከተማ የለም። እባካችሁ የቀበሌ ቤት ስጡኝ ብዬ ስጠይቅ ነው የኖርኩት። እስከ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ቢሮ ድረስ ሄጃለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ምን አሉህ ታዲያ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አይ፤ ጥበቃ ላይ ያሉት አላስገቡኝም። አትገባም ተብዬ ተከለከልኩ።

**አዲስ ዘመን፡- የቀበሌ/ወረዳ አመራሮችን ስታናግር የሚሰጡህ ምላሽ ምንድን ነው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ምንም ምላሽ የለም። አንዳንዶቹ "ቆይ እስቲ" ነው የሚሉት፤ አንዳንዶቹ ምንም አይነት ምላሽ አይሰጡም። እነዚህን ሁሉ ቤተሰቦች ይዤ እየተሰቃየሁ መሆኔን ግን ሁሉም ያውቃሉ። የአካባቢው ሰው ሁሉ ያውቃል።

**አዲስ ዘመን፡- ደግመህ ስትሄድ የሚሰጡህ ምላሽ ወይም ምክንያት አለ፣ ካለ ምንድን ነው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** የሚሰጡኝ መልስ "የነዋሪነት መታወቂያ የለህም፤ በመሆኑም ልናስተናግድህ አንችልም" የሚል ነው። "እሺ መታወቂያ ስጡኝ" ብዬም ያልጠየኩበት ጊዜ የለም። ለምን እንደ ሆነ እንጃ ሁሉም ሊሰጡኝ አልቻሉም። እኔ ላለፉት ስምንት አመታት እዚህ መኖሬን ማንም ያውቃል፤ ይህ እየታወቀ እንደ ነዋሪ ሳልቆጠር መታወቂያ ሊሰጡኝ አለመቻሉ ለምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም። እኔ ከሌላ ቦታ (ሻሸመኔ) መምጣቴ ከሆነ ችግሩ ከየትም ልምጣ ከየት ያው ዜጋ ነኝ፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ። "እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ለምን አልስተናገድም?" የሚል ነው የእኔ ጥያቄ።

**አዲስ ዘመን፡- ለምን መልቀቂያ አምጥተህ እዚህ አታስገባም?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ወደ እዛ አልሄድኩም። እኔ እዚሁ ነው ያለሁት።

**አዲስ ዘመን፡- እዛ መልቀቂያ እንዲሰጡህ ጠይቀሀል?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አይ፤ አልጠየኩም።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አሁን እየነገርከን ካለው ችግርህ አኳያ፣ በተለይም ከመኖሪያ ቤት አኳያ እስከ ዛሬ ያናገረህ አካል፣ ተቋምም ይሁን ድርጅት ወይም ሌላ የለም?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ያልመጣ የለም። ብዙ ናቸው። ከኮተቤ ነው፣ ከዚህ ድርጅት ነው፤ ከዛ ድርጅት ነው ..... በማለት ብዙዎቹ መጥተው አናግረውኛል። እስካሁን ግን ምንም ያደረጉልኝ ነገር የለም። አንዱ ብቻ መጥቶ ለስድት ወር የቤት ኪራይ እንከፍልልሀለን፤ ከዚህ ተነስ አለኝ። አይሆንም አልኩ።

**አዲስ ዘመን፡- ለምን?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ስድስት ወር ስድስት ቀን ነው። "ከዛስ ወዴት እሄዳለሁ፤ ምን ውስጥ እገባለሁ? እነዚህን ሁሉ ልጆች ይዤ የት እወድቃለሁ?" በሚል ስጋት ነው ፈቃደኛ መሆን ያልቻልኩት። ድጋፉ ዘለቄታ ከሌለው አስቸጋሪ ነው። ልጆቼ ሕፃናት ናቸው። ዘጠኝ ነን። ዘጠኝ የቤተሰብ አባላት ....

**አዲስ ዘመን፡- ኑሮ እንዴት ነው፤ አይከብድም?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** በጣም ይከብዳል፤ ከባድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የቀለብ ሁኔታስ፣ ከየት ነው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** በፊት የሸገር ዳቦ በደንብ ይዞን ነበር። ማታ ማታ አስርም አስራ ሁለትም ብር ይገኝ በእሱ ወደ 10 ዳቦ አካባቢ ገዝተን እንመገብ ነበር። አሁን እሱም ቆመ። ኑሮ በጣም ችግር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደው ለመሆኑ፣ መጀመሪያውኑ ይህ አደባባይ መሆኑን እያወቅህ እንዴት አስበህ እዚህ ላይ ኑሮህን መሰረትክ?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** ይህ ቅድም እንዳልኩህ ከቦታው ጋር የተዋወኩት በስራ ምክንያት ነው። በመንገድ ስራ። ቀደም ሲል የመንገድ ተቋራጩ ስራውን አቋርጦ ሲጠፋ ሰራተኞች ተበተንን። እኔ እዚሁ ቀረሁ። መነሻው ይህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በክረምት እንዴት ነው፣ ዝናብ አያስቸግርም?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** አንዳንዴ ያስቸግራል። (እኛ እንደ ተመለከትነው በተቻለ መጠን በተገኘው ነገር ሁሉ "ቤቱ" ተጠቅጥቋል። ክፍሎችም አሉት። "ግቢ" ውስጥም ነው።)

**አዲስ ዘመን፡- አሁን "ጥያቄህን ባጭሩ አቅርብ" ብትባል ጥያቄህ ምንድን ነው?**

**አብዱልከሪም መሀመድ፡-** የመኖሪያ ቤት፤ የቀበሌ ቤት ብቻ ስጡኝ ነው የእኔ ጥያቄ። እነዚህን ህፃናት ይዤ የምጠለልበት ቤት ብቻ ነው ችግሬና ቤት ስጡኝ የሚል ነው የኔ ጥያቄ። ምግብ የትም ተውሎ፣ የትም ተበልቶ ይገባል። ቤት ከሌለ የት ይገባል? ምን ውስጥ ይገባል? ምንም ሆነ ምን፣ እኔም ሆንኩ የማስተዳድራቸው ቤተሰቦቼ ኢትዮጵያዊ ነን። እኔ ዜጋ ነኝ፤ ከየትም አልመጣሁም፤ ከዚሁ ከኢትዮጵያ ነው የመጣሁት። ስለዚህ ይህ ሁሉ ግንዛቤ ተይዞበት ቤት ብቻ እንዲሰጠኝ ነው የምጠይቀው። የልጆች ትምህርት ቤትን ነገር ያው መንግስት እያገዘኝ ስለ ሆነ ብዙም አልተቸገርኩም። የእኔም ሆነ የቤተሰቤ ዋና ችግር ቤት ነው። እንዲሰጠን የምንጠይቀውም እሱኑ ነው።


# ስፖርት





# የባህርዳር ስቴድየም አለም አቀፍ ጨዋታ የማስተናገድ ጉዳይ በቅርብ ቀናት ይታወቃል

**ቦጋለ አበበ**



**የባህርዳር ስቴድየም በካፍ ባለሙያ ተገምግሞ በቅርቡ አለም አቀፍ ጨዋታ ለማስተናገድ ውሳኔ ይጠብቃል፣**

በኮትዲቯር አዘጋጅነት የሚካሄደው የ2023 አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ሊካሄዱ ከአንድ ወር ያልበለጠ እድሜ ብቻ ይቀራቸዋል። የተለያዩ አገራትም ለማጣሪያ ጨዋታዎች ውድድር የሚያስተናግዱባቸውን ስቴድየሞች ለካፍ እያሳወቁ ይገኛሉ። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በጥቅምት ወር ባሳለፈው ውሳኔ ያስቀመጣቸው መስፈርቶች እስኪሟሉ ድረስ ኢትዮጵያ በሜዳዋ የምታደርጋቸው ጨዋታዎችን በገለልተኛ አገር እንድታከናውን መወሰኑ ይታወቃል።

ከእገዳው በኋላ የባህር ዳር ስቴዲየም ሁኔታን በማሻሻል ውድድር የማስተናገድ ፈቃዱን መልሶ እንዲያገኝ የተለያዩ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፤ በመጫወቻ ሜዳ፣ በሚዲያ ክፍል፣ በቪአይፒ፣ በተመልካች ፋሲሊቲ፣ በህክምና ክፍልና ተያያዥ አገልግሎት መስጫዎች ላይ የተደረገውን የማሻሻያ ሥራ ከካፍ ተወክለው የመጡት ሚስተር ኢቫን ኪንቱ ከትናንት በስቲያ በስቴድየሙ ተገኝተው ምልከታ አድርገዋል።

ሚስተር ኢቫን የምልከታቸውን ሪፖርት ለካፍ ካቀረቡ በኋላ ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር የምታደርገውን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ሁለተኛ ጨዋታ ጨምሮ በቀጣይ በሜዳዋ የምታደርጋቸው ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን እንድታከናውን የሚያስችላት ፈቃድ ማግኘት ያለማግኘቷ ጉዳይ በቅርብ ቀናት ምላሽ እንደሚያገኝ ይጠበቃል።

ካፍ ባለፈው አመት ከሃያ በላይ የአፍሪካ ስቴድየሞች አለም አቀፍ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ ዝቅተኛ መስፈርቶችን አያሟሉም በማለት ማገዱን ተከትሎ በርካታ አገራት በቅርቡ የሚያደርጓቸውን የማጣሪያ ጨዋታዎች በገለልተኛ ሜዳ ለማድረግ እንደሚገደዱ ስጋት ሆኖ ነበር። ይሁን እንጂ ካፍ ባለፉት የተወሰኑ ቀናት በርካታ ስቴድየሞችን ገምግሞ መጪዎቹን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች እንዲያስተናግዱ ይሁንታ እንደሰጠ አሳውቋል።

በዚህ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ አርባ ስምንት አገራት የሚሳተፉ ሲሆን፣ ካፍ ይህ ዘገባ እስከ ተጠናከረበት ሰአት ድረስ ለሰላሳ ስቴድየሞች ብቻ ጨዋታዎችን እንዲያስተናግዱ ይሁንታ መስጠቱ ተረጋግጧል። የቀሪ አስራ ስምንት አገራት ስቴድየሞችም በቀጣይ ጥቂት ቀናት ካፍ የግምገማ ቡድኑን ልኮ በሚያገኘው ግብረመልስ መሰረት ይሁንታውን ይሰጣል ወይም እገዳውን ያጸናል ተብሎ ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ከአንድ አመት በላይ አለም አቀፍ ጨዋታዎችን በሜዳቸው እንዳያስተናግዱ እገዳ ከተጣለባቸው አገራት መካከል አንዷ መሆኗ ይታወቃል፤ ካፍ በቀጣይ ቀናት ስቴድየሞችን ገምግሞ መጪዎቹን የአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታዎች ማስተናገድ አለማስተናገዳቸውን ከሚወስንላቸው አገራት መካከልም ኢትዮጵያ አንዷ እንደምትሆን ታውቋል።

በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊና ጊኒ ጋር የተደለደለችው ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የማጣሪያ ጨዋታ ከማላዊ አቻዋ ጋር ከሜዳዋ ውጪ ታደርጋለች። በመጪው ሰኔም ከግብጽ ጋር በሜዳዋ ትጫወታለች። ዋልያዎቹ ከፈርኦኖቹ ጋር ለሚያደርጉት ፍልሚያ ኢትዮጵያ አሁን ስቴድየሞቿ ከሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ከባህርዳር ስቴድየም በስተቀር ሌሎቹን ለካፍ ግምገማ ማቅረብ አልቻለችም።

የቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎችን ከዛሬ ጀምሮ የሚያስተናግደው የባህርዳር ስቴድየም ባለፉት በርካታ ወራት በካፍ ግብረመልስ መሰረት እድሳት ሲደረግለት መቆየቱ ይታወቃል። የተደረገለት እድሳት ተጠናቆ ካፍ ብቁ መሆኑን ይሁንታ ካልሰጠው ግን ኢትዮጵያ በገለልተኛ አገር ለመጫወት እንደምትገደድ ተረጋግጧል።

ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ጨዋታዎችን እንዳታስተናግድ ከአመት በፊት በካፍ ከመታገዷ አስቀድሞ የባህርዳር ስቴድየም በብቸኝነት አለም አቀፍ ጨዋታዎች ሲካሄዱበት መቆየቱ ይታወቃል። የባህርዳር ስቴድየም ጨዋታዎችን ሲያስተናግድ የነበረውም በካፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከስር ከስር የማሻሻያ ስራዎችን እንዲያከናውን ነበር። የማሻሻያ ስራዎቹ እየተከናወኑ በነበረበት ሁኔታም ካፍ በቂ ማሻሻያ አልተደረገም ብሎ በማመን እገዳውን መጣሉ ይታወሳል። በዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለኳታሩ የአለም ዋንጫ ማጣሪያ የመጨረሻ ጨዋታዎች ጋናንና ዚምቡዋቤን በገለልተኛ ሜዳ ለመግጠም ተገዷል።

ለመጪው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከሚሳተፉ አርባ ስምንት አገራት ሃያ አራቱ ብቻ ወደ አፍሪካ ዋንጫ በሚያልፉበት ፉክክር ዋልያዎቹ ከጠንካራው ምድባቸው ቢያንስ ሁለተኛ ሆነው ለማለፍ በሜዳቸውና በደጋፊያቸው ፊት ወሳኝ ነጥቦችን መሰብሰብ እንደሚኖርባቸው ይታመናል። በስቴድየሞች መስፈርት አለማሟላት ይህ እድል ከእጃቸው እንዳይወጣ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ያለው ስጋት በቅርብ ቀናት ይለይለታል።

ካፍ ከትናንት በስቲያ ለአፍሪካ ዋንጫው ማጣሪያ ጨዋታዎች ይሁንታ ከሰጣቸው ሰላሳ ስቴድየሞች መካከል ከዋልያዎቹ ጋር በምድብ ማጣሪያው የተደለደለችው ግብጽ አንዷ ስትሆን ጊኒና ማላዊ የካፍን ይሁንታ ለማግኘት እንደ ኢትዮጵያ በቀጣይ ቀናት ይጠባበቃሉ።

የአልጄሪያው ኮምፕሌክስ ደ ኦራን፣ የአንጎላው ስታዲዮ ናሺዮናል፣ የቤኒኑ ስታድ ዲ አሚቴ፣ የቦትስዋናው ኦቤድ ኢታኒ ስታዲየሞች ይገኙበታል፡፡ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ካሜሩን፣ ሴኔጋል፣ ኢኳቶሪያል ጊኒ፣ ጋቦን፣ ኮሞሮስ፣ ጋና፣ ማሊ፣ ማዳጋስካር ስቴድየሞቻቸው ጨዋታዎችን እንዲያከናውኑ ፍቃድ ከተሰጣቸው አገራት መካከል ይገኙበታል።

የአፍሪካ ዋንጫውን የምታስተናግደው ኮትዲቯር በቀጥታ የምታልፍ አገር ብትሆንም የማጣሪያ ጨዋታዎችን እንዲያስተናግዱ ከተመረጡ ሰላሳዎቹ ስቴድየሞች መካከል አለመካተቷ አስገራሚ ነው። ሌሴቶ፣ ናሚቢያና ደቡብ ሱዳን ደግሞ በገለልተኛ ሜዳ ጨዋታዎችን እንደሚያደርጉ ያረጋገጡ አገራት ናቸው።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የዋቻ ከተማ አስ/ር ፋይናንስ ጽ/ቤት ህጋዊ የግንባታ ሥራ ተቋራጮችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ፀጥታ ጽ/ቤት እና ፖሊስን ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ ማሰራት ይፈልጋል:: ስለዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርት የምታሟሉ የግንባታ ሥራ ተቋራጮች በውድድሩ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃል ::

**ሀ.የመዳደሪያ መስፈርቶች ተጫራቾች :**

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋብ የሆኑ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ሰርተፍኬት እና የአቅሪቢነት ምዝገባ “ምስክር ወረቀት ያላቸው
2. በጠቅላላ ሥራ (GC) ወይም ህንጻ ግንባታ ሥራ (GBC) ተቋራጭነት ዘርፍ ደረጃ 6 እና ከዚያ በላይ የሆኑት
3. ከሚመለከተው አካል የታክስ ክሊራንስ ማረቅብ የሚችሉ እንዲሁም በሥራ ዘመኑ አስፈላጊውን የንግድ ሥራ ፍቃድና የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ያደረጉ ሊሆን ይገባል::

**ለ. የውድድር ሂደትና የጨረታ ሰነድ አቀራረብ በመመሪያ**

- ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የምታሟ ተጫራቾች በዋቻ ከተማ አስ/ር ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ዋናውንና የማይመለስ አንድ ኮፒ ይዘው በአካል በመገኘት የማይመለስ ብር 300/ሦስት መቶ ብር/ ከፍለው የጨረታውን ሰነድ መግዛት ይችላሉ::
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበርያ ብር 50,000/ሃምሳ ሺህ ብር/በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ (CPo) ማቅረብ አለባቸው ::
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ፋይናሺያልና ቴክኒካል ዶክሜንት እያንዳንዱን አንድ ኦርጅናል በተጨማሪ ሁለት ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን የእያንዳንዱን ፋይናሺያልና ቴክኒካል ዶክሜንት ጥራዞች ኮፒ ለየብቻ በፖስታ እንዲሁም ኦርጅናል ፋይናሺያን እና ቴክኒካል ዶክሜንት በተመሳሳይ እያንዳንዱን በየራሱ ፖስታ ካሸጉ በኋላ በአንድ ፓስታ አጠቃልለው በማሸግ /ቴክኒካል/ ፋይናሺያል ኮፒ እና ቴክኒካል/ ፋይናሺያል ኦርጅናል በማለት/ በመጨረሻም የጨረታ ማስከበርያ ሰነድ ሲፒኦ (CPo) ጨምረው በእናት ፖስታ በማጠቃለል በሰም አሽገው ማቅረብ አለባቸው።
- ተጫራቾች የሚያቀርቧቸው በእያንዳንዱ የታሸገ ፖስታ ላይ የተጫራቹ መ/ቤት ድርጅት ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የአጫራቹ መ/ቤት ስምና አድራሻ ጨረታው የቀረበለት ፕሮጀክት ስም እንዲሁም የዶክሜንቱ ምንነት፣ መለያ (ምሳሌ:- ቴክኒካል ኮፒ፣ ኦርጂናል ፋይናሻል ሲ.ፒ.ኦ (CPo ...) ወዘተ በማለት) በጉልህ ፅሁፍ ማስፈር፣ የድርጅቱን ማህተም ማሳረፍና መፈረም ይጠበቅባቸዋል።
- ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ21 (ሃያ አንድ) ተከታታይ ቀናት ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን በ21ኛው ቀን ከጧቱ ልክ 4፡30 ሠዓት ላይ በዋቻ ከተማ አስ/ር ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ተዘግተው በተመሳሳይ ቀንና ቦታ 7:30 ሠዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። በጨረታው የመክፈቻ ሰዓትና ቦታ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ መክፈቻውን ሥርዓት አያስተጓጉልም::
- ከላይ የተጠቀሰው 21ኛው ቀን ብሔራዊ ወይም ህዝባዊ በዓል ላይ ወይም ቅዳሜና እሁድ ላይ ሆኖ ከተገኘ የጨረታው መዝጊያም ሆነ መክፈቻ በቀጣዩ የሥራ ቀን በተጠቀሰው ቦታ እና ሰዓት ይካሄዳል።
- መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::
- ይህንን ጨረታ አስመልክቶ ለማናቸውም ተጨማሪ መረጃ ከዋቻ ከተማ አስ/ር/ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በመድረስ አልያም በስልክ ቁጥር 047-3-80-04-59 በመደወል አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይቻላል።

**በደ/ም/ ኢት/ሕ/ክ/መ/ በካፋ ዞን የዋቻ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**



## የጣውላ ምርት ግልጽ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ

የጨረታ ቁጥር OFWE/XA05/2014 በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት በእያንዳንዱ የጣውላ ዓይነት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል።

**ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ**

1. በአርሲ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
2. በባሌ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
3. በቦረና ጉጂ ራደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያዎች ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
4. በፊንፊኔ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
5. በሐረርጌ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
6. በኢሉአባቦራ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
7. በጂማ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
8. በወለጋ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤

**በመሆኑም፤**

1. የጣውላ የቤትና የቢሮ እቃዎችና ተዛማጅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም Tin number ያላቸውና እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ ስለ ጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ የጨረታ ሰነድ ለእያንዳንዳቸው 100/መቶ ብር/ በመክፈል ቀበና ሼል /አይል ሊቢያ አጠገብ በሚገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 201 እና ጨረታው በሚወጣበት በወለጋ ቅ/ጽ/ቤት (ጊንቢ) በጂማ ቅ/ጽ/ቤት (ጂማ) በኢሉአባቦራ ቅ/ጽ/ቤት (መቱ) በአርሲ ቅ/ጽ/ቤት (አርሲ ነጌለ) ፊንፊኔ ቅ/ጽ/ቤት (ፊንፊኔ)በሐረርጌ ቅ/ጽ/ቤት (ጭሮ) በቦረና ጉጂ ቅ/ጽ/ቤት (አዶላ) በመግዛት በጨረታው መሣተፍ ይችላሉ።
2. ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው ጨረታ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ለ15 ተከታታይ ቀናት ይቆይና ግንቦት 03 ቀን 2014 ጠዋት 4፡00 ሰዓት ታሽጎ 4፡30 ላይ ይከፈታል።
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid bond) የሚሆን ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ 5% በማስላት በድርጅቱ ዋና መ/ቤት የምትጫረቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች ፤ በቅ/ጽ/ቤት የምትጫረቱ መ/ቤቱ ከሚገኝበት ከተማ በባንክ በተረጋገጠ ደረሰኝ (cpo) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል።
4. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0111240249 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።

**የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት**